# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

እሁድ 84 ዓመት ቁጥር 012 መስከረም 12 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




## የህትመት ሚዲያ ተግዳሮቶችን እንዴት ማሻገር ይቻላል?

ዳግማዊት አበበ

ዜና ትንታኔ

የሀገራችን የመገናኛ ብዙሃን ዘርፉ እድገት እያሳየ ሲሆን በተቃራኒው ፈር ቀዳጁ የህትመት ሚዲያ ማደግ ባለበት ልክ እያደገ አይደለም፡፡ ለዚህም የማንበብ ባህል መቀነስ፣ መረጃን በቀላል የዲጂታል አማራጮች ማግኘት መቻል እና የህትመት ዋጋ መናር የህትመት ሚዲያው እንዳያድግ የሚጎትቱት ምክንያቶች እንደሆኑ የዘርፉ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡

የህትመት ሚዲያው ለማህበረሰባዊ እድገት ከፍተኛ ሚና ያለውና የማንበብ ባህልን የሚፈልግ ዘርፍ ቢሆንም በሀገራችን ያለው የማንበብ ባህል ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሸረሸረ መምጣቱ እውን ነው፡፡

የህትመት ሚዲያ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ፈውስ ያገኙ ልቦች

ዳግማዊት አበበ

ዜና ሀተታ

አክሊለ በቀለ ትባላለች፡፡ ቤተሰቦቿ የልብ ችግር እንዳለባት ያወቁት የስድስት ወር ህጻን እያለች ነው። የነበረብኝ የልብ ችግር የልብ ቀዶ ህክምና ማድረግ እንዳብኝ የሚያስገድድ ነበር የምትለው አክሊለ የዛሬ 23 ዓመት ገደማ የሁለት ዓመት ከስድስት ወር ህጻን እያለች በእስራኤል ሀገር በሚገኝ ዓለም አቀፍ ግብረ ሰናይ ድርጅት አማካኝነት የቀዶ የህክምና ማድረጓን

ፈውስ ያገኙ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አክሊለ በቀለ



ልዑል ሰገድ ደሳለኝ



## የዘንድሮ ኢሬቻ በዓል መስከረም 25 እና 26 ይከበራል

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- የ2017 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል ባህላዊ እሴቱን በጠበቀ መልኩ መስከረም 25 ቀን በአዲስ አበባ ሆራ ፊንፊኔ ፣ መስከረም 26 ቀን ደግሞ በቢሾፍቱ ሆራ ሃርሰዴ እንደሚከበር የኦሮሚያ ሕብረት አባገዳዎች አስታወቀ።

የመጫ አባገዳ እና የኦሮሚያ ሕብረት አባገዳዎች ሰብሳቢ አባገዳ ወርቅነህ ተሬሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የኦሮሞ ሕዝብ ከሚያከብራቸው የእርቅና የሰላም ክብረ በዓላት መካከል ኢሬቻ አንዱ ነው። በዓሉም ዘንድሮ መስከረም 25 ቀን በአዲስ አበባ ሆራ ፊንፊኔ፣ መስከረም 26 ቀን ደግሞ በቢሾፍቱ ሆራ ሃርሰዴ ይከበራል፡፡

የ2017 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል መስከረም 25 ቀን በአዲስ አበባ ሆራ ፊንፊኔ ፣ መስከረም 26 ቀን ደግሞ በቢሾፍቱ ሆራ ሃርሰዴ እንደሚከበር አመልክተው፤ በዓሉን ለመታደም የሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች የባህል ልብሳቸውን በመልበስ በዓሉን በፍቅር፣ በአንድነትና በሰላም ማክበር እንደሚገባ ተናግረዋል።

የዘንድሮው የኢሬቻ በዓል በሆራ ፊንፊኔና በሆራ ሀርሰዴ በልዩ ሁኔታ ደምቆ እንዲከበር በርካታ የዝግጅት ሥራዎች እየተከናወኑ ነው ያሉት አባገዳ ወርቅነህ፤ በዚህም ለኢሬቻ በዓል አስተባባሪ

የዘንድሮ ኢሬቻ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል
















ዜና




## በትምህርት ቤቱ የተገኘው ከፍተኛ ውጤት የአስተማሪዎች እና የተማሪዎች የጥንካሬ ውጤት ነው

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በቓላሚኖ ልዩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለከፍተኛ ትምህርት መግቢያ የተገኘው ከፍተኛ ውጤት የአስተማሪዎች እና የተማሪዎች ጥንካሬ ማሳያ መሆኑን ተገለፀ።

የትምህርት ቤቱ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ መምህር ታጋይ ዘበነ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳሉት፤ ትምህርት ቤቱ በ1990 ዓ.ም የተመሠረተ ሲሆን፤ እስከ አሁን ከሁለት ሺህ አምስት መቶ በላይ ተማሪዎችን አስተምሮ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማስገባት ችሏል፡፡ ዘንድሮች በትምህርት ቤቱ የተገኘው ከፍተኛ ውጤት የመምህራንና የተማሪዎቹ ጥንካሬ አንዱ ማሳያ ነው፡፡

በክልሉ ከሚገኙት ትምህርት ቤቶች የስምንተኛ ክፍል ውጤታቸው ከፍተኛ ነጥብ ያመጡ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤቱ ገብተው አራት ዓመት ነፃ የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ እንደሚያደረግ የጠቀሱት ኃላፊው፤ ተማሪዎቹ የነበራቸው ዕውቀት በማዳበር የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ አመርቂ ውጤት እያመጡ እንደሚገኙ አመልክተዋል፡፡

ትምህርት ቤቱ በትግራይ ልማት ማህበር የተመሠረተ ሲሆን፤ ዋና ዓላማው የተማረ የሰው ኃይል በማፍራት የሕዝብን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለመቅረፍ እና ሀገርን በዕውቀት ከፍ ለማድረግ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

በክልሉ ችግር ለመፍታት የተሻለ ዕውቀት እና ምርምር ላይ ትኩረት በማድረግ እና ትምህርት ቤቱ ለሌሎች አርአያ እንዲሆን እንዲሁም ሌሎች ተመሳሳይ ትምህርት ቤቶች እንዲከፈቱ ታስቦ መመስረቱን ተናግረዋል፡፡

በጦርነቱ ምክንያት ተማሪዎች ከባድ ችግር ቢያሳልፉም የመማር ማስተማር ሂደቱ 2015 ዓ.ም መጨረሻ ላይ መጀመሩን ጠቅሰው፤ የሶስት ዓመት መርሃ ግብር በአንድ ዓመት በማስተማር በጥረት ከፍተኛ ውጤት ማምጣት መቻሉን አብራርተዋል፡፡

አሁንም ቢሆን አዲሱ የትምህርት ፖሊሲ ከመጣ ወዲህ ዘንድሮ 284 ተማሪዎች መፈተናቸው ጠቅሰው፤ ከፍተኛ ውጤት 675 ወንዶችና 662 ሴቶች ከፍተኛ ውጤት ያመጡ ሲሆን 92 ተማሪዎች ደግሞ 600 ማምጣታቸውን ተናግረዋል፡፡ ትምህርት ቤቱ 567 አማካይ ውጤት በማስመዝገብ የቆየ የብልጫ ታሪኩን አምናና ዘንድሮም ማስቀጠል መቻሉን ገልጸዋል፡፡

በትምህርት ቤቱ ተምረው የወጡ ተማሪዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚታወቁት ኩባንያዎች ጎግል ማይክሮሶፍት፣ ናሳ፣ በሀገር ውስጥም በኢንሳ እንዲሁም በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች በማስተማር እና በምርምር ሥራዎች ተሠማርተው ይገኛሉ፡፡

የቓላሚኖ ተማሪዎች ውጤት ሲታይ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥም ቢሆን ጥረትና ዓላማ በመሰነቅ የአስተማሪዎች እና የተማሪዎች ይህን ውጤት ማስገኘቱ እጅግ የሚያስደስት ነው ብለዋል፡፡ የቀድሞ ተማሪዎች አሁን በተለያየ የሥራ መስክ የሚገኙ ውጤታማ ምሁሮች ከያሉበት የሚሰባሰቡበት መድረክ በማዘጋጀት ለሀገራቸው አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ ጥረቶች እየተደረጉ መሆኑንም አመልክተዋል፡፡

# አብሮነትንና ሰላምን የሚያውጀው የእርቅ በዓል "ያሆዴ"

**አማን ረሺድ**

ዜና ሀተታ

ወርሃ መስከረም ለኢትዮጵያውያን የግል ስጦታ ናት። የአዲስ ዓመት መባቻ፣ የብሩህ ተስፋ፣ የአዲስ ሕይወት፣ የአዲስ ምኞት፣ የምህረትና የቸርነት ደጆች የሚከፈቱባት የወሮች አውራ ናት። ምን ይህ ብቻ የሰዎች ግንኙነት የሚያይልበትና የሠብዓዊነት ምህዋር የሚጠነሰስባት ወርሃ በኩር እንደሆነች በብዙሃኑ ኢትዮጵያውያን ልብ ታትማለች።

በወርሃ መስከረም ሰማይ የክረምት ጠባይዋን ረስታ ከደመናው፣ ከጉምጉምታው ተላቃ ፣ መሬትም ከጭቃ ተላቃ፣ የውሃ ማማዎች ጠርተው፣ አበባዎች ፈክተው፤ ቡቃያዎችም ለምልመው በመልካም ወዘና ለፈጣሪያቸው የሚያረግዱ ይመስላሉ። ታዲያ በዚህ ጊዜ ሰዎች ለፈጣሪቸው ምስጋና የሚያቀርቡባት ወር ናት። በኢትዮጵያን የዘመን ቀመር መስከረም አንድ "ሀ" ብሎ የጀመረው ዘመን መለወጫ በወሩ አጋማሽ ቀናት በአደባባይ በዓላት ይዋባሉ።

በተለይ በደቡባዊ የኢትዮጵያ ክፍለ ግዛት አጀብ የሚያሰኙ በዓላት መስከረም ወር ላይ ጎልተው ይደምቃሉ፡፡ መስቀል፣ ጊፋታ፣ ያሆዴ፣ መሰላ ከብዙዎቹ መካከል ተጠቃሽ ናቸው። በዓላቱ ባህላዊ እሴታቸው ተላብሰው የአዲስ ዓመት መቀበያ በመሆናቸው ልዩ ስሜትን ይፈጥራሉ። የአካባቢው ማህበረሰቦችም አሮጌውን ዓመት በመሸኘት ተናፋቂውን አዲስ ዓመት ለመቀበል ሽርጉድ ሲሉ ይታያሉ።

የሀድያ ብሔር የራሱ የሆኑና ተለይተው የሚታወቁ ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፉ የመጡና ጠብቆ ያቆያቸው የበርካታ ባህላዊ እሴቶች ባለቤት ሲሆን በተለያዩ ክዋኔዎች በመታጀብ በየዓመቱ በወርሃ መስከረም በድምቀት የሚከበረውን የ "ያሆዴ" የሀዲያ ዘመን መለወጫ በዓልን አንዱ ነው። "ያሆዴ" ዘመድ አዝማድና ቤተሰብ የሚገናኝበት የተጣሉ እርቅ በማውረድ ሰላምን የሚያጸኑበትና ከጨለማው ክረምት ወደ ፈካው ፀደይ መሸጋገርን ማብሰሪያም ነው።

የሀድያ ዞን ምክትል አስተዳዳሪ በፍቃዱ ገብረሃና (ዶ/ር)፤ "ያሆዴ" የብሔሩ ተወላጆች የሚገናኙበት፣ የተጣላ የሚታረቅበት፣ ሰላምና ደስታ የሚያብብበት በዓል መሆኑን ይገልጻሉ። ያሆዴ በብሔሩ የአዲስ ዓመት ማብሰሪያ፣ ብሩህ ተስፋ፣ ፍቅርና መልካም ነገር የሚሰነቅበት እንሆነም ያብራራሉ።

በያሆዴ በዓል የተጣላ ሳይታረቅ በዓሉ አያከበርም የሚሉት በፍቃዱ (ዶ/ር)፤ በዓሉ የተረራቁ ዘመዶች የሚጠያየቁበት፣ የሰላም ማስተሳሰሪያ ትልቅ ባህል ስለመሆኑም ይናገራሉ። ያሆዴን የመሰሉ የብሔሩ ባህላዊ እሴቶች ተጠብቆ እንዲኖር፤ እንዲተዋወቅና የበዓሉ ክዋኔዎች ሳይበረዙ ወደ ትውልድ ለማሸጋገር ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው ባይ ናቸው።



በቀጣይ ጊዜያት የያሆዴ በዓልን በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) ከማይዳሰሱ የዓለም ቅርሶች መካከል አንዱ ሆኖ እንዲመዘገብ ከተለያዩ አካላት ጋር እየተሰራ መሆኑን ይጠቁማሉ።

የሀድያ ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ኃላፊ አቶ መስፍን በጋለ በበኩላቸው፤ በያሆዴ በዓል ያለው ለሌለው አካፍሎ በመተሳሰብ እና በፍቅር አዲሱ ዓመት በደስታ የሚቀበልበት ሀዲያ ሕዝብ መገለጫ መሆኑ ይናገራሉ።

እንደ መምሪያ ኃላፊው ገለጻ፤ ያሆዴ ሰላምን፣ ወንድማማችነትን፣ አብሮነትን የሚያንጸባርቅ በዓል ነው። በቀጣይ የያሆዴ በዓልን ይበልጥ በማጉላትና በማጎልበት፣ ወደ አካባቢው የሚመጡ ጎብኚዎችን ቁጥር ለማሳደግ መምሪያው ከባለድርሻ አካላት ጋር ይሠራል።

በበዓሉ ወጣት ልጃገረዶች የቤቱን ወለል ቆፍረው በመደልደልና የተለያዩ ውበት የሚሠጡ ቀለማት ያላቸውን ኖራዎችን በመጠቀም የቤቱን ውስጥና የውጭ ግርግዳን በመቀባት የተለያዩ ጌጥ ሠርተው ያስውባሉ ይላሉ።

ወጣት ወንዶች በበኩላቸው ከነሃሴ መግቢያ አንስተው አባቶቻቸው የሚያሳዩዋቸውን ግንድ ቆርጠው ለምግብ ማብስያ እንዲውል ፈልጠው ያደርቃሉ የሚሉት ኃላፊው፤ ለችቦ የሚሆኑ እንጨቶች ከጫካ በመልቀም አስረው እንደሚያዘጋጁ ያብራራሉ። በተጨማሪም ወጣት ወንድ ልጆች ያሆዴ /አሌ/ ጭፈራ ሲጫወቱ ያነጋሉ፤ ይህ ጭፈራ ከያሆዴ በዓል ውጭ አይጨፈርም ነው ያሉት፡፡

በዕለቱ ለእርድ የተዘጋጀው ሠንጋ ከቀረበ በኋላ የባህል ሽማግሌዎች የበሬውን ሻኛ በለጋ ቅቤና በሠርዶ ሳር ይቀቡታል፤ ወተት ያፈሱበታል፡፡ ይህም በሚከናወንበት ወቅትም ክፉ ቀን አይምጣ፣ ርሃብ ሰቀቀን ይጥፉ፣ ጥጋብ ይስፈን፣ በአካባቢው በሀገሩ ጥጃ ይቦርቅ፣ ልጅ ይፈንጭበት፣ ሀገር ሰላም፣ ገበያ ጥጋብ ይሁን፣ ሰማይና ምድሩ ይታረቁን በማለት ምረቃቱን ፈጽመው በሬው ይጣልና የእርድ ሥርዓት እንደሚካሄድ ያመላክታሉ፡፡

በዓሉ የሚከውኑበት ቦታ (ነፈራ) የሚባል ሲሆን ቦታው በማህበረሰቡ ዘንድ በአባወራ ጊቢ የተለያዩ ባህላዊ ክዋኔዎችን ለመከወን እንዲመች በተለያዩ የጥላ ዛፎች ተውቦና ተከልሎ የተዘጋጀ ሥፍራ ነው፡፡ በዚህ መሠረት (ሀዲይ ነፈራ) የሚለውን ስያሜ አግኝቶ በዓሉ ሁሉም የብሔሩ ተወላጆች በሥፍራው ላይ ተሰባስበው በድምቀት ያከብራሉ ሲሉ ነው የተናገሩት፡፡

በሀድያ ብሔር ሩቅ ያሉ ልጆች ወላጆችንና ዘመዶችን ለመጠየቅ ለመመረቅ ቀጠሮ የሚይዙለት በያሆዴ ክብረ በዓል በመሆኑ በዓሉ ዘመድ አዝማድ ተገናኝቶ ይጠያየቃል ይመራረቃል ይላሉ። በተጨማሪም በዓሉን ለማክበር አቅም ለሌላቸውን ያላቸው ካላቸው በማካፈል በሥራም በመርዳት ከሁሉም ጋር እኩል በዓሉን ተደስተው እንዲያከብሩ በማድረግ የመረዳዳትና የሥራ ባህልን ለማጠናከር ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ያስረዳሉ።

የ2017 ዓ.ም "ያሆዴ" የሀዲያ ዘመን መለወጫ በዓል በሀዲይ ነፈራ በርካታ የብሔሩ ተወላጆች በተገኙበት በትናትናው ዕለት በተለያዩ ዝግጅቶች ተከብሯል፡፡

# መስቀል በጉራጌ

**ነፃነት አስሙ**

**ዜና ሐተታ**

መስቀል ደርሷል፤ ብርድና ፀሐዩን ተቋቁሞ ጀብሎ ሠርቶ ጥቂት ጥሪት የያዘውም በአስመጪና ላኪነት ሚሊዮኖችን ያካበተውም በየፊናቸው በዓሉን ከቤተሰብና ጎረቤት ጋር ለማክበር ጉድ ጉድ የሚሉበት ወቅት ነው።

ሴቶች የበዓል ምግብ ማጣፈጫ ቅቤና የተለያዩ ቅመሞችን ዝግጅታቸውን አላስታጎሉም። ከተማ ያለውም ብርም ልብስም አሊያም የበዓል ስጦውን ይዞ ለመሄድ ተዘጋጅቷል። ከነዚህ መሃከል ደግሞ ማርታ ተመስገን አንዷ ነች።

በአዲስ አበባ በቤት ሠራተኝነት ተቀጥራ እየሠራች ሕይወቷን ትመራለች። መስቀል ደርሷልና ልቧ ሁሉ በዓሉን እንዴት አከብራለሁ የሚለው ላይ ማተኮሩን አልሸሸገችም። ለበዓሉ በጉራጌ ዞን ወደሚገኘው የትውልድ መንደሯ ለመሄድ ዝግጅት እያደረገች ነው።

በዓሉን ለማክበር የምትሄደው አያቶቿ ቤት ነው፡፡ አባቷ በሕይወት ስለሌሉ እናቷ የእሷን ታናናሾች ይዛ እናት አባቷ ቤት ትመጣለች፡፡ በዚህ ምክንያት ብቻ ሳይሆን በዓሉ በአብሮነት ከመከበሩ ጋር ተያይዞ የአያቶቿ ቤት እዛ ላሉትም ሆነ እንደእሷ ለሥራ ከሄዱበት በዓሉን ለማክበር ለሚመጡ ቤተሰቦች መሰባሰቢያ ነው፡፡

በእርሷ በኩል ለዚሁ በዓል ብላ ባጠራቀመችው ገንዘብ ለመላው ቤተሰብ አልባሳት ከመግዛት ጀምሮ ለማብሰያ የሚሆን ነዳጅ ጋዝ፣ ዘይትና ሌሎችም ለቤተሰቦቿ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ይዛ ለመሄድ መዘጋጀቷን ትገልፃለች፡፡

ቀኑ ደርሶ ከቤተሰቦቿ ጋር ቆንጆ ጊዜ እስካሳልፍ በቂ እንቅልፍም አልተኛ ስትል መጓጓቷን አሳውቃለች። በዓላት ሲመጡ የሚታዩ ችግሮችን ለመቀነስ በተለይ የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች ታሪፉን ባማከለ ሁኔታ ህብረተሰቡን ሊያገለግሉ እንደሚገባ መልዕክቷን አስተላልፋለች።

በጉራጌ ዞን ቸሀ ወረዳ አውቃቅር ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ ውባለም ደጉ በበኩላቸው፤ አሁን ላይ ዝግጅቱ ሁሉ አልቆ ቤት የማስዋብ፣ አካባቢን የማፅዳት ሥራ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ በዓሉ መስከረም 14 ከሚኖረው የሴቶች መስቀል ወይም የጎመን ክትፎ እንደሚጀምር ያስረዳሉ፡፡

የበዓል ክትፎ፣ ቆጮና ማባያ ቅመሞችን ሁሉ የማዘጋጀቱ ኃላፊነት የሴቷ መሆኑን አንስተው፤ ወንዶች እርድ የማከናወንና ባህላዊ ሥርዓቶችን የመምራት ኃላፊነት እንዳለባቸው ይናገራሉ።

ከሕፃን እስከ አዋቂ በጉጉት በሚጠበቀው በዓል ሁሉም ባለው አጊጦና ተደስቶ ለማሳለፍ ዓመት ሙሉ ይዘጋጃል የሚሉት ወይዘሮዋ፤ እርሳቸውም በባህላዊ ልብሳቸው አጊጠው ከጎረቤትና ዘመዶቻቸው ጋር በፍቅር ለማሳለፍ መዘጋጀታቸውን ይገልጻሉ።

በኃይማኖታዊና ባህላዊ ሁነቶችን የሚደምቀው በዓሉ ተራርቆ የነበረ ሰው ከወዳጅ ዘመድና ጎረቤት የሚገናኝበት ነው፤ ህብረተሰቡም ምንም ሳይለየው አብሮነቱና መተጋገዙን ያጠናክርበታል ይላሉ።

የምስራቅ ጉራጌ ዞን ባህል ቱሪዝም መምሪያ ኃላፊ የሆኑት ወይዘሮ ብሩክታዊት ፀጋዬ በበኩላቸው፤ የበዓል ዝግጅቱ ባህላዊ ትውፊቱን በጠበቀ መልኩ መስከረም 11 እና 12 ለማክበር መዘጋጀታቸውን ይገልጻሉ፡፡

የመስቀል በዓል እስከ መስከረም 16 ቀን ድረስ እርድ እስከሚከናወንበት መከበሩ እንዳለ ሆኖ እስከ ጥቅምት አምስት ድረስ ደግሞ በዓሉን ተንተርሰው የሚመጡ የአዳብና ጨዋታ መኖሩን ይጠቁማሉ። አዳብና በልጃገረዶችና በወጣት ወንዶች የሚደረግ ጨዋታ በመሆኑ ዞኑ ሕዝቡ እንደሚያከብረው ያስረዳሉ።

በዓሉን የምናከብረው በዙሪያችን ከሚገኙ በርካታ አጎራባች ማህበረሰቦች ጋር በጋራ በመሆን ነው ያሉት ኃላፊዋ፤ የመስቀል በዓል ቁርኝት የሚፈጥርና ለአንድነታችንም መሠረት የሚጥል መሆኑን ነው ያነሱት።

የጉራጌ ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ኃላፊ ወይዘሮ መሠረት አመርጋ በበኩላቸው፤ በዞኑ በዓሉ "የመስቀል በዓላችን ለቱሪዝም ሀብታችን" በሚል መሪ ሃሳብ ይከበራል ይላሉ።

የመስቀል በዓል ከምግብና ባህላዊ ሥርዓቶቹ ባሻገር በቱሪዝሙ ዘርፍ ትልቅ የኢኮኖሚ ምንጭ አድርጎ ለመጠቀም የሚያስችል ዝግጅት መደረጉን ነው ያመላከቱት።

ከመስከረም 9 እስከ 11 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስ በዞኑ የተዘጋጀ የመስቀል በዓል ፌስቲቫል እንደሚካሄድ አስታውቀው፤ በዓሉ ባህላዊ ይዘቱን በጠበቀና የቱሪስቶችን ቀልብ በሚስብ መልኩ ለማክበር የሚረዳ ገጠራማ ሥፍራ መመረጡን ይጠቁማሉ።

ለሰባተኛ ጊዜ በሚካሄደው ዞናዊ ፌስቲቫል ከጉንችሬ ከተማ 50 ኪሎሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው እኖር ወረዳ በሚገኝ ጋራድ ቀበሌ በተሰኘ ውብ ሥፍራ ላይ ይካሄዳል ብለዋል።

በዓሉ ጀፎረ በተሰኘውና በባህላዊ መንገድ የተዘጋጀ ሰፊ መንገድን በያዘ የጉራጌ ባህላዊ መንደር ውስጥ ይካሄዳል ሲሉ ተናግረዋል። ለፌስቲቫሉ አስፈላጊ የሆኑ የመስተንግዶ፣ አካባቢውን የማስዋብና ሌሎች ዝግጅቶች መጠናቀቃቸውን ነው የገለጹት።

በፌስቲቫሉ የቁንጅና ውድድርና የባህላዊ ዕቃዎች አውደ ርዕይ እንደሚካሄድ አስታውቀው፤ የመስቀል ጎመን ክትፎ ዝግጅትን የሚያካትተው የከብት እርድና የባህላዊ ምግብ ፌስቲቫል፣ የኪነ- ጥበብ ዝግጅቶች እንዲሁም የጥያቄና መልስ ውድድሮች መዘጋጀታቸውንም ያስረዳሉ።

ፌስቲቫሉን ለማክበር ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገራት የተጋበዙ እንግዶች እንደሚሳተፉ ጠቁመው፤ ለሚኒስትር መሥሪያ ቤቶች፣ ለሚዲያ አካላት፣ ለኪነ-ጥበብ ሰዎች፣ ለአስጎብኚ ድርጅቶች፣ በቱሪዝም ላይ ለሚሳተፉ አካላትና ለተለያዩ እንግዶች ጥሪ ተደርጓል ይላሉ።

ማህበረሰቡ በርካታ ታሪክ ያለው በመሆኑ የቱሪዝም መዳረሻዎችንም የማስተዋወቅ ሥራ እንደሚከናወን ይገልጻሉ።

ለመስቀል በዓል የሚመጡ ባለሀብቶችና የዞኑን ተወላጆች በማስተባበር በትምህርት ቤት ግንባታ፣ በመንገድ ሥራ፣ በተለያዩ ተቋማት የልማት ሥራዎች ላይ ለማሳተፍ የሚረዳ ንቅናቄ እየተካሄደ መሆኑን አንስተዋል።

በዞኑ በሚገኙ እያንዳንዱ ወረዳዎች አንድና ከዚያም በላይ የቱሪስት መዳረሻዎችን ማልማት ይገባል የሚል አቅጣጫ ተቀምጦ እየተሠራበት ይገኛል ይላሉ።

ዞኑ እንግዶቹን ለመቀበል ከመቼውም ጊዜ በላይ ዝግጁ መሆኑን ገልጸው፤ የበዓሉ ታዳሚዎች በሰላም አክብረው እንዲመለሱ አገልግሎት ሰጪዎች፣ የፀጥታ አካላትና ሌሎችም የበኩላቸውን እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሕዝባችን የባንዳዎችን ተልዕኮ ማምከን የሚያስችል ሁለንተናዊ አቅም ባለቤት ነው!

የአንድን ሀገር እና ሕዝብ ብሄራዊ ጥቅም በሁለንተናዊ መንገድ ማስከበር ከማንም በላይ የዚያች ሀገር ሕዝቦች ትልቁ ኃላፊነት ነው። ይህንን ኃላፊነት በአግባቡ የመወጣት እና ያለመወጣት ጉዳይ የህልውና ጉዳይ ተደርጎም ይወሰዳል። ከዚህ የተነሳም ከብሔራዊ ጥቅሞች ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ለየትኛውም ሀገር ዜጋ ከዜግነት ጋር የተያያዙ ፤ ወደማንም የማይገፉ አጀንዳዎች ሆነው ለዘመናት ቆይተዋል።

በተለይም የብሔራዊ ጥቅሞች አልፋ እና ኦሜጋ / ዋነኛ ማዕቀፍ ተደርጎ የሚወሰደው የሉዓላዊነት ጉዳይ የየትኛውም ሀገር ዜጋ ፤ በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ የሚደራደርበት ጉዳይ አይደለም። እንደ ሀገርም ሆነ እንደ አንድ ማኅበረሰብ የመቆም እና ጸንቶ የመቀጠል መሠረት በመሆኑ ፤ የየትኛውም ሀገር ዜጋ እና በየትኛውም ዘመን ያለ ትውልድ በጽናት የሚቆምለት ሀገራዊ አጀንዳ ነው።

እኛ ኢትዮጵያውያን ለዚህ እውነታ ባዕድ አይደለንም ፤ ዘመናት ስለሚያስቆጥረው የሀገረመንግሥት ታሪካችን ስናወራም ፤ የምናወራው ሉዓላዊነታችንን ለማስከበር እና አጽንቶ ለትውልዶች ለማስተላለፍ ያደረግናቸው የተጋድሎ ታሪኮች ፤ ስለ ነጻነታችን እና ከዚህ ስለሚመነጨው ሉዓላዊነታችን የከፈልናቸው በድል ያሸበረቁ መስዋዕትነቶች ነው።

በየዘመኑ የነበሩ ትውልዶች ለብሔራዊ ነጻነታችን / ሉዓላዊነታችን ዘመኑ የጠየቀውን መስዋዕትነት ያለ ማቅማማት ፤ ከፍ ባለ የሀገር ፍቅር ስሜት ከፍለዋል ። በዚህም የሀገር ፍቅር ምን ማለት እንደሆነ ለትውልዶች አስተምረዋል ። እንደሀገርም የነጻነት ፋና ወጊ የሆንበትን በጎ ትርክት ፈጥረውልን አልፈዋል።

ይህ የቀደሙት አባቶቻችን ከሀገር ፍቅር የሚመነጭ የነጻነት ተጋድሎ ትርክት ፤ ዘመናትን በነጻነት መሻገር የቻለች ሀገር ባለቤት ከማድረግ ባለፈ ፤ በየዘመኑ ስለሀገሩ ነጻነት ቀናኢ የሆነ ትውልድ በማፍራት ዛሬም በሀገሩ ሉዓላዊነት የማይደራደር ፤ ሁሌም ለሀገሩ ክብር መስዋዕት ለመሆን የተዘጋጀ ትውልድ እንዲኖር አስችሏል።

ታሪካዊ ጠላቶቻችንም ሆኑ በየወቅቱ የሚፈጠሩ በብሔራዊ ጥቅሞቻችን ላይ የሚሰለፉ ኃይሎች፤ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሚፈጥሩብንን ፈተናዎች ተሻግረን ዛሬ ላይ የደረስነውም ሁሌም በሀገር ጉዳይ ለመስዋዕት ዝግጁ በሆነው ትውልድ እና በተጨባጭ በተግባር በተፈተነው የተጋድሎ የአሸናፊነት ትርክት ነው።

ይህም ሆኖ ግን የሀገር ሉዓላዊነት እና ከዚህ የሚመነጨው ብሔራዊ ክብራችን ትርጉም የማይሰጣቸው፤ ብሔራዊ ክብርን ከግል እና ከቡድን ፍላጎት አሳንሰው የሚያዩ ፤ በዚህም ለሀገር እና ለሕዝብ ፈተና የሆኑ ግለሰቦች እና ቡድኖች በየዘመኑ አጋጥመውናል። የጠላቶችንን አጀንዳ ተሸካሚ በመሆንም ብዙ ዋጋ አስከፍለውናል።

እነዚህ በግልጽም ይሁን በስውር ፤ አውቀውትም ይሁን ሳያውቁት የባንዳነት ተልዕኮ ተሸክመው ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ኃይሎች ፤ እንደሀገር የተጀመሩ የለውጥ /የመለወጥ መነቃቃቶች ስኬታማ እንዳይሆኑ አድርገዋል። የሕዝባችን በልማት የመለወጥ መሻት እውን እንዳይሆንም ፈተና ሆነው ቆይተዋል።

የኛ እንደ ሀገር መልማት እና መበልጸግ ለብሔራዊ ጥቅማቸው ፈተና አድርገው የሚወስዱ የታሪካዊ ጠላቶቻችን የአስተሳሰብ ጥላ በመሆን ፤ ሀገር ከአንድ የግጭት ምዕራፍ ወደ ሌላ የግጭት ምእራፍ እንድትጓዝ፤ ዘላቂ ሀገራዊ ሰላም እና መረጋጋት እንዳይኖር አድርገዋል።

እነዚህ ኃይሎች ለጠላቶቻችን ዘመን ተሻጋሪ የጥፋት ተልእኮ መሣሪያ በመሆን ፤ ዛሬም ከሕዝባችን የለውጥ/የመለወጥ መነቃቃት ማግስት ጀምሮ በገዛ ሕዝባቸው የመልማት ፍላጎት ላይ በተቃርኖ ቆመው ባልተለመደ መንገድ ያለእፍረት ብሔራዊ ክብራችንን በሚፈታተን መልኩ በአደባባይ በባንዳነት ተሰልፈዋል።

በብዙ መስዋዕትነት ዛሬ ላይ የደረሰውን የሀገርን ሉዓላዊነት ጨምሮ የሕዝባችንን ብሔራዊ ጥቅም አደጋ ውስጥ የሚከቱ የታሪካዊ ጠላቶቻችንን የጥፋት ተልዕኮ ተሸክመው ፤ ለተግባራዊነቱ ያለ ዕረፍት ሲቃትቱ ፤ በዚህ የባንዳነት ሥራቸው ከማፈር ይልቅ ሲኩራሩ እያየን ነው ።

በሕዝባችን የዘመናት በመልማት የመለወጥ ፍላጎት ላይ ብቻ ሳይሆን በብዙ ፈተናዎች ውስጥ አልፎ እውን ያደረጋቸውን ህልሞችን በማንቋሸሽ እና በማሳነስ ፤ ከድህነት እና ከኋላ ቀርነት አብሮ እንዲቀጥል ፤ ግጭት እና ግጭት ቀስቃሽ ተልዕኮዎችን ከታሪካዊ ጠላቶቻችን ሳይቀር ተቀብለው ለመስፈጸም ባላቸው አቅም ሁሉ እየሠሩ ነው።

እነዚህ በሉዓላዊነታችን እና በብሔራዊ ጥቅሞቻችን ላይ በአደባባይ በተቃርኖ በባንዳነት የቆሙ ግለሰቦች እና ቡድኖች፤ ለሕዝባችን በልማት በልጽጎ የመገኘት አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ፈተና ከመሆን ባለፈ የሚያመጡት ነገር አይኖርም ። ምክንያቱም ትውልዱ እንደቀደሙት አባቶቹ የነዚህን ባንዳዎች ተልዕኮ ለማምከን የሚያስችል የሁለንተናዊ አቅም ባለቤት ነውና!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## ሪፎርም፤ የመንግሥት እና የሕዝባችን ትልቁ መሻት

ግርማ መንግሥቴ

በመሠረቱ ሪፎርም አዲስ ጽንሰ ሃሳብ አይደለም። አይደለም ባደጉት ሀገራት እኛም ጋ ያለማቋረጥ ሃሳቡን በተመለከተ ሃሳቦች ሲሰነዘሩ እንሰማለን። አንድ ነገር ብቻ አንስተን በቀጥታ ወደ ጉዳያችን እንሂድ። ይህ ጉዳይ የብዙዎች ስለሆነ ምላሽ ባንሰጥበትም ለውይይት ያመች ዘንድ ነካክተነው ብናልፍ ባይጠቅምም አይጎዳምና እንንካው።

የሪፎርም ጉዳይ ሲነሳ በፍጥነት ወደ አእምሯችን ጓዳ የሚመጣው ሕዝባዊ አገልግሎት ስለመስጠት፣ የሕዝብ አገልግሎት ተቀባይነት፣ የመንግሥት ሠራተኛ (ሲቪል ሰርቫንት የሚባለው)፣ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ወዘተ ናቸው (ለነገሩ ከማንም በፊት ዘመናዊ ተቋማትን የመሠረትነው እኛ ነበርን)። እነዚህ ሲታሰቡ ደግሞ "ለእነዚህ ጉዳዮች ምን ያህል ትኩረት ተሠጥቷል?" ብሎ መጠየቅ የግድ ይሆናል።

በሀገራችን በቀደሙት ዓመታት፤ ሪፎርም የሚለው ጽንሰ ሃሳብ የዘፈን ግጥም እስኪመስል ድረስ ደጋግመን ሰምተነዋል። እንደውም አንዳንድ ልጆች በግጥም መልክም እስከ ማሾፍ ድረስ የዘለቀ (ልክ እንደ "ልማታዊ ...") ትችቶችን ሲሰነዝሩበት ተሰምቶ ያውቃል። ጥያቄው ተዝወትሮ የመነሳቱን ያህል ለምን ተዝወትሮ ሥራ ላይ አይውልም? ነው።

ሪፎርም በመንግሥት በኩል ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራ ይገኛል የሚለው ሁላችንም ሊያስማማ ይችል ይሆናል። ነገር ግን፣ መንግሥትና የመንግሥት ተቋማት ምን እና ምን ሆነው ነው ሪፎርሙ ወደ መሬት መውረድ ያልቻለው? የሚለው ጥያቄ ግን አግባብ ባለው መልኩ ጊዜ ወስደን ቆም ብለን ልናስበው የሚገባ ነው።

**ሪፎርም በመንግሥት በኩል ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራ ይገኛል የሚለው ሁላችንም ሊያስማማ ይችል ይሆናል። ነገር ግን፣ መንግሥትና የመንግሥት ተቋማት ምን እና ምን ሆነው ነው ሪፎርሙ ወደ መሬት መውረድ ያልቻለው? የሚለው ጥያቄ ግን አግባብ ባለው መልኩ ጊዜ ወስደን ቆም ብለን ልናስበው የሚገባ ነው**

የመጀመሪያው ጥያቄ ሊሆን የሚገባው፤ እውነት መንግሥት ራሱ ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቷል ወይ? የሚለው ነው፤ በለውጥ ላይ ያለ መንግሥት ለለውጡ ስኬት ትልቁ አቅም የለውጡን አስተሳሰብ የተሸከሙ የሪፎርም ሥራዎችን መሥራት ከመሆኑ አንጻር ብዙም ለጥያቄ የሚቀርብ አይሆንም። ለጽሑፌ ማጣቀሻ ይሆነኝ ዘንድ፤ አንድ የመንግሥትን የባለፈው ዓመት መረጃ በመጥቀስ "አዎ ሰጥቷል" የሚለውን እንውሰድ።

መረጃውም ፤በ2014 በጀት ዓመት 11 ወራት ለ2,949,293 ዜጎች ቋሚ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ2,137,932 ዜጎች (72%) ቋሚ የሥራ ዕድል መፍጠር የተቻለ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ 43 በመቶው በአገልግሎት የሥራ ዘርፍ ነው።

እንደ አጠቃላይ እንየው ካልንም፣ የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ሰኔ 2014 ዓ.ም ለፓርላማ ባቀረበው ሪፖርት እንደገለፀው፣ በመላ ኢትዮጵያ ወደ ሁለት ሚሊዮን የመንግሥት ሠራተኞች ይገኛሉ። እንደ ሀገር፣ ሪፎርሙ እነዚህን ሁሉ ይመለከታል (እዚህች ላይ "ተቋማት የሰዎች አስተሳሰብ ውጤት ናቸው።" የሚለውን የሪፎርሚስቶች ሃሳብ ማስገባት ያስፈልጋል)።

መሬት ላይ ያለው (ዝቅ ብለን የምናየው ሆኖ) 12ቱ መርሆችን (ቅንነት፣ ታማኝነት፣ አገልጋይነት ወዘተ) በሚል በየመሥሪያ ቤቱ ግድግዳ ላይ የተለጠፉ መርሆዎችን ለጊዜው እንተወው እና ፤"43 በመቶ በአገልግሎት ዘርፍ" የሚለውን ስንመለከት ከላይ "አዎ ሰጥቷል" ያልነውን እንድንደግም ያደርገናል።

ጥልቁ ጉዳይ ግን መሬት ላይ ያለውን የአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ያለው ተጨባጭ እውነታ ነው፣ በአብዛኛው የአገልግሎት ዘርፍ "ለዜጎች እየተሰጠ ያለው አገልግሎት ምን ይመስላል?" ብለን እንጠይቅ ካልን "ሪፎርም አድርገናል" የሚሉ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሳይቀር ብዙ ጥያቄ የሚነሳባቸው ናቸው ።

በተደጋጋሚ ሲነገር እንደሚሰማው ሪፎርም (ለውጥም እንበለው ማሻሻያ) የነበሩና የተለዩ ጉድለቶችን በማረም እና ያሉትን ጥንካሬዎች ደግሞ በማስቀጠልና በማጎልበት ላይ ያተኮረ ሥራን መሥራት፤ እንዲሁም፣ ዜጎችን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ መሠረታዊ ማሻሻያዎችን ማድረግ መሆኑ፤ ከነበሩ ችግሮች በፍጥነት በመላቀቅ ሕዝቡን ተጠቃሚ ማድረግ የሚቻልበት አሠራር መተግበር ነው።

ያልተቋረጠ ሀገራዊ ልማትን ለማረጋገጥ፣ ሀገራዊ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ፣ የተቋማትንና ሠራተኞችን አቅም በማጎልበት የሕብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማሳደግ፤ በዚህም የአገልግሎት ተቀባዩን ማህበረሰብ እርካታ ለመጨመር ወዘተ ሪፎርም እጅጉን አስፈላጊ መሆኑ ያለ ማቋረጥ ተነግሯል። ወሳኝ የሆነውን፣ የግብርናውን ዘርፍ እንኳን ብንመለከት የሚከተለውን የሥራና ክሂሎት ሚኒስቴርን ሪፖርት እናገኛለን።

የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የቅርብ ጊዜ ሪፖርት "ሀገራዊ የልማት ዕቅዱ የተሳካ እንዲሆንና ኢኮኖሚያዊ ነፃነታችንን መቀዳጀት እንድንችል ግብርናችንን ማዘመንና የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማሳደግ ወሳኝ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ተጠሪ የሆኑ የግብርና ተቋማትን በበቂ ጥናት ላይ በመመስረት የሪፎርም ሥራ ተጀምሯል። እዚህም ላይ የሚነሳው መቼ ነው ከ "ተጀምሯል" ይልቅ "ተጠናቋል"ን የምንሰማው?" የሚለው ነው።

በመጨረሻም፣ ከላይ የጠቀስነው የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ሪፖርት በቀረበበት መድረክ ላይ "በመንግሥት ተቋማት አሁን ላይ ውጤት ተኮር ትግበራ እንደሚባለው ሁሉ የአቅም ግንባታ፣ የክሂሎት ምዘና፣ ካይዘን፣ ወዘተ እየተባለ በሰው ኃይልም ሆነ በንብረት አያያዝና በአደረጃጀት በኩል የአሠራር ማሻሻያ ተደረገ መባሉ የተለመደ ሪፖርት ነው። ይሁን እንጂ ይህ ሁሉ የአሠራር ሥርዓት ማሻሻያ በተገልጋዮች ዕርካታ ቢመዘን "ምን ምን ውጤት አስገኘ?" የሚለው ተገቢውን ምላሽ የሚፈልግ ነው።

ይህ ደግሞ አጠቃላይ ሀገሪቱ ካለባት የተቋማት ግንባታ ሕመም ጋር የተያያዘ "እንደ ሆነ ተነግሯል። የሪፎርም ህመም አለ ማለት ነው፤ የሪፎርም ህመም ካለ ደግሞ ተያያዥ ከሆኑት መካከል አንዱ የሆነው የመልካም አስተዳደር ችግር አለ ማለት ነው። የመልካም አስተዳደር ህመም ካለ ደሞ ሁሉም የለም ማለት ነውና አደጋ ላይ ስለመሆናችን ጠንቋይ መጠየቅ አያስፈልግም።

በዚህ አዲሰ ዓመት (2017 ዓ⁘ም) መግቢያ ላይ ስለሪፎርም ዙሪያ ያለን ግንዛቤም ሆነ፤ የሪፎርም ሥራዎች ለጀመርነው ለውጥ ሁለንተናዊ ስኬት ከሚኖራቸው የማይተካ አስተዋጽኦ ጋር በተያያዘ ጉዳዩን ከተለመደው እይታ አውጥተን በአግባቡ ልናጤነው የገባል።

በተለይም ለመንግሥት የለውጥ መንገድ ተገማች ፈተና የሆነውን፣ የአገልግሎት ፈላጊዎችን እርካታ እንዴት በአጭር ጊዜ፣ ዘላቂነት ባለው መንገድ በሕግ፣ በአሠራር ሥርዓት፣ በቴክኖሎጂ እና በተለወጠ ማንነት ታግዘን ከፍ ማድረግ እንዳለብን በብዙ አስበን በጠንካራ ዲሲፕሊን እየተመራን መንቀሳቀስ ይኖርብናል።

ለዚህም ደግሞ መላው ሕዝብ ከሁሉም በላይ የሚመለከታቸው ሁሉ በአዲሱ ዓመት፣ በአዲስ መነቃቃት እና ሀገራዊና የዜግነት ሃላፊነት መሥራት ይጠበቅባቸዋል። ይህን ማድረግ ስንችል ነው የመንግሥት እና የሕዝባችን ትልቁ መሻት የሆነውን ሪፎርም እውን ማድረግ የምችለው ።

# የጊፋታ በዓል ዜጎች ለሀገር አንድነትና ዕድገት ተባብረው እንዲሠሩ ጉልህ አስተዋጽኦ ያበረክታል

ማህሌት ብዙነህ



አዲስ አበባ፡- ጊፋታ በዓል ዜጎች ለሀገር አንድነትና ዕድገት ተባብረው እንዲሠሩ ጉልህ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት የወላይታ ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ አስታወቀ፡፡

የወላይታ ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ኃላፊ አቶ ምህረቱ ሳሙኤል ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ የብዙ ብሔር ብሔረሰቦች ሀገር እንደመሆኑዋ መጠን ጊፋታን እና መሰል በዓላትን በጋራ ተሰባስቦ ማክበር ዜጎች ለሀገር አንድነትና ዕድገት ተባብረው እንዲሠሩ ጉልህ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ፡፡

ይህም በህብረ ብሔራዊነት ውስጥ ያሉ አንድነቶችን በማጠናከር የባህል ቅብብሎሽ እንዲዳብር እና ሕዝቦች በጋራ ተዋደውና ተከባብረው ለሀገር አንድነትና ዕድገት ተባብረው እንዲሠሩ ከፍተኛ ሚና አለው ብለዋል፡፡

የጊፋታ በዓል የወላይታ ሕዝብ ጥንት በአንድ ቦታ ሰፍሮ መኖር ከጀመረበት ጊዜ እንስቶ የፀሐይና የጨረቃ ኡደትን ተከትሎ በሚያደርገው የዘመን አቆጣጠር አሮጌውን ዓመት ሸኝቶ አዲሱን ዓመት የሚቀበልበት የዘመን መለወጫ በዓል መሆኑን አንስተዋል፡፡

ለበዓሉ የሶዶ ከተማን ከማስዋብ ጀምሮ የጊፋታ ሩጫና የኤግዚቢሺን ዝግጅቶች የተከናወኑበት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በዓሉ በዛሬው ዕለት ''የጊፋታ ዕሴቶች ለሁንተናዊ ብልጽግና'' በሚል መሪ ቃል በሩጫ ውድድር፣ በቋንቋና የባህል ሲምፖዚየም፣ በባህላዊ ሙዚቃ ዝግጅትና የባህል ትርኢቶች በሚቀርቡበት ሁኔታ እንደሚከበር ገለጸው፤ በተመሳሳይ ጥናታዊ ጽሑፎች እንደሚቀርቡ አስረድተዋል፡፡ እንዲሁም ታዋቂው የወላይታ ቁርጥን ጨምሮ የተለያዩ ባህላዊ የምግብ ዓይነቶች ለበዓሉ ድምቀት ይቀርባሉ ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በበዓሉ ላይ የተዘጋጁ ምግቦችና መጠጦች ከተመገቡ እና ከተጠጡ በኋላ የአካባቢው ነዋሪዎች በጋራ በመሰባሰብ በአካባቢው በአንድ ታዋቂ ሰው ደጃፍ ላይ ከወራት በፊት ያቆሙትን ጉሊያ የበዓሉ ዕለት (ሹሆ ዎጋ) አመሻሽ ላይ ካቀጣጠሉ በኋላ በጋዚያ ጨዋታ ይዝናናሉ፡፡

እንዲሁም በዓሉን ሕዝቡ በጋራ በአንድ ላይ ተሰባስቦ እንዲያከብር በማሰብ በወላይታ ሶዶ ስቴዲየም የሙዚቃ እና የመዝናኛ ዝግጅቶች የሚቀርቡ ሲሆን የጉሊያ ዝግጅትም በዚያው ሥፍራ የሚከናወን ይሆናል፡፡

የጊፋታ በዓል በውስጡ ለማህበረሰቡ በርካታ ጠቀሜታ ያላቸውን ዕሴቶች የያዘ መሆኑን አቶ ምህረቱ አንስተው፤ በዓሉ መከበሩ እነዚ ዕሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ እንዲጎለብቱ እና ይዘታቸውን ሳይለቁ ለቀጣይ ትውልድ እንዲተላለፉ ጉልህ ሚና ይጫወታል ብለዋል።

በበዓሉ ለመታደም ከተለያዩ አካባቢዎች ወደ ወላይታ የሚመጡ ግለሰቦች በዓሉን ከማክበር የቱሪስት መዳረሻዎችን እንዲጎበኙ በማድረግ የማስተዋወቅ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

የጊፋታ ዕሴቶች የህብረ-ብሔራዊነት ዋነኛ መገለጫ እንደመሆናቸው መጠን በመላው ዓለም ያሉ ዜጎች አንድ ላይ ማክበራቸው፣ በአንድ ማዕድ መጋራታቸው የባህል ቅብብሎሹ እየዳበረ እና እየጎለበተ እንዲዘልቅ የሚያችል ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

# ፈውስ ያገኙ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ትገልጻለች፡፡

ወደ እስራኤል ሀገር ሄዳ የቀዶ ጥገናውን ከማግኘቷ በፊት በሀገር ውስጥ የተለያዩ መድሃኒቶችን ስትወስድ መቆየቷን የምትናገረው አክሊለ፤ ስትወለድ ጀምሮ የነበረው የልብ ክፍተት ችግር ክብደት አለመጨመር፣ ምግብ ፍላጎት መቀነስ፣ እንዲሁም ቶሎ ቶሎ ለሳንባና ለሌሎች ኢንፌክሽኖች ያጋልጣት እንደነበር ታነሳለች።

አክሊለ በወቅቱ በኢትዮጵያ የልብ ቀዶ ህክምና ሃኪም አለመኖሩን ገልጻ፤ ነገር ግን የልብ ካርዲዎሎጂስቶች ባደረጉልኝ ህክምና የልብ ችግሩ እንዳብኝና ከሀገር ውጭ ወጥቼ ቀዶ ህክምናውን ማድረግ እንዳብኝ አሳውቀውኛል ትላለች፡፡

ከዛም በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል አማካኝነት እስራኤል ካለው ዓለም አቀፍ ግብረ ሰናይ ድርጅት ሴቭ ዘ ቺልድረን ጋር መገናኘት በመቻሏ በእስራኤል ሀገር የልብ ቀዶ ህምናውን ማድረጓን ታስታውሳለች፡፡

አሁን ላይ አክሊለ በተደረገላት ህክምና ድጋፍ ሙሉ በሙሉ ጤነኛ መሆኗንና ነርሲንግ ትምህርት ተምራ በአሁኑ ጊዜ በልብ ቀዶ ህክምና ወቅት ልብና ሳንባን ተክቶ የሚሠራ ማሽን ላይ ለመሥራት የውጭ የትምህርት እድል አግኝታ ለመሄድ ዝግጅት ላይ መሆኗን ተናግራለች፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ ወላጆች በዚህ ህመም ምክንያት ከልጆቻቸው ጋር እየተቸገሩ መሆናቸውን የምትገልጸው አክሊለ፤ በኢትዮጵያ ልብ ህሙማ ህጻናት መርጃ ማዕከል ብቻ ከስምንት ሺህ በላይ ህጻናት ወረፋ እየጠበቁ እንደሚገኙ ትጠቁማለች፡፡

እኔ ያገኘሁትን አይነት እድል ሁሉም ህጻናት እንዲያገኙም ምኞቴ ነው ያለችው አክሊለ፤ የእስራኤል መንግሥት በጤናው ዘርፍ የሚያደርገው ድጋፍ የህክምና አገልግሎት ብቻ ሳይሆን የጤና ባለሙያዎችን ማሰልጠንም ጭምር የሚያካትት መሆኑን ገልጻለች። ይህም በቀጣይ ልብ ቀዶ ህክምናዎች በሀገር ውስጥ እንዲሠሩ የሚረዳ ነው ትላለች፡፡

ልዑልሰገድ ደሳለኝ ፤ የልብ ችግር እንዳለበት ያወቀው በ13 ዓመቱ ነው፡፡ ችግሩ እንዳለበት እንዳወቀም በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ክትትል ያደርግ እንደነበርና ሆስፒታሉ ከሴቭ ዘ ቺልድረን ግብረሰናይ ድርጅት ጋር ባለው ግንኙነት የዛሬ 14 ዓመት በፊት በ14 ዓመቱ እስራኤል ሀገር ሄዶ መታከሙን ያስታውሳል፡፡

በወቅቱ የነበረው የልብ ችግር ቫልቭ መሆኑን የሚናገረው ልዑልሰገድ፤ ህክምናው ተደርጎለት ከተመለሰ በኋላ ጤነኛ መሆኑን ይናገራል። ከህክምናው በኋላም ቅርጫት ኳስ ሲጫወት እንደቆየና በኋላ ማሠልጠን መጀመሩን ይናገራል፡፡

በሂደት ግን እንደገና የልብ መድከም ችግር እንዳጋጠመው የሚያስታውሰው ልዑልሰገድ፤ ድርጅቱም የዛሬ ሶስት ዓመት በድጋሚ ወደ እስራኤል ሀገር ወስዶ አሳክሞኛል ይላል፡፡

ልዑልሰገድ፤ ለህክምና እስራኤል በሄድኩበት ወቅት የሚደረግልኝ እንክብካቤ የሚያስደስት ነው። እንደኔ አይነት የልብ ችግር ካላቸው ህጻናት ጋርም ተገናኝቼ ሃሳባችንን እንድጋራ ተደርጓል፡፡ አሁን ላይም በሙሉ ጤንነት በሂልተን ሆቴል እየሠራ እንደሚገኝ ተናግሯል፡፡

ሴቭ ዘ ቺልድረን ግብረ ሰናይ ድርጅት መቀመጫውን በእስራኤል ያደረገ ተቋም ነው፡፡ ድርጅቱ በተለያዩ 70 የዓለም ሀገራት በልብ ህመም ሲሰቃዩ የቆዩ ከሰባት ሺህ በላይ ህጻናት ሕይወትን ታድጓል፡፡ ከሰሞኑም በእስራኤል መንግሥት አማካኝነት በአራት የህክምና ዘርፎች የህክምና አገልግሎት ለመስጠት ወደ ኢትዮጵያ ከገቡት ግብረ ሰናይ ድርጅቶች አንዱ ነው፡፡

በኢትዮጵያ የሴቭ ዘ ቺልድረን ተወካይ ሪኪ ሮዘንቤል እንደገለጹችው፤ ግብረሰናይ ድርጅቱ ከጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት ለ200 ከፍተኛ የልብ ችግር ላለባቸው ህጻናት ህክምና ለመስጠት ማቀዱን ገልጸዋል፡፡

የህክምና ልዑክ ቡድኑ ሥራውን መጀመሩን የገለጹት ሪኪ፤ ከፍተኛ የልብ ችግር ያለባቸው ህጻናትን ለይቶ ህክምና ካደረገ በኋላ ብዙዎቹን ወደ እስራኤል ሀገር ወስዶ ለማከም እቅድ እንዳለው ነው የተናገሩት፡፡

# የህትመት ሚዲያ ተግዳሮቶችን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ለመሆኑ የህትመት ዘርፉ ለማህበረሰባዊ፣ ለኢኮኖሚና ፖለቲካዊ እድገት ያለው አስተዋጽኦ ምንድነው? ዘርፉ ያሉበት ችግሮች ምንድናቸው? ያሉትን ችግሮችን ለመሻገር መሠራት ያለባቸው ተግባራትስ ምንድናቸው? የሚሉ ጉዳዮች ላይ የዘርፉ ምሁራን ለኢፕድ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

በጅማ ዩኒቨርሲቲ የሚዲያና ኮሙኒኬሽን መምህርና ተመራማሪ ጌታቸው ጥላሁን (ዶ/ር)፤ የህትመት ሚዲያ ሃሳብን ፣ባህልን፣ ፍልስፍናን፣ እውቀትን፣ ይዘትን በዋናነትም መረጃን ለረዥም ጊዜ በመሰነድ በጽሁፍ የሚያቀርብ ነው ይላሉ፡፡

በሁለተናዊ እድገት ውስጥ የህትመት ዘርፉ ያለው ሚና ቀላል የሚባል አይደለም የሚሉት ጌታቸው ጥላሁን (ዶ/ር)፤ ማህበረሰቡ እውቀቱንና ባህሉን እንዲሁም ማንነቱን እርስ በእርስ የሚጋራበትና የሚያስተላልፍበት መሆኑን ይገልጻሉ።

አንድ ማህበረሰብ የንባብ ባህል ሲኖረውና ያነበበውንም ሲወያይበት አጠቃላይ የሆነ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም የባህል እድገትን ሊያመጣ እንደሚችል ይናገራሉ።

ጌታቸው (ዶ/ር)፤ የህትመት ዘርፉ ያሉ ችግሮች በርካታ ናቸው፤ በዋናነት የዲጂታል ሚዲያው እየተበራከተ መምጣት የሚጠቀስ ነው፡፡

የዲጂታል ሚዲያው በአጭር ጊዜ ብዙ መረጃ በተለያዩ አማራጮች ማግኘት የሚቻልበት በመሆኑ የሰዎች ምርጫ መሆን ችሏል፡፡ ይህም የህትመት ዘርፉን በእጅጉ ጎድቶታል ይላሉ፡፡

የህትመት ሚዲያው በተፈጥሮው ጊዜን፣ አስተውሎትን እንዲሁም ጥሞና ይፈልጋል የዲጂታል ሚዲያው ግን በተቃራኒው ነው ሲሉ የሚናገሩት መምህሩ፤ በሀገራችን ብቻ ሳይሆን በዓለም ላይ በዲጂታል ሚዲያው ተጽዕኖ ምክንያት ጋዜጦችንም ሆነ ሌሎች የህትመት ውጤቶችን የማንበብ ልምዱ በእጅጉ መቀነሱን ያነሳሉ፡፡

በሌላ በኩል ከህትመት ግብዓቶች የዋጋ መናር፣ የማንበብ ባህል መቀነስ፣ የህትመት ዘርፉን የሚያበረታታ ፖሊሲ አለመኖር ፣ ሃሳብን በነጻነት ያለመጻፍ፣ ለሁሉም እድሜ ክልል የሚሆኑ ህትመቶች አለመኖር የህትመት ዘርፉ እየደከመ እንዲመጣ ምክንያት የሆኑ ሌሎች ጉዳዮች መሆናቸውን ይጠቁማሉ፡፡

የህትመት ዘርፉ ወደቀደሞ ቦታው እንዲመለስና እንዲያድግ ለማድረግ በዋናነት የማንበብ ባህልን ማሳደግ አስፈላጊ መሆኑን የሚገልጹት ጌታቸው ጥላሁን (ዶ/ር)፤ ለሁሉም የእድሜ ክልል ተነባቢ የሆኑ ጽሁፎችን ለአንባቢው ማበርከትም ሌላኛው የቤት ሥራ መሆን አለበት ይላሉ፡፡ በመንግሥት በኩልም የህትመት ዘርፉን የሚያበረታታ ፖሊሲ መንደፍ እንሚያስፈልግ ይናገራሉ።

ህትመት ሚዲያው ከየትኛውም ሚዲያ ቀድሞ የተፈጠረ መሆኑን የሚያነሱት ደግሞ በወልዲያ ዩኒቨርሲቲ ጋዜጠኝነትና ተግባቦት መምህርና የዩኒቨርሲቲው የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር ብርሃን ደጀን ናቸው፡፡

የህትመት ሚዲያ የተዋጀው ህብረተሰብን ለማንቃት፣ መረጃን ለማሳወቅና የሚዲያ ምንነትን ለመግለጽ ነው የሚሉት አቶ ደጀን፤ በዓለም ላይ የእንግሊዝና የፈረንሳይ አብዮት ሲቀሰቀስ፣ አሜሪካ ነጻነቷን ስታውጅ፣ ሀገራችንም ሃይለሥላሴን ጨምሮ ሌሎች መሪዎችን ስታስተናግድ የህትመት ሚዲያው ያበረከተው ሚና ቀላል አልነበረም ይላሉ፡፡

ከጊዜ ወደ ጊዜ የህትመት ሚዲያው እየተቀዛቀዘ መምጣቱንና በተለይም መጽሄቶች የድሮ ዝናቸውና ተነባቢነታቸው እየቀነሰ መምጣቱን የሚያነሱት መምህሩ፤ ለዚህም ዋነኛ ምክንያት የሚሆነው ከዲጂታል ሚዲያው መረጃን በቀላሉ ማግኘት መቻሉ መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡

አሁን ላይ የህትመት ሚዲያው በሌሎች አማራጮች የገበያው እየወጣ ይገኛል፡፡ ይህም የዲጂታላይዜሽ ጋር የተገናኘ በመሆኑ ሲሆን በሚዲያው ዘርፍ ብቻ ሳይሆን በሁሉም ዘርፍ የኤሌክትሮኒክስ አማራጮች በሰዎች ተመራጭ እየሆነ መጥቷል ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

የህትመት ሚዲያው አሁን ካለበት ችግር ሙሉ በሙሉ መውጣት አይችልም የሚሉት መምህሩ፤ ሆኖም አሁን ያለውን አቅም ይዞ እንዲቀጥል ዘርፉ እራሱን በማዘመን ወይም ኮንቨርጅድ የሚዲያ ሥርዓትን በመጠቀም አማራጮችን ማስፋት ይኖርበታል፡፡ ነገር ግን ህትመቱ ለሕጋዊ አማራጮችና ለሰነድ (ለአርካኢቭነት) እንዲውል መደረግም ያስፈልጋል ይላሉ።

ሚዲያው እንዲቀጥልና ማንበብ ክህሎት እንዲጨምር በዘርፉ ያሉ ጫናዎችን በመረዳት የህትመት ወጪዎችን በተለይም ከውጭ የሚገቡ ወረቀቶችን ከታክስ ነጻ የማድረጉ ሥራ የመንግሥት መሆን እንዳለበት ይናገራሉ፡፡

በሌላ በኩል መንግሥት የማስታወቂያ ሥራዎች ለህትመት ሚዲያው ቅድሚያ እንዲሰጥ እድል ሊፈጥር እንደሚገባ ገልጸው፤ ይህም የህትመት ሚዲያው በኢንዱስትሪው ላይ እንዲቆይ እንደሚረዳው ይናገራሉ፡፡

የመገናኛ ብዙሃን ፈር ቀዳጅ የሆነው የህትመት ሚዲያ በአንድ ሀገር ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ውስጥ ጉልህ ሚና ይጫወታል። በተለይም በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ከፍተኛ ሚና አለው። በተለይ ለሕዝብ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ በማቅረብ፣ በማሳወቅ፣ በማስተማርና በማዝናናት የሚዲያ ሚናውን ይጫወታል። እንዲሁም የዜጎችን ሃሳብን የመግለጽ ሕገ መንግሥታዊ መብት ተግባራዊ በማድረግ እና የተለያዩ አመለካከቶችንና አስተያየቶችን በማስተናገድ ለዴሞክራሲ ሥርዓት መዳበር ከፍተኛ ድርሻ ያበርክታል።

ይህ ፈር ቀዳጁን ሚዲያ ሚናውን እንዲጫወት ተግዳሮቶችን ፈትቶ ወደ ተሻለ ደረጃ እንዲሸጋገር ሁሉም የበኩሉን ሚና ሊወጣ ይገባል፡፡

ከሕትመት ዋጋ መናርና ከድጅታል ሚዲያው መምጣት ጋር ተያይዞ አጣብቂኝ ውስጥ የሚገኘውን የኢትዮጵያ የሕትመት ሚዲያ ኢንዱስትሪ ለመታደግ ሁለተናዊ ጥረት ማድረግ እንደሚገባም ምሁራት ይመክራሉ፡፡

# የዘንድሮ ኢሬቻ በዓል መስከረም

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ወጣቶች የስምሪት አቅጣጫ መስጠት እንዲሁም ከአባ ገዳዎች ጋር በመሆን ስለ ኢሬቻ በዓል ምንነትና እሴት ግንዛቤ መስጠት ይገኙበታል ብለዋል።

ከአባ ገዳዎች፣ ከሀደ ስንቄዎች፣ ከመንግሥት እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በዓሉ በሰላም፣ በፍቅር እና በደስታ እንዲከበር ለማድረግ ውይይት መከናወኑን ጠቁመው፤ በዓሉን ሌሎች ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ከኦሮሞ ሕዝብ ጋር በመሆን እንዲያከብሩ ጥሪ አቅርበዋል።

ከዚህም ባለፈ ከኢትዮጵያ ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን በዓሉን እንዲያከብሩ ጥሪ የተደረገ መሆኑን የገለጹት አባገዳ ወርቅነህ፤ ከቢሾፍቱና ከፊንፊኔ ከሚከበረው በተጨማሪ በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች እንደሚከናወን ተናግረዋል።

ቄሮዎች፣ ቀሬዎችና ፎሌዎች የበዓሉ ባለቤት መሆናቸውን በመግለፅ፤ ኢሬቻ ባህላዊ እሴቱን ጠብቆ እንዲከበር ማስቻል እንደሚገባ አስገንዝበዋል። ሆረ ፊንፊኔና ሆራ ሀርሰዴ ጨምሮ በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች በሚከናወነው የኢሬቻ በአል ከ12 ሚሊዮን በላይ ሰዎች በዓሉን ይታደማሉ ተብሎ እንደሚጠበቅም ገልጸዋል።

ሀደስንቄ ቱለማ ዘውዲቱ በበኩላቸው፤ የኢሬቻ በዓል የሰላም በዓል በመሆኑ የኦሮሞን ባህልና ሥርዓት በተከተለ መልኩ መከበር እንዳለበት ገልጸው ፤በዓሉ ባህልና እሴትን ተከትሎ እንዲከበር ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ ይገባል ብለዋል።

የዘንድሮው ኢሬቻ በዓል የገዳ ሥርዓት እሴቱን በጠበቀ መልኩ ለማክበር ዝግጅት እየተከናወነ መሆኑን የገለጹት ሀደስንቄ ቱለማ፤ በዓሉ ያለምንም እንከን እንዲከበር ሁሉም በጋራ መቆም አለበት። በተለይም ወጣቱ ሚናውን በአግባቡ መወጣት እንዳለበት ተናግረዋል።

ከዚህም ውስጥ አንዱ በዓሉ የሚከበርበትን ቦታ የመጎብኘትና ጽዱ የማድረግ ሥራዎችን ተጠቃሽ መሆኑን ነው የተናገሩት ሀደስንቄ ቱለማ ዘውዲቱ።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# የግብጽ የጂኦፖለቲካ ከበባ

የታላቁ የሕዳሴ ግድብ በመጠናቀቅ ላይ መሆኑ ግብጽን የቆሰለ አውሬ አድርጓታል። ክፉኛ አስቆጥቷታል። ደሟን እያዘራች ኢትዮጵያን ለመንከስ አክለፍልፏታል። በዚህ አውሬያዊ ስሜት ውስጥ ሆና እየዛከረች እያለ ነው ሶማሊያ አጋር ሆና የተከሰተችው። ኢትዮጵያ ከስምንት ወራት በፊት ከሶማሌላንድ ጋር ለባሕር ኃይል የጦር ሰፈርና የባሕር በር ለማግኘት መስማማቷ ስልጣን ላይ ላለው የሶማሊያ መንግሥት ያልታሰበ አጀንዳ ፈጥሮለታል። ፕሬዚዳንት ሀሰን ሼክ ሞሐመድ ይህን አጋጣሚ በጎሳ መሪዎች ተከፋፍሎ የሚገኘውን ሕዝብ ለፀረ አልሻባብ ትግል አንድ ለማድረግና አጀንዳ ለማስቀየር ሌት ተቀን እየተጠቀሙበት ነው።

ግብጽፅም የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ግንባታና ውሃ ሙሊት ጫፍ ላይ መድረሱ በሀገሪቱ ልሒቃንና በሕዝቡ ዘንድ የሰላ ትችት እያስነዘረና የፕሬዚዳንት አልሲሲ አገዛዝም ብሔራዊ ጥቅምን አሳልፎ ሰጠ እየተባለ እየተከሰሰ ባለበት ነው የፕሬዚዳንት ሀሰን አገዛዝ ወደ ጂኦፖለቲካዊ ቀለበታቸው ዘው ብሎ የገባው። አልሲሲም ጊዜ አላጠፉም። ወዲያው ለሶማሊያ የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት አጋር መሆናቸውን ከመግለጽ አልፈው ከሀገሪቱ ጋር የደህንነት ስምምነት ተፈራረሙ።

ሶማሊያ የአረብ ሊግ አባል ስለሆነች ሀገራቸውን ጨምሮ ሊጉ ከጎኗ መሆኗን ገለጹ። በዚያ ሰሞን ደግሞ የጦር መሳሪያና ወታደሮቻቸውን ወደ ሞቃዲሾ ላኩ። ፕሬዚዳንት አልሲሲ ይህን እያደረጉ ያሉት የሶማሊያ ሉዓላዊነት ገዷቸው ሳይሆን ኢትዮጵያን በጂኦፖለቲካ ከበባ ውስጥ ለማስገባት ነው። ከዚያ ለማህበራዊ መሰረታቸውንና ለግብፃውያን መደለያነት ይጠቀሙበታል።ይህ የግብፅ ጂኦፖለቲካዊ ደባ ዛሬ የተጀመረ አይደለም። ጥንታዊና ከዘመነ ኦሪት ጀምሮ የነበረ መርገም እንጂ።

ግብፅ ዓባይን ከምንጩ ለመቆጣጠር፣ ሀገራችንን ቅኝ ለመግዛት እና ጠንካራ ሉዓላዊ ሀገር ሆና እንዳትወጣና ይህ ቀን (ዓባይ የሚገደብበት ቀን) እውን እንዳይሆን ከ11 ጊዜ በላይ ወራናለች፡፡ በስውር ደግሞ ምን አልባት ለሺህ ዓመታት አሲራለች፡፡ በተለይ ከ20ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ ደግሞ በእነ ሶማሊያ ፣ ሱዳን ፣ ጀብሀ ፣ ሸዓቢያ ፣ ትህነግ ፣ ኦነግና የኦጋዴን ነጻ አውጪን በመጠቀም የውክልና (proxy) ጦርነት በማካሄድ ሀገራችንን ስታዳክም ኖራለች፡፡ ሀገርና የባሕር በር አሳጥታናለች። የማንነት ፖለቲካ እንዲሰለጥንብን አድርጋለች።

ውስጣዊ አንድነታችን እንዲፍረከረክ አርጋለች። የእኛ ለዚህ ደባ መመቻቸት ሳይካድ።ይህ እኩይ አላማዋ ከሞላ ጎደል በመሳካቱ የቤት ስራዋን በማጠናቀቋ ዝቅ አርጋ ስታየን ኖራለች፡፡ ከታሪካዊዋ ሐምሌ 15 ቀን 2012 ዓ.ም ወዲህ ማለትም የታላቁ ህዳሴ ግድብ የመጀመሪያ ውሃ ሙሊት መጠናቀቅ ግን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሁኔታዎችን ቀያይሯል፡፡ በሴራና በደባ በቀጣናውም ሆነ በዓለም አቀፍ መድረክ ያሳጣችን ጂኦፖለቲካዊ እና ስትራቴጂካዊ ስፍራ ከ33 ዓመታት በኋላ መልሰን ተረክበናል፡፡ ምርኳችን ተመልሷል፡፡

የቀጣናው ጂኦ ፖለቲካዊ አሰላለፍ በታላቁ የህዳሴ ግድብ እንደ አዲስ ተበይኗል፡፡ ከዚህ በኋላ የሀገራችን ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታና ጂኦፖለቲካዊ ስፍራ ከ1983 ዓ.ም በፊት ወደነበረው ከመመለሱ ባሻገር ከግብፅ የሚተናነስ አይደለም። ይሄን ማስቀጠል ማፅናትና ተቋማዊ ማድረግ እንዳለ ሆኖ። ስለ ጂኦፖለቲካዊ አንድምታ ይህን ያህል ካልሁ አይቀር ስለ ጽንሰ ሃሳቡ ደግሞ ትንሽ ልበል።

ጂኦፖለቲካ ማለት ከዓለም አቀፍ ግንኙነት አንጻር ወይም አኳያ የጂኦግራፊንና የፖለቲካን ግንኙነት ማጥናት ነው። የሀገራችን አንድነት ፣ ድንበር ፣ የተፈጥሮ ሀብት ፣ የሕዝብ አሰፋፈር ፣ የእድገት ደረጃ ፣ የምታራምደው የፖለቲካ ሥርዓትና ወታደራዊ አቅም የሀገራችንን የጂኦፖለቲካ ዋጋ ይወስናል። የሀገራችን የሕዝብ ብዛትና የተፈጥሮ ሀብት ጂኦፖለቲካ ከፍ ሲያደርጉት፤ በአንጻሩ የሀገሪቷ ውስጣዊ አንድነት ደካማ መሆን ጂኦፖለቲካዊ ስፍራዋን ወይም ዋጋውን ያሳንሰዋል። የሕዳሴው ግድብ መጠናቀቅ ደግሞ ጂኦፖለቲካዊ ቦታዋን ከፍ ያደርገዋል።

> **የቀጣናው ጂኦ ፖለቲካዊ አሰላለፍ በታላቁ የህዳሴ ግድብ እንደ አዲስ ተበይኗል። ከዚህ በኋላ የሀገራችን ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታና ጂኦፖለቲካዊ ስፍራ ከ1983 ዓ.ም በፊት ወደነበረው ከመመለሱ ባሻገር ከግብፅ የሚተናነስ አይደለም**

የአረቡ ዓለም የነዳጅ ባለቤት መሆኑ ከተረጋገጠ ፣ እኤአ በ1948 ዓ.ም እስራኤል የአይሁዶች መንግሥት ሆና ከቆመች፣ ከ1993 ዓ.ም የመስከረም 1ቀን የሽብር ጥቃት በኋላ የአሜሪካ፣ የምዕራባውያንና የዓለም አቀፉ ተቋማት የውጭ ግንኙነትና ዲፕሎማሲ ማጠንጠኛ ነዳጅ ፣ የእስራኤል ደህንነት እና የጸረ ሽብር ዘመቻ ሆነ፡፡ ዛሬ እንዲህ ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል ሁኔታ ወደ ቻይናና ራሺያ ሊወሰድ ሆኖም ለቆየው የአሜሪካ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ተግባራዊነት ከአረቡ ዓለም ግብፅ ቀዳሚዋ ስትራቴጂካዊ አጋር ሆና ተመርጣለች፡፡

ግብፅን ተመራጭ ያደረጋት ለምዕራባውያን የጡት ልጅ እስራኤል ጎረቤት መሆኗ፤ መልከዓ ምድራዊ አቀማመጧ በተለይ የስዊዝ ቦይ ባለቤት መሆኗ፤ የእስላማዊ አስተምህሮ ማዕከል እና የአረብ ብሔርተኝነት አቀንቃኝ መሆኗ፤ ዜጎቿ ከሌላው የአረብ ዓለም ጋር ሲነጻጸር በዓለማዊም ሆነ በእስላማዊ ትምህርት የገፉ በመሆናቸው በአጠቃላይ በነበራት ጂኦፖለቲካዊ በምዕራባውያንም ሆነ በእስላማዊው ዓለም ዘንድ ሞገስ አግኝታለች፡፡ ይህን ሞገሷን የአረቡን ዓለም ጨምሮ የአረብ ሊግን እንዳሻት ለማሽከርከር ትጠቀምበታለች፡፡

በልዩነትና በክፍፍል ከሚንጠራወዘው የአረቡ ዓለም ግብፅ እንደ ሰንደቅ ከፍ ብላ እንድትታይ ረድቷታል። ይህን መከፋፈል እስራኤልን ጨምሮ አሜሪካውያን ሆኑ ምዕራባውያን ይፋ ባያወጡትም የሚደግፉት ስለሆነ ግብፅ ሽብልቅ ሆና እንድታገለግል አሞሌ እያላሱ ( ብድርና እርዳታ እየሰጡ) በአናቱ የጦር መሳሪያ እስካፍንጫዋ እያስታጠቁና ወታደራዊ ስልጠና እየሰጡ ይንከባከቧታል፡፡ ይለባኟታል፡፡ አሜሪካ ብቻ በየዓመቱ ወደ 4 ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ የጦር መሳሪያ ፣ የወታደራዊ እርዳታና የልማት ድጋፍ ታደርጋለች፡፡

ግብፅ በአጸፋው ይህን ውለታ ከግምት ያስገባ እና እኤአ በ1979 በአንዋር ሳዳትና በእስራኤል መካከል የተፈረመውን የሰላም ስምምነት መሰረት ያደረገ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ቀርጻለች፡፡ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ፣ ደህንነትና ፖለቲካ በመዳፉ የጠቀለለው የግብፅ ጦርና ደህንነት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲን ተግባራዊነት ያረጋግጣል፤ በአይነ ቁራኛ ይከታተላል ፡፡ ዘብ ሆኖ ሌት ተቀን ከአረቡ አብዮት በኋላ በምርጫ የፈርኦኖችን በትረ ስልጣን ጨብጠው የነበሩ የመጀመሪያው የእስላም ወድማማቾቹ አባል ፕሬዚዳንት ሞሐመድ ሙርሲ እንኳ የድርጅታቸውንም ሆነ አክራሪ እስላሞች ግፊት ተቋቁመው የግብፅና እስራኤልን የሰላም ስምምነት ማክበር ችለዋል፡፡

መጀመሪያ በመፈንቅለ መንግሥት በኋላ በምርጫ ወደ መንበሩ የመጡት ፕሬዚዳንት አብዱልፈታህ አልሲሲም ከናሰር ፣ ከሳዳት ፣ ከሙባረክና ከሙርሲ በላይ የሰላም ስምምነቱን እያስፈጸሙ ነው ፡፡ የእስራኤል ጉዳይ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲያቸው ቀኖና ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከእስራኤል ጀርባ ደግሞ አሜሪካ አለች፡፡ ግብፅ ናይል የህልውናዬ ጉዳይ ነው ብላ በሕገ መንግሥቷ ብታካትተውም፤ በውስጠ ታዋቂ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲዋ የማዕዘን ራስ ቢሆንም በግላጭ ትኩረቱ እስራኤል ፣ ፍልስጤምና አሜሪካ ላይ ነው፡፡

ወደ ዋናው ርዕሰ ጉዳዬ ስመለስ፤ ዘላቂው መፍትሔ ውስጣዊ ሀገራዊ ጉዳያችን እንደ ግብጽ ላሉ ታሪካዊ ጠላቶቻችን አሳልፎ እንዳይሰጠን ችግሮቻችንን ቀርፈን ሀገራዊ አንድነትን መመለስ ነው። እንዲሁም ምዕራባውያን ድህነታችንና ኋላቀርነታችንን መያዣ አድርገው ዝቅ አድርገው እንዳያዩን፤ ከፍ ሲልም በእርዳታና በብድር ሰበብ በነጻነታችንና በሉዓላዊነታችን ላይ እንድንደራደር እጃችንን ለመጠምዘዝ የሚደረገውን ጥረትና ጫና ለመቋቋም የድህነትንና የኋላቀርነትን ቀንበር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከላያችን ላይ መስበር አለብን። የግብርናው ፣ የኢንዱስትሪው፣ የአገልግሎት ዘርፉን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ የድህነትንና የኋላቀርነትን ቀለበት ሰብረን የመውጣት ጉዳይ ለነገ የሚተው ጉዳይ አይደለም።

አስተማማኝ ሰላም ማስፈን፣የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ፣ የስራ ዕድል መፍጠር ፣ የዋጋ ግሽበትንና የኑሮ ውድነትን ከመቀነስ ጎን ለጎን ደግሞ የዴሞክራሲ፣ የደህንነትና የጸጥታ ተቋማትን መገንባት፤ የሕዝብን አንድነት የሚሸረሽሩ ፖለቲካዊ ሴራዎችንና ደባዎችን ተቆራርጦ መታገል፣ ብልሹ አሰራሮችንና ሙስናን ፣ ጽንፍ የረገጠ ብሔርተኝነትን ፣ ወዘተረፈ ማስወገድ፤ ውስጣዊ ለቀውስ ተጋላጭነትን ከመቀነስ ባሻገር እንዳለፉት አምስትና ስድስት ዓመታት ያሉ ያላባሩ ጫናዎችን ለመመከት ጉልበት ይሆናሉ። ከውጭው ጫና ይልቅ እነዚህን የቤት ሥራዎቻችንን አበክረን ባለመከወናችንና ባለመስራታችን የሚመጣብን አደጋ የከፋ መሆኑ ግንዛቤ ተወስዶ ሊሰራ ይገባል።

ለዚህ ነው በተለይ የሕዳሴው ግድብ ላይ ተደቅኖበት የነበረን አደጋ የመቀልበስ ፣ የአረንጓዴ አሻራ ፣ የኩታ ገጠም እርሻ ፣ የበጋ ስንዴ ፣ የሜካናይዜሽን ግብርናን ፣ ወዘተረፈ በመተግበር የሚጨበጥ ለውጥ ያመጣው። ሕዳሴውን ከለየለት ክሽፈት ታድጎ ለዚህ ስኬት የበቃው። ይህ ስኬት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲያችን አካልና መደላድል ነው ። ውስጣዊ ድሎቻችን ለውጭ ጉዳይ ፖሊሲያችን አቅም ናቸው። የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ጉምቱ አሜሪካዊ ሪቻርድ ሀስ፤ “ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ከሀገር ቤት ይጀምራል ፤ “/ FOREIGN POLICY BEGINS AT HOME :...”በሚል መጽሐፉ ይሄን ይተነትናል።

ሰሞነኛውን የሶማሊያና የግብጽ ያልተቀደሰ ጋብቻን እግረ መንገድ እንዳስ። በቅርቡ በሶማሊያ እና በግብጽ መካከል የተፈረመው ወታደራዊ ስምምነት ተግባራዊ ወደ መሆን ተሸጋግሯል። ለዚያም ነው የግብጽ ሁለት ወታደራዊ አውሮፕላኖች በሶማሊያ ዋና ከተማ ሞቃዲሾ የጦር ጄነራሎችን እና መሳሪያዎችን ይዘው ማረፋቸው የተሰማው። በግብጽ የሶማሊያ አምባሳደር አሊ አብዲ አዋሬ፣ ይህ የግብጽ ጦር ከጥር 2025 ጀምሮ የአፍሪካ ህብረት ጥላ ሥር በመሆን የሽግግር ተልዕኮ (አትሚስ)ን የሚተካው አዲሱ የሰላም አስከባሪ ተልዕኮ ከመተካቱ በፊት የሆነ ነው ብለዋል።

በተጨማሪም በመጪው ዓመት ጥር ወር የሚጠናቀቀው በሶማሊያ የአፍሪካ ህብረት የሽግግር ተልዕኮ (አትሚስ)ን የሚተካው አዲሱ የሰላም አስከባሪ ተልዕኮ በተለያዩ ጊዜያት የሚሰማሩ 10 ሺህ ወታደሮችን ግብጽ ለማሰማራት ዕቅድ ይዛለች። የግብጽ ጦር የሶማሊያ መሬት ላይ እግሩን ማሳረፉ በኢትዮጵያ ዘንድ በበጎ አልታየም። ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ ላይ እየገነባችው ባለው ታላቁ የህዳሴ ግድብ ምክንያት፣ ራስን እንደ ነጻ ሀገር ካወጀችው እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅና ካላገኘችው ሶማሊላንድ ጋር የባህር ኃይል ጣቢያ ለማግኘት ባደረገችው ስምምነት የተነሳ ከግብጽ እና ከሶማሊያ ጋር ሆድና ጀርባ ከሆነች ሰንበትበት ብሏል ይለናል ቢቢሲ።

ምንም እንኳ ግብጽ በሶማሊያ ዋና ከተማ ሞቃዲሾ አየር ማረፊያ ስለደረሱት የጦር ጄነራሎቿ እና መሳሪያዎቿ ያለችው ነገር ባይኖርም ጉዳዩን በቅርበት የሚከታተሉ ግን፣ በአፍሪካ ቀንድ ውጥረት መንገሱን የጦርነት ነጋሪት ጉሰማ መሆኑን በማንሳት ይህ ለአዲስ አበባ የተላከ መልዕክት ነው እያሉ ነው። ግብጽ ከኢትዮጵያ ጋር በህዳሴ ግድብ ላይ የምታደርገው ድርድር መቋጫ ባያገኝም፣ በሱዳን ግጭት ውስጥ ሊኖራት የምትፈልገው ተጽዕኖ የምትፈልገውን ያህል ውጤት ባያመጣም፣ በቀይ ባሕር ላይ የየመኖቹ ሁቲዎች የሚያደርሱት ጥቃት ቢጨምርም እየተዳከመ የሚገኘው የውጭ ጉዳይ ፖሊሲዋ ላይ ለውጥ የማድረግ ፍላጎት አላት።

የግብጽ አዲሱ የትብብር ርዕይ ኡጋንዳን፣ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎን፣ ካሜሮንን፣ ኬንያን፣ ደቡብ ሱዳንን፣ ማዕከላዊ ሪፐብሊክ አፍሪካን፣ ጂቡቲን፣ ኤርትራን፣ ታንዛንያን፣ ሶማሊያን እና ናይጄሪያን ያካተተ ነው። ለዚህ ነው የግብጽ አካሄድ ኢትዮጵያን ጂኦፖለቲካዊ ከበባ ውስጥ በማስገባት መፈናፈኛ ማሳጣት ነው የሚባለው። ኢትዮጵያ ሶማሊያ የግዛቷ አንድ አካል አድርጋ ከምትቆጥራት ሶማሊላንድ ጋር በኤደን ባህረ ሰላጤ ላይ የባሕር በር የማግኘት እና በምትኩ ዕውቅና የመስጠት ስምምነት መፈረሟን ተከትሎ ሶማሊያ ላቀረበችላት ጥሪ ምላሽ መስጠት አድርገው የሚያዩት አሉ።

ሌሎች ጉዳዩን በቅርበት የሚከታተሉ አካላት ኢትዮጵያ “በቀይ ባሕር ላይ ያላት ፍላጎት” የባሕር ኃይል በሶማሌላንድ እስከ መገንባት ከደረሰ፣ የግብጽ ዋነኛ የንግድ መስመር እና የገቢ ምንጭ የሆነው ስዊዝ ካናል ላይ አደጋ ሊኖረው ይችላል የሚል ስጋት ቀስቅሷል። ባለፈው ዓመት ጥር ወር ላይ ፕሬዚዳንት አብዱልፈታህ አልሲሲ ለሥራ ጉብኝት ግብጽ ከነበሩት የሶማሊያው ፕሬዚዳንት ሀሰን ሼክ ሞሐሙድ ጋር በመሆን በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ሀገራቸው ሶማሊያ ደኅንነት ላይ የሚደቀን ማንኛውንም አደጋ አትፈቅድም ሲሉ የተናገሩ ሲሆን፤ ይህም በበርካቶች ለኢትዮጵያ የተላለፈ መልዕክት ተደርጎ ተወስዷል።

በቀጣዩ ወራትም በሶማሊያ እና በግብጽ መካከል ያለው ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ያደገ ሲሆን፤ ይህም ከካይሮ ሞቃዲሾ የቀጥታ የአየር በረራ በመጀመር፤ ግብጽ በሞቃዲሾ ኤምባሲዋን መክፈት ታይቷል። የሶማሊያ ፕሬዚዳንት ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ካይሮ ባቀኑበት ወቅትም ሁለቱ ሀገራት ወታደራዊ ስምምነት ተፈራርመዋል። ኢትዮጵያ ወታደሮችን እንዲሁም የጦር መሳሪያዎችን የጫኑ ሁለት የግብጽ የጦር አውሮፕላኖች በሞቃዲሾ የአየር ማረፊያ ደርሰዋል መባሉን ተከትሎ የሶማሊያ መንግሥት “ቀጣናውን ለማተራመስ ከሚሹ የውጭ ኃይሎች ጋር እየሰራ ይገኛል” ስትል ከስሳለች።

ከዚህ በተጨማሪም የአፍሪካ ቀንድ ቀጣናን ለማተራመስ እርምጃ የሚወስዱ ሌሎች ተዋናዮች አሉ ብላለች። የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤቱ ባወጣው በዚህ መግለጫ ላይ የአፍሪካ ቀንድን ለማተራመስ እርምጃ እየወሰዱ ነው ያለቻቸውን “ሌሎች ተዋናዮች”ም ሆነ የውጭ ኃይሎች ማንነት እንዲሁም በምን መንገድ እንደሆነ አልገለጸችም። ግብጽ በበኩሏ በሶማሊያ ስለሚኖራት ወታደራዊ ተሳትፎ ወይንም የጦር አውሮፕላኖቿ ሞቃዶሾ ማረፋቸውን ተከትሎ በወጣው መግለጫ ዙሪያ ያለችው አንዳችም ነገር የለም።

ሻሎም ! አሜን ።

# ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ

# የሰላማዊ ትግል ተምሳሌት - የሀንሳር ጋሪድ



ራስወርቅ ሙሉጌታ

"ስለኢትዮጵያ መቼም በእኛ በኩል የምንሰስተው፣ የማንሆነው፣ የማናደርገው ነገር አይኖርም፤ መነሻችንም መሰረታችንም ኢትዮጵያን እንደ ሀገር ማኖር፤ ሕዝቦቿም ከዚያ አንድነት እንዲጠቀሙ ማብቃት ነው፡፡ ርዕያችንም የነበረው ይኸው ነው፡፡ ከእንግዲህ ወዲህም በተቻለን ሁሉ ባለን አቅምም ጥረት የምናደርገው ለዚህ ነው፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያዊነት በዋዛ የሚታይ አይደለም፡፡" የሀንሳር ጋራድ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ፣ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት 'ስለኢትዮጵያ' ካዘጋጃቸው መድረኮች በአንደኛው መድረክ ላይ የተናገሩት ነበር፡፡

ሀገር የብዙዎች መኖሪያ መሆኗ ግልጽ ቢሆንም በሀገር ግንባታ ሂደት ለታሪክ የሚቀመጥ ሕዝብና ሀገርን የሚጠቅም ሥራ የሚከውኑት ጥቂቶች ናቸው። ምክንያቱም ከራስ አስበልጦ ለሌሎችና ለሀገር መሥራት አነሰም በዛ የሚያስከፍለው መስዋእትነት በመኖሩ ነው። ኢትዮጵያም ዛሬ የደረሰችው ትናንት ብዙዎች በከፈሉት መስዋዕትነት ጭምር ነው፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በሚሊኒየም አዳራሽ በተካሄደው የፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ የአስከሬን ሽኝት ፕሮግራም ላይ ባደረጉት ንግግር፤ ፕሮፌሰሩን እንዲህ ገልጸዋቸዋል፡፡ «እጃቸው ደም የለበትም፤ ልባቸው ጥላቻ የለበትም። ቤተሰብን መውደድ ተግቶ መሥራትና በእንዲህ ያለ ክብር ለመሸኘት መብቃት ታላቅ እድል ነው። ቀጣዩ ትውልድ ይህንን መማር አለበት። ፕሮፌሰር በየነ በሕይወት በነበሩበት ወቅት ታታሪና ሀገር ወዳድ ምሁር ነበሩ። ለሀገራቸውም በርካታ ሥራዎችን ሠርተው አልፈዋል፡ ፡ ይህ ሥራቸውም ከመቃብር በላይ ሲታወስ ይኖራል። ሁላችንም ጊዜ ሳናባክን ለሀገር ጠቃሚ ሥራዎችን ሠርተን ማለፍ አለብን »ሲሉም መልእክታቸውን አስተላልፈዋል።

ልጃቸውም ሚሻ በየነ ጴጥሮስ አባታቸውን የገለጹት እንዲህ ነበር «ሰው ወዳድ ነበር። የህይወት መርሁ የነበረው፤ እግዚአብሔርን የወደደበትን መንገድ ለሰዎች በመኖርና ሰዎችን በመውደድ ነው። ይህንንም በሥራው ፣ በቤተሰቡ በአባትነትና በባልነት ተግብሮታል። በማህበራዊ ግንኙነት ረገድ ከየትኛውም ማህበረሰብ ጋር ጠንካራ ቁርኝት ነበረው። ሰው ራስ ወዳድ ካልሆነ በቀር ጊዜው በቂ ነው ይቻላል ይለን ነበር። »

### ውልደትና እድገት

ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ከአባታቸው አቶ ጴጥሮስ ሎዳሞ ሰብሮ እና ከእናታቸው ከወይዘሮ ሸዋዬ ኢብራሒም በቀድሞው ሸዋ ጠቅላይ ግዛት በአሁኑ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በሀዲያ ዞን በምሥራቅ ባደዋቾ ወረዳ አምቡርሴ ቀበሌ መጋቢት ሁለት ቀን 1942 ዓ.ም ተወለዱ። የፕሮፌሰር በየነ ወላጅ አባት ጴጥሮስ ሎዳሞ ወታደርና የክቡር ዘበኛ አባል፣ በኋላም የፖሊስ ሠራዊት አባል በመሆናቸው በሥራቸው ምክንያት አብዛኛውን ጊዜ ከቤተሰባቸው እርቀው ይኖሩ ስለነበር ፕሮፌሰር በየነ ልጅነታቸውን ያሳለፉት ከአያታቸው ጋር ነበር።

ፍትሕ ተዛብቶ ሲያዩ ዝም የማይሉት የፕሮፌሰር በየነ ወላጅ አባት የሆኑት አቶ ጴጥሮስ ሎዳሞ ከመንደራቸው ርቀው በፍትሕ አደባባይ ተሟግተው ፍትሕ ተበይኖላቸው ወደ ቤት ሲመለሱ ባለቤታቸው ወንድ ልጅ ወልደው በማግኘታቸው ደስታቸው ድርብ ሆነ። ያገኙትን ፍትሕ ለማስታወስ ሲሉም ልጃቸውን በየነ ብለው ሰየሟቸው። የልጅነት ጊዜያቸውን እንደማንኛውም የአካባቢው ልጅ ከብት በመጠበቅና በመወጫት ከቤተሰባቸው ጋር በመልካም እንክብካቤ አድገዋል።

### የትምህርትና አካዳሚክ ጉዞ

ፕሮፌሰር በየነ አባታቸው ጴጥሮስ ሎዳሞ የክብር ዘበኛ አባል፣ የኮሪያ ዘማችና በኋላም የፖሊስ ሠራዊት አባል ስለነበሩ እንዲሁም ቤተሰቦቻቸው መንፈሳዊ ትምህርትን የቀሰሙ በመሆናቸው በለጋ እድሜያቸው ትምህርት ቤት እንዲገቡ እድል ፈጥሮላቸዋል። በሀዲያ ዞን ሾኔ ከተማ በሚገኘው አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል ድረስ የተማሩት ፕሮፌሰር በየነ ከልጅነታቸው ጀምሮ በጣም ጎበዝ ተማሪ በመሆናቸው በአንድ ዓመት ሁለት ሁለት ክፍሎችን እየደረቡ እየተማሩ በሦስት ዓመታት ብቻ ስድስተኛ ክፍልን ማጠናቀቅ ችለዋል።

የሰባተኛ ክፍል ትምህርታቸውን ሆሳዕና ከተማ በሚገኘው ራስ አባተ ቧያለው ትምህርት ቤት ካጠናቀቁ በኋላ ቀጥሎ ያለውን ትምህርት ለመከታተል ከቤተሰብ መለየት ግድ ነበርና ሻሸመኔ ከተማ ኩየራ ትምህርት ቤት ስምንተኛ ክፍል ትምህርታቸውን ተከታትለዋል። ስምንተኛ ክፍል ያስመዘገቡት ውጤት ከፍተኛ በመሆኑ አዳማ በሚገኘው አፄ ገላውዲዮስ ትምህርት ቤት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እስከ አስራ አንደኛ ክፍል ድረስ ለመከታተል ስኮላር ሺፕ አገኙ። በመቀጠልም የ12ኛ ክፍል (ለዩኒቨርሲቲ መግቢያ መዘጋጃ) ትምህርታቸውን በዕደማርያም ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተከታትለው አጠናቅቀዋል።

የ12ኛ ክፍል ትምህርታቸውን በከፍተኛ ማዕረግ ያጠናቀቁት ፕሮፌሰር በየነ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን



ሲቀላቀሉ አንድ ሰው በአእምሮአቸው ይዘው ነበር የገቡት። አፄ ገላውዴዎስ ትምህርት ቤት ሲማሩ በሳይንስ ክለብ አማካኝነት እውቁ ተመራማሪ ዶክተር አክሊሉ ለማ በእንግድነት ተጋብዘው ንግግር ሲያደርጉ ሰሙ። ዶክተር አክሊሉ በሠሩት ጥናትና በሳይንስ ዘርፍ ባካሔዱት የምርምር ሥራ በመመሰጣቸው ዶክተር አክሊሉ ለማን የትምህርት ምሳሌያቸው አድርገው ወሰዱ።

እናም ወጣቱ በየነ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ሲቀላቀል የዶክተር አክሊሉን ፈለግ በመከተል በባዮሎጂ (ስነሕይወት) ትምህርት ክፍል ትምህርታቸውን በመከታተል እሳቸውና ጓደኞቻቸው የቀዳማዊ አጼ ኃይለ ስላሴ ሥርዓት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመጨረሻ ምሩቆች ሆነው በ1965 የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ተቀብለዋል።

በወቅቱ የውጪ ሀገር መምህራንን ለመተካት እንቅስቃሴ ላይ የነበረው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እንደ በየነ ጴጥሮስ ያሉ የላቀ ውጤት ያላቸውን ተማሪዎች በጀማሪ መምህርነት እንዲሠሩ እድሉን አመቻችቶ ነበርና እሳቸውም አንድ ብለው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማስተማር ጀመሩ። ለሁለት ዓመት በዩኒቨርሲቲው ካስተማሩ በኋላ በ1967 ዓ.ም የድህረ ምረቃ ትምህርታቸውን ለመከታተል ወደ አሜሪካ ዊስኮንሲን ዩኒቨርሲቲ በማምራት በ1970 ዓ.ም የድህረ ምረቃ ትምህርታቸውን በትሮፒካል ዲዚዝ አጠናቅቀዋል። ለትምህርት ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጡ በመሆናቸውም እዚያው አሜሪካን ሀገር የሦስተኛ ዲግሪያቸውን ከቱላን ዩኒቨርሲቲ በመከታተል በማህበረሰብ ጤና (ፐብሊክ ሄልዝ) የዶክትሬት ዲግሪያቸውን አግኝተዋል።

ፕሮፌሰር በየነ በርካቶችን ከቀረጹበት የመምህርነት ህይወታቸው በተጨማሪ በተላላፊ በሽታዎች (ትሮፒካል ዲዚዝ) ላይ በርካታ ምርምሮችን ከሥራ አጋሮቻቸው እና ተማሪዎቻቸው ጋር አከናውነዋል። በተለይም በወባ በሽታ፣ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ላይ፣ በሳምባ ነቀርሳ፣ እንዲሁም በርከት ባሉ ሌሎች ህዋስ ወለድ በሽታዎች ላይ ሰፊ ምርምር አድርገዋል። ባልተሟሉ ቤተ ሙከራዎች እና ሁኔታዎች ውስጥ በተለይ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ከሌሎች በሽታዎች ጋር ስላለው ግንኙነት ሰፊ ምርምር አድርገዋል። በዚህም ከ193 በላይ ጥናቶችንና የምርምር ጹሑፎችን በዓለም አቀፍ መድረኮች ይፋ አድርገዋል። ከዚህ በተጨማሪ ፕሮፌሰር በየነ በርካታ ወጣት ተመራማሪዎችን በመምራትና በማስተባበር ለውጤት ያበቋቸው ምርምሮች በስነ ሕይወት ሳይንሱ ምርምር ዘርፍ በዓለም አቀፍና በሀገር ቤት ላበረከቱት ድርሻም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሙሉ ፕሮፌሰርነት ማዕረግ ሰጥቷቸዋል።

### ፖለቲካዊ ሕይወትና ትግል

የፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ የፖለቲካ ሕይወት እጅግ ልዩ ህይወት ነው። የብርቅዬ ልጆቿን ደም በሚጠጣው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ በእሳት የተፈተነ፣ ለአፍታም ያልተሸነፈ፣ በመላው ኢትዮጵያ ለሦስት አስርት ዓመታት ያንጸባረቀ፣ በፖለቲካ እሳት ተፈትኖ ያልተበገረ የሰላማዊ ፖለቲካ ትግል አሻራ አስቀምጠው አልፈዋል። በመሆኑም ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ትግል ስነ ምህዳር ውስጥ የሰላማዊ ፖለቲካ ትግል ምልክት ተደርገው የሚወሰዱ አንጋፋ ፖለቲከኛ ነበሩ። ተወልደው ባደጉበት የገጠር መንደር አርሶ አደሮች የለፉበትንና ላባቸውን ያፈሰሱበትን የማሳ ፍሬ ለበዝባዦች ሲገብሩ እያዩ ያደጉት ፕሮፌሰር በየነ፤ የሕዝብ በደል የገባቸው በለጋ እድሜያቸው ነበር።

ትምህርት ከቀሰሙ በኋላ ደግሞ የተበደሉ አርሶ አደሮችን አቤቱታ ለመጻፍ እድል በማግኘታቸው የማህበረሰቡን የመከራ ጥልቀት ለመገንዘብ አስቻሏቸዋል። እንዲህ በልጅነታቸው የሕዝብን በደል የተረዱት ፕሮፌሰር በየነ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ሲቀላቀሉ የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች በወቅቱ የሚያነሱትን የመብት ጥያቄ በፍጥነት ተረድተው ወደ ትግሉ ለመግባት አፍታም አልፈጀባቸውም።

ፕሮፌሰር በየነ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ደጅ ከረገጡ አንስቶ የኢትዮጵያ የለውጥ ጠያቂዎችን

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## የሰላማዊ ትግል ተምሳሌት...

ከገጽ 6 የዞረ

ሃሳብ ተጋርተው ታግለዋል። የገበሬውን ምሬት በቅርብ ማወቃቸው እና የአስተዳደር ብልሹነቱን መታዘባቸው፣ እንዲሁም መሠረታዊ የሚባሉ የማህበራዊ ግልጋሎቶች ቅንጦት ከሆኑባቸው የገጠር መንደሮች በአንዱ ማደጋቸው ብዙ መሻሻል ያለበት ጉዳይ እንዳለ ለፕሮፌሰር ግልጽ ነበር። በዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ዓመት መምህርነታቸው ወቅት «ሕዝባዊ መንግሥት ይመስረት» የሚል ደብዳቤ ይዘው ከሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር በጋራ በመሆን ለደርግ ጽህፈት ቤት በማስገባት ቁርጠኛ የሕዝብ ልጅ መሆናቸውን በተግባር ያስመሰከሩ ታላቅ የፖለቲካ መሪ ነበሩ።

በ1967 ዓ.ም የድህረ ምረቃ ትምህርታቸውን ለመከታተል አሜሪካን ሀገር በነበራቸው ቆይታ በሰሜን አሜሪካ የተማሪዎች ንቅናቄ ተሳታፊ ነበሩ። በ1970 ዓ.ም የድህረ ምረቃ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁት ፕሮፌሰር በየነ ሀገራቸውን ለማገልገል ካላቸው ጥማት እና የፖለቲካ ትግሉን በቅርበት ሆኖ መታገል ያስፈልጋል ብለው በማመናቸው በወቅቱ በሀገር ውስጥ ከነበረው የፖለቲካ ትኩሳት አንጻር ወደ ሀገር ቤት መመለስ እንደ እብደት በሚቆጠርበት ጊዜ የብዙ መካሪዎችን ምክር ወደ ጎን በመተው አሻፈረኝ ብለው ሀገራቸውን ለማገልገል ተመልሰዋል። ወደ ሀገር ቤት ተመልሰው የማስተማር ሥራቸውን እንደቀጠሉ ከሙያ ሥራቸው ጎን ለጎን በወቅቱ በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ሊስተካከሉ ስለሚገባቸው ሀገራዊ ጉዳዮች አስተያየት ከመስጠትና ለለውጥ ከመወትወት ቸል ብለው አያውቁም።

በ1983 ዓ.ም የመንግሥት ለውጥ ሲደረግ በሽግግር መንግሥት ምስረታ የሀዲያን ሕዝብ የሚወክል የፖለቲካ ቡድን በማደራጀት የፊት ለፊት የፖለቲካ ትግላቸውን ማካሔድ የጀመሩት ፕሮፌሰር በየነ፤ በሽግግር መንግስቱ የትምህርት ሚኒስቴር ምክትል ሚኒስትር በመሆን አገልግለዋል። በሽግግር መንግስቱ ላቅ ያለ አስተዋጽኦም አበርክተዋል። ከእዚህም መሀከል፤ የቀድሞ ሠራዊት እንዳይበተን ከፍተኛ ትግል ማድረጋቸው፣ የወቅቱ አየር ኃይል ህልውናው እንዲቀጥል የበኩላቸውን ሚና መወጣታቸው፤ በሰብአዊ መብት አያያዝ ኢትዮጵያ የዓለም አቀፉን የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ ያለ ምንም መሸራረፍ በሕገመንግሥቷ እንድትካተት ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ማሰማታቸው እንዲሁም የፕሬስ ነጻነት እንዲከበርና የሕግ ከለላ እንዲያገኝ የበኩላቸውን ሚና መወጣታቸው ተጠቃሽ ናቸው።

እነዚህ ለአብነት ተነሱ እንጂ ፕሮፌሰር በየነ ለሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር፣ በትምህርትና እውቀት ስርጸት፣ በብሔር ብሔረሰቦች መብት፣ መልካም አስተዳደርና ብልሹ አሠራሮች ወዘተ.. ላይ ከፍተኛ ተጋድሎ አድርገዋል። ከፖለቲካ ህይወት ፍልስፍናቸው የሚቀዳው ሰላማዊ የትግል እና የሙግት ሥርዓትን ለማስፈን አጥብቀው ታግለዋል። የሀዲያን ሕዝብ ወክለው የሽግግር መንግሥቱን የተቀላቀሉት ፕሮፌሰር በየነ፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ የደቡብ ሕብረት ፓርቲን በማቋቋም ከ1983 ዓ.ም እስከ 1987 ዓ.ም በነበረው የሽግግር መንግሥት ወቅት የተደራጀ ፖለቲካዊ ትግል በማድረግ አማራጭ የፖለቲካ ሃሳቦችን አቅርበዋል።

ከ1987 ዓ.ም አንስቶ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ባልተገባ መንገድ መጓዝ ሲጀምር ፕሮፌሰር በየነ በገዢው ፓርቲ አምባገነናዊ አካሔድ እና በተቃዋሚዎች የኃይል እና የእልህ መስመር መካከል ሰላማዊ መስመርን እየፈለጉ ለኢትዮጵያ የሚበጀውን አድርገዋል። የምርጫ ቅስቀሳ በሚያካሂዱበት ወቅት በተወለዱበት መንደር ጭምር እንደ ባዳ እየተንገላቱ ምርጫን ደጋግመው በማሸነፍ የሕዝብን ድምጽ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እያሰሙ ቆይተዋል። በሰላማዊ የፖለቲካ ትግል አማራጭ ላይ የማይናወጥ አቋም ያላቸው ፕሮፌሰር በየነ፤ የሕዝብን ድምጽ ለማሰማት ሁልጊዜም ቢሆን ተገቢው ቦታ ላይ ይገኛሉ። ጠባብ እድሎችን ታግሎ ማስፋት፣ ሰላማዊ መንገድን መከተል፣ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ መልዕክት ማስተላለፍና መታገል የፕሮፌሰር በየነ ልዩ መገለጫቸው ነበር።

የኢትዮጵያ ፖለቲካ ከዋልታ ረገጥነትና ጽንፈኝነት ተላቅቆ በሰከነ መንገድ እንዲጓዝ ብዙ ደክመዋል። የተበታተኑ ኃይሎች እንዲሰባሰቡና የሃሳብ ውህደት ለመፍጠር በሀገር ውስጥና በውጪ ያሉ ከ50 በላይ የፖለቲካ ኃይሎችን በማሰባሰብ የኢትዮጵያ የሰላምና ዲሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት በመመስረት በመምራት የተረጋጋ ፖለቲካ ለመፍጠር የመሪነት ሚናቸውን ተወጥተዋል። በአንድነትና ሕብረት ጠንካራ እምነት ያላቸው ፕሮፌሰር፤ ከምክር ቤቱ ምስረታ በተጨማሪ አስራ አምስት የፖለቲካ ፓርቲዎችን በማደራጀት "የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያ ኃይሎች ሕብረት" በማቋቋም የተደራጀና የተረጋጋ የፖለቲካ ትግል አካሂደዋል።

በደቡብ ክልል ይህ ነው የሚባል የተቃዋሚ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ባልነበረበት ወቅት ቀድመው የነቁት ፕሮፌሰር በየነ፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ሕብረት ፓርቲን መስርተው በክልሉ መንግሥትን የሚሞግት የፖለቲካ እንቅስቃሴ አድርገዋል። በወቅቱ ገዢውን ፓርቲ በምርጫ ማሸነፍ እንደሚቻል ለሀገርም ሆነ ለደቡብ ክልል የፖለቲካ ኃይሎች በተግባር አሳይተዋል።

ማህበራዊ ፍትሕ በሀገራችን ውስጥ ማረጋገጥ የህልውና ጉዳይ አድርገው የሚታገሉት ፕሮፌሰር በየነ፤ ሃሳባቸውን ለመተግበር እንዲያስችላቸው የርዕዮተ ዓለም መሰረቱ ማህበራዊ ፍትሕ የሆነውን የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራሲ ፓርቲን በመመስረት ሕይወታቸው እስካለፈበት ጊዜ ድረስ ፓርቲያቸውን ከፊት ሆነው ሲመሩ ቆይተዋል። በዚህ ሁሉ የፖለቲካ ትግል ውስጥ በብሄር በሃይማኖትና ሌሎች ሰብአዊ ልዩነቶች ውግንና ሳይዙ ለሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምጽ የነበሩ የሰብአዊ መብት ተሟጋችም ነበሩ። በሀገራችን ለሦስት አስርት ዓመታት ሰላማዊ የፖለቲካ ትግልን በማካሔድ ስላበረከቱት አስተዋጽኦ በሀገር አቀፍ ደረጃ ብሔራዊ የእውቅና ኮሚቴ ተቋቁሞ በ2013 ዓ.ም የእውቅና ፕሮግራም ተዘጋጅቶ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል። ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ የኢትዮጵያ የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ምክትል ዋና ዳይሬክተር እና ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ ሕይወታቸው እስካለፈበት ጊዜ ድረስ በዋና ዳይሬክተርነት ተቋሙን ሲመሩ ነበር።

### የሥራ ባህል

ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ እጅግ የተለየ የሥራ ባህልና ልማድ ያላቸው ሰው ነበሩ። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሙሉ ጊዜ መምህርና በአማካሪነታቸው ለተማሪዎቻቸው፣ የጥናት ወረቀቶች እርማትና ግምገማ፣ ለሳይንሳዊ ምርምር ሥራዎች በቂ ጊዜ መድበው ይሠራሉ። ምርምሮቻቸውን በጥልቀት ይፈትሻሉ፤ ማሻሻያዎችን ለተማሪዎቻቸው ይሰጣሉ። ሙሉ የሥራ ሰዓታቸውን ለመደበኛ ሥራቸው ከማዋል በተጨማሪ ቤታቸውም ወስደው ያርማሉ፤ያስተካክላሉ።

በፖለቲካው መስክ ንቁ ተሳትፎ ለማድረግ ፕሮፌሰር በየነ ለንባብ ጊዜ ይሰጣሉ። የሀገር ቤት እና የዓለም ተለዋዋጭ የፖለቲካ ሁኔታን በመመርመር እና በመተንተን የፖለቲካ አሰላለፍን ለይተው የትግል ስልትን ይቀምራሉ። በዚህ ስልት የፖለቲካ ፓርቲያቸውን ያደራጃሉ፣ ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር ይደራደራሉ፣ ገዢው ፓርቲን ይሞግታሉ። በማህበራዊ ሕይወት የነቃ ተሳትፎ ያደርጋሉ። ለቤተሰባቸውም ጊዜ አላቸው። ይህን ሁሉ ሥራ መሥራት አይከብድም ወይ ተብለው በአንድ ወቅት የተጠየቁት ፕሮፌሰር በየነ «24 ሰዓት ለሁሉም ነገር በቂ ነው» የሚል ምላሽ ሰጥተዋል።

### ቤተሰብና ማህበራዊ ሕይወት

በ1970 ዓ.ም ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ተቀብለው እንደተመለሱ ትዳር የመሠረቱት ፕሮፌሰር በየነ 47 ዓመታትን ባስቆጠረው ትዳራቸው የሁለት ወንድና የሁለት ሴት ልጆች አባት ሲሆኑ፤ አስር የልጅ ልጆችንም አፍርተዋል። ከልጆቻቸው ጋር የጓደኝነት ግንኙነት የነበራቸው ፕሮፌሰር በየነ፤ ለቤተሰባቸው ጊዜ የሚሰጡ በተለይም ልጆቻቸው ትምህርትን አጥብቀው እንዲይዙ ሁሌም የሚጎተጉቱ አባት ነበሩ። በማህበራዊ ሕይወትም የሚያውቋቸውን ሰዎች ሀዘንም ሆነ ደስታ በመካፈል ረገድ ያላቸው የጊዜ ጥበት ሳይገድባቸው ሰው ጠያቂ ነበሩ። በተለይ ደግሞ ሀዘንተኛን በማጽናናት ሁልጊዜም ቢሆን ፈጥነው የሚደርሱ የሰው ሁሉ ወዳጅ ነበሩ። በሀዲያ ሕዝብ ባህል በማህበራዊ ህይወት ተሳትፎ ለሚያደርግ፤ የተጣላ ለሚያስታርቅና ለሁሉ ሰው ወዳጅ ለሆኑ ሰዎች የሚሰጠውን ባህላዊ ሹመት «የሀንሳር ጋራድ » ባህላዊ ሹመት አግኝተዋል። «የሀንሳር ጋራድ» ማለት የሰላም ሰው የሁሉ ወዳጅ እና በማህበራዊ ህይወት ለሰው ደራሽና ጠያቂ ማለት ነው።

### የግል ባህሪይና ስብዕና ፤

ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ታላቅ የሳይንስ ምሁርና ጉምቱ የሰላማዊ ፖለቲካ ትግል ምልክት መሆናቸው በአደባባይ የሚታይ መታወቂያቸው ነበር። ፕሮፌሰሩ በሙያ ሥራቸውም ሆነ በፖለቲካ ትግላቸው ወቅት ያሳዩት የነበረው ባሕሪይ፣ ኑሮአቸውን ለመምራት የመረጡበት መንገድ፣ ለሌሎች ጥለው ያለፉት ተምሳሌታዊ ህይወት በርግጥም ፕሮፌሰር በየነ የታላቅ ስብዕና ባለቤት እንደነበሩ የሚያረጋግጥ ነው።

ፕሮፌሰር በየነ ኑሮን ቀለል አድርገው መኖር የሚመርጡ፣ ከራሳቸው ፍላጎት ይልቅ ለትውልድና ለሀገር የሚጨነቁ ስብዕና ነበራቸው። ትሁት እና ራሳቸውን ዝቅ በማድረግ የሚታወቁ ነበሩ። በፖለቲካ ትግላቸውም ሆነ በምርምር ሥራዎቻቸው ግልጽ አቋም በመያዝ ሥራን የሚሠሩ፣ ላመኑበት ነገር ዋጋ መክፈልና ኃላፊነትን መውሰድ፣ እውነትን ይዘው ፊት ለፊት የሚጋፈጡ ቁርጠኛም ነበሩ። በመርህና በምክንያታዊነት መታገል የፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ሌላው መለያቸው ነው። ሲቃወሙ ግልጽ እና ተጨባጭ ነጥቦችን በማንሳት እንደሆነ ሁሉ መልካም ብለው ለሚያምኑት ሥራም ምስጋና ለመስጠት ንፉግ አይደሉም።

በአንድ ወቅት "መልካም ስትሰሩ እደግፋለሁ፣ ስታጠፉ እቃወማለሁ" ብለው ሲናገሩም ተደምጠዋል። ራሳቸውን የሚገዙ፣ በማህበራዊ ሕይወት የነቃ ተሳትፎ የሚያደርጉና የወዳጅ ዘመዶቻቸውን ሀዘንና ደስታ የሚጋሩ ማህበራዊ ሰውም ነበሩ። በፖለቲካ ትግላቸውም ሆነ በግል ሕይወታቸው ወጥ የሆነ ማንነት የነበራቸው ተገማች ባህሪይ ያላቸው ሰው ነበሩ። ሕዝብን የሚወዱና እግዚአብሔርን የሚያከብሩ ፈሪሀ እግዚአብሔር ያላቸው ታላቅ ስብዕና ነበራቸው። ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ሕመም በህክምና ሲረዱ ቆይተው መስከረም ስድስት ቀን 2017 ዓ.ም በተወለዱ በሰባ አምስት ዓመታቸው ከዚህ ዓለም ድካም አርፈዋል። መስከረም ዘጠኝ ቀን 2017 ዓ.ም ጴጥሮስ ወጳውሎስ መካነ መቃብር ሥርዓተ ቀብራቸው ወዳጅ ዘመድና በርካታ ወዳጆቻቸው በተገኙበት ተፈጽሟል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም በእኒህ ምሁር እና ተመራማሪ፤ጉምቱ ፖለቲከኛ እና ሀገር ወዳድ ዜጋ እረፍት የተሰማውን ሀዘን መግለጽ ይወዳል።



**ከ1987 ዓ.ም**
**አንስቶ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ባልተገባ መንገድ መጓዝ ሲጀምር ፕሮፌሰር በየነ በገዢው ፓርቲ አምባገነናዊ አካሔድ እና በተቃዋሚዎች የኃይል እና የእልህ መስመር መካከል ሰላማዊ መስመርን እየፈለጉ ለኢትዮጵያ የሚበጀውን አድርገዋል**

ኢኮኖሚ

# ባህልና ቱሪዝም

## የሳተላይት አካውንት- የቱሪዝም ዘርፉን ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ የመለየት ግብ

ዳግም ከበደ

የያዝነው የመስከረም ወር ለኢትዮጵያ ቱሪዝም ልዩ ትርጉም አለው። የአዲስ ዘመን መለወጫ በሆነው በዚህ ወር በርካታ የቱሪዝም መስህብ ሁነቶች ይካሄዳሉ። እነዚህ ሁነቶች ሃይማኖታዊና ባህላዊ ስነስርአቶች ሲሆኑ ፣ በመላው ሀገሪቱ በሚያሰኝ መልኩ በተለያዩ አካባቢዎች ላይ ይከናወናሉ፡፡

ከእነዚህ መካከል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንና ምእመኖቿ የሚያከብሩት የመስቀል ደመራ ክብረ በዓል አንዱ ሲሆን፣ ይህ ታላቅ ሁነትና አከባበር በዩኔስኮ የማይዳሰስ የሰው ልጆች ወካይ ቅርስ በሚል የተመዘገበ ነው። ከዚህ ክብረ በዓል በተጨማሪ በኦሮሞ ብሄር ዘንድ በደማቅ ስነስርአት የሚከበረው የኢሬቻ በአልም እንዲሁ በወርሃ መስከረም ሰፊ ቁጥር ያለው የሀገር ውስጥና የውጪ ጎብኚዎች የሚታደሙበት የምስጋና በዓል ነው።

ከእነዚህ ሁለት ዓመታዊ ክብረ በዓላት ባሻገር ቀድሞ ደቡብ በመባል በሚታወቀው አሁን በተለያዩ ክልሎች በአዲስ በተዋቀረው የሀገሪቱ ክፍልም እንዲሁ የማህበረሰቦችን ባህል፣ ወግ፣ እሴት፣ ሀገር በቀል እውቀት የሚያሳዩ የአዲስ ዘመን መለወጫ ሁነቶች ይካሄዳሉ። ሁነቶቹ ለውጪም ሆነ ለሀገር ውስጥ ጎብኚዎች ልዩ ትውስታን የሚያጭሩ፣ እውቀትን የሚያስጨብጡና የሰው ልጆችን ማቀራረብ የሚያስችል ጥልቅ ጥበባዊ እሴት የያዙ ሆነው እናገኛቸዋለን። በማይዳሰስ የመስህብ ሀብት ውስጥ የሚመደቡት በዓላቱ ኢትዮጵያውያን በመስከረም ወር የሚያከብሯቸው ታላላቅ በዓላት ናቸው።

**መስከረም ለሀገሪቱ ቱሪዝም ከዚህም ያለፈ ትርጉም** አለው። በዚህ ወር የዓለም ቱሪዝም ቀን ይከበራል። ለተፈጥሮ፣ ለባህል፣ ለታሪክ፣ ለአርኪዮሎጂ፣ ለቅርስ እና መሰል እሴቶች መጠበቅና ውግንናን ለማሳየት ወሩ በልዩ ሁኔታ ለቱሪዝም ልዩ ትኩረት የሚሰጥበት እንዲሆን ተሰይሞበታል።

ለሀገሪቱ የተለያዩ ማህበረሰቦች እሴቶች ከሆኑት ኢትዮጵያዊ ታላላቅ ሁነቶች የሚካሄዱ ከመሆናቸው ባሻገርም የተለያዩ ቱሪዝም ነክ ሁነቶች በወርሀ መስከረም ይካሄዳሉ። በያዝነው 2017 ዓ.ም ተመሳሳይ ሁነቶች ተካሂደዋል። ከእነዚህ መካከል የቱሪዝም ሚኒስቴር በዓለም አቀፍ ደረጃ ያካሄደው አውደ ርዕይ ሲሆን፣ በዚህም የኢጋድ ሀገራት ተሳትፈውበታል። ሁነቱ በየዓመቱም ታስቧል፤ ቀስ በቀስም ዓለም አቀፍ ተሳታፊዎች ጭምር እንዲካተቱበት ለማድረግ ታቅዷል።

የኢትዮጵያ መንግሥት ለቱሪዝም ዘርፍ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ በመዳረሻ ልማት ፕሮጀክቶች፣ የመስህብ ስፍራዎችን በማስተዋወቅ፣ አዳዲስ መዳረሻዎችን ይፋ በማድረግ እንዲሁም ዘርፉ ለሀገሪቱ ምጣኔ ሀብት እድገት ጉልህ ድርሻ እንዲኖረው የፖሊሲ ማሻሻያዎችን በማፅደቅ እየሰራ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ። እነዚህን ተግባራት የሚያጠናክሩ ስራዎችም በዚህ በያዝነው የ2017 ዓ.ም ወርሀ መስከረም እየተካሄዱ ናቸው።

ከእነዚህ ውስጥ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ይፋ ያደረገው የቱሪዝም ሳተላይት አካውንት (TSA) አውደ ርእይ አንዱ ነው፡፡ ይህም በቱሪዝም ዘርፉ አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ አስተዋጽኦ ማድረግ የሚያስችል ሳይንሳዊ ስልት መሆኑ ተጠቁሟል፡፡ የቱሪዝም ሳተላይት አካውንት አውደ ርእዩን ይፋ ከማድረግ ባሻገር የኢጋድ ሀገራት የዘላቂ የቱሪዝም ዘርፍ ልማት እቅድ የጸደቀበት ሁነትም ተካሂዷል።

የቱሪዝም ሳተላይት አካውንት በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን የመስህብ ሀብቶች እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ አስተዋጿቸውን (በያዝነው የመስከረም ወር የሚከበሩትን የማይዳሰሱ ባህላዊ ሀብቶችን ጨምሮ) በሚመለከት ትክክለኛ መረጃ ይሰጣል። የቲኤስ ኤው የማስጀመሪያ መርሀ ግብርም ደማቅ ክብረ በዓላትን በሚያስተናግደው እንዲሁም የዓለም የቱሪዝም ቀን በሚከበርበት ወር ማስጀመሪያ ላይ ነው ይፋ የተደረገው።

በዚህ በዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም በተደረገ ይፋ የማድረጊያ ሥነሥርዓት ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የቱሪዝም ሚኒስትር አምባሳደር ናንሲሴ



አምባሳደር ናንሲሴ ጫሊ

ጫሊ፤ ኢትዮጵያ በታሪካዊ፣ ተፈጥሯዊ እና ባህላዊ ሀብቶችና የቱሪዝም መዳረሻዎች የበለጸገች ሀገር መሆኗን ጠቅሰው፤ የኢትዮጵያ ቱሪዝም ሳተላይት አካውንት ይፋ መሆን በዘርፉ ያለውን የተደራጀ መረጃ ውስንነት መፍታት ያስችላል ብለዋል፡፡

‹‹ኢትዮጵያውያን የአብሮነት መሰረታቸው፣ ባህላቸውና ወጋቸው የዓለም ጎብኚዎችን ትኩረት በመሳብ ለዓመታት ዘልቋል›› ያሉት አምባሳደሯ፤ ያላትን እምቅ የቱሪዝም አቅም በቱሪዝም መሰረተ ልማት ማበልፀግ ባለመቻሏ ከዘርፉ የሚገባትን ጥቅም ሳታገኝ እንደቆየች አመልክተዋል።

ከለውጡ በኋላ መንግሥት ለዘርፉ ትልቅ ትኩረት በመስጠት ቱሪዝምን ለማሳደግ እየሰራ መሆኑን በመግለፅም፣ ቱሪዝም የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ መሰረታዊ በሆነ መንገድ መቀየር የሚችል አቅም እንዳለውም ተናግረዋል፡፡ እሳቸው እንዳሉት፤ ቱሪዝም የውጭ ምንዛሪን በማሳደግና የሥራ ዕድል በመፍጠር የጎላ አበርክቶ አለው፡፡ አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የቱሪዝም ዘርፉን ለማዘመን እየተሰራ ይገኛል። የኢትዮጵያ ቱሪዝም ሳተላይት አካውንት ለቱሪስቶች የተደራጀ መረጃ በመስጠት የተሳለጠ አገልግሎት ማግኘት ያስችላል።

የቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ስለሺ ግርማ ፤ የቱሪዝም ሳተላይት አካውንት ኢትዮጵያ በ2017 ዓ.ም በመስከረም ወር ለመጀመሪያ ጊዜ ይፋ ማድረጓን አስመልክቶ ስለ ጉዳዩ ዝርዝር ማብራሪያ ሰጥተዋል። የዝግጅት ክፍላችንም የቱሪዝም ሳተላይት አካውንት ምንነት እንዲሁም የሚሰጠውን ጠቀሜታ በሚከተለው መልኩ አቅርቦታል።

### የቱሪዝም ሳተላይት አካውንት (TSA)

የቱሪዝም ሳተላይት አካውንቱ መስከረም 7 ቀን 2017 ዓ.ም በዓድዋ ሙዚየም ይፋ ተደርጓል፡፡ ሚኒስትር ዴኤታው የቱሪዝም ሚኒስቴር ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የኢትዮጵያን የቱሪዝም መዳረሻዎች እና ሀብቶች የመጠበቅ፣ የማልማትና የማስተዋወቅ ተልእኮ እንደተሰጠው ይገልጻሉ፡፡ ይህንን አስመልክቶም መስሪያ ቤቱ ቱሪዝም ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ በቅጡ ተገንዝቦ ለመተንተን እና በማስረጃ ላይ የተመሰረተ የፖሊሲ ቀረጻ እና ስልታዊ የእቅድ ዝግጅትን እውን ለማድረግ ለሀገሪቱ የመጀመሪያ የሆነውን የቱሪዝም ሳተላይት አካውንት (TSA) ከተለያዩ አጋር አካላት ጋር በመተባበር ማዘጋጀቱን ይናገራሉ፡፡

‹‹የቱሪዝም ሳተላይት አካውንት ይፋ መደረጉ ኢትዮጵያን የቱሪዝም ሳተላይት አካውንትን በስኬት አጠናቀው ተግባራዊ ካደረጉ ጥቂት የአፍሪካ ሀገራት ተርታ ያሰልፋታል›› የሚሉት ሚኒስትር ዴኤታው አቶ ስለሺ ግርማ፤ ለኢትዮጵያ ቱሪዝም እድገት ጉልህ ድርሻ እንደሚኖረውም አስረድተዋል።

### የቱሪዝም ሳተላይት አካውንት ምንድነው?

የቱሪዝም ሳተላይት አካውንት የተመድ /ዩኤን/ ቱሪዝም ተቋም፣ ከተመድ ስታቲስቲክስ ክፍል፣ ከዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት እና ከሌሎች ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በመተባበር ያዘጋጀው ዓለም አቀፍ እውቅና ያለው የስታቲስቲክስ ማእቀፍ መሆኑን የሚያስረዱት አቶ ስለሺ፤ የሳተላይት አካውንቱ ቱሪዝም በኢኮኖሚ ላይ የሚያሳድረውን አዎንታዊ ተጽእኖ ወጥነት ባለው ሁኔታ የሚለካ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ዘርፉ ለሀገር ኢኮኖሚ ያለውን አበርክቶ በጥልቀት እንደሚያሳይ ያብራራሉ፡፡

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ማብራሪያ፤ የቱሪዝም ሳተላይት አካውንቱ ማስረጃን መሰረት ላደረገ ፖሊሲ ቀረፃ፣ ውሳኔ አሰጣጥ እና ስልታዊ እቅድን እውን ለማድረግ የሚያስችል የመረጃ ምንጭ ሲሆን፣ ይህም ከቱሪዝም ዘርፍ የሚያገኘውን ኢኮኖሚያዊ አበርክቶ አሟጦ ለመጠቀም የሚያስችል ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ አለው፡፡

የስታቲስቲክስ ማእቀፉ ቱሪዝም ለጠቅላላ አመታዊ ምርት (GDP) የሚያበረክተውን ቀጥተኛ ድርሻ፣ ዘርፉ ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች አንጻር ያለውን አንጻራዊ ግዝፈት (መጠን) ፤ ዓለም አቀፍ የቱሪዝም ግብይት መጠንን እንዲሁም መንግሥታት ከቱሪዝም ክንውኖች የሚያገኙትን የገቢ መጠን ለመረዳት የሚያስችል እንደሆነም አቶ ስለሺ ይናገራሉ። ዘርፉ ለስራ ፈጠራ እና ለኢንቨስትመንት የሚያደርገውን አስተዋጽኦም ለማወቅ እንደሚያግዝ አስረድተዋል፡፡

### የቱሪዝም ሳተላይት አካውንት ለምን አስፈለገ?

‹‹ኢትዮጵያ የቱሪዝም ዘርፍ ለኢኮኖሚ የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ በትክክል ለመለካት የሚያስችል ጠንካራ የስታቲስቲክስ ማእቀፍ አልነበራትም›› የሚሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ይህ የመረጃ ክፍተት ሀገሪቱ ቱሪዝም የሚያስገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም አሟጣ መጠቀም እንዳትችል አድርጓታል ይላሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ የቱሪዝም ዘርፍን የተመለከተ የመረጃ ውስንነት መኖሩን በመግለፅም፤ በዋናነት ወደ ሀገር የሚገቡ የቱሪስቶችን ቁጥር እና ጎብኚዎች ለዳሰሳ ጥናት የሚሰጡትን ምላሽ መሰረት ያደረገ እንደሆነ ያነሳሉ፡፡

ካሁን ቀደም የነበረው የተበታተነ የመረጃ አሰባሰብ ሂደት አመርቂ የፖሊሲ ቀረጻ እና አተገባበር እንዳይኖረን ምክንያት ሆኖ ቆይቷል የሚሉት አቶ ስለሺ ግርማ፤ ለዚህ ተገዳሮት እልባት ለመስጠት ቱሪዝም ሚኒስቴር ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን /ኢሲኤ/ ቴክኒካል ድጋፍ በመጠየቅ የኢትዮጵያን ቱሪዝም ሳተላይት አካውንት ማዘጋጀቱን አስረድተዋል፡፡

### ዝግጅቱ መቼ ተጀመረ?

የቱሪዝም ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነት ሥራ አስፈፃሚ አቶ አለማየሁ ጌታቸው ያደረሱን መረጃ እንደሚያመለክተው፤ የኢትዮጵያ የቱሪዝም ሳተላይት አካውንት ዝግጅት ከፕላን እና ልማት ሚኒስቴር እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር እ.ኤ.አ በ2023 የካቲት ወር ነው የተጀመረው፡፡ በቅርቡ ይፋ በተደረገበት ሥነሥርዓት ላይም የኢጋድ ሀገራት ዘላቂ ቱሪዝም ልማትን የተመለከተ ዝግጅት ተደርጓል።

ኢጋድ እና አባል ሀገራቱ ዘላቂ የቱሪዝም ልማትን በቀጣናው እውን ለማድረግ የሚያስችላቸው ዘላቂ የቱሪዝም ማስተር ፕላንም ተዋውቋል፡፡ ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ የኢጋድ ሴክሬታሪያት እና ዩኤን ኢሲኤ የሚመለከታቸው አካላት በተገኙበት የዘላቂ ቱሪዝም ማስተር ፕላኑ መስከረም 9 ቀን መርሀ ግብሩ ተከናውኗል፡፡

የኢጋድ ዘላቂ ቱሪዝም ማስተር ፕላን (STMP) የኢጋድ አባል ሀገራት ዘላቂ የቱሪዝም ልማትን ለማረጋገጥ በጋራ ያዘጋጁት የ10 ዓመት ማስተር ፕላን ነው፡፡ ማስተር ፕላኑ የቀጣናው ሀገራት የተቀናጁ እና ተወዳዳሪ የቱሪዝም መዳረሻዎች መሆን እንዲችሉ የሚረዳ የቱሪዝም ልማት ማእቀፍ ነው፡፡ የዝግጅት ክፍላችን ይህንን ርእሰ ጉዳይ በቀጣይ እትም የሚመለከተው ይሆናል።

### እንደ መውጫ

በመግቢያችን ላይ ለማስቀመጥ እንደሞከርነው ኢትዮጵያ የበርካታ መስህቦች ባለቤት ነች። በመስከረም ወር የሚካሄዱትን ቱሪዝም ነክ ሁነቶች ብቻ ነጥለን ብንመለከት ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታቸው ጉልህ የሆነ ሀገር በቀል እውቀቶች፣ እሴቶችን የሚያንፀባርቁ በርካታ መስህቦችን መጥቀስ እንችላለን።

ከተፈጥሮ ሀብት እስከ ታሪካዊ ቦታ፣ ከዱር እንስሳት መኖሪያ ፓርክና ጥብቅ ቦታዎች እስከ አርኪዮሎጂካል ስፍራ አያሌ ለጉብኝት ምቹ የሆኑ ሀብቶችን መዘርዘር እንችላለን። ይሁን እንጂ እነዚህን የመስህብ ሀብቶች በትክክለኛው መረጃ አደራጅቶ፣ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳቸውንና ጠቀሜታቸውን ለይቶ ለመተንተን የሚያስችል የመረጃ ሥርዓት አልነበረም። በተለያዩ ጊዜያት የሚወጡ አሀዛዊ መረጃዎች ትክክለኛውን የኢትዮጵያን የቱሪዝም እድገት የሚለኩ፣ ክፍተቶችን የሚለዩ፣ ቱሪዝም በሀገሪቱ ላይ የሚያሳድረውን ተፅእኖ የሚያሳዩ አልነበሩም።

ከዚህ የተነሳ ከታችኛው ማህበረሰብ ጀምሮ እስከ ሀገራዊ ጥቅል ጉዳይ የቱሪዝም ድርሻንና ተፅእኖን በትክክል መለየት ሳይቻል ቆይቷል። የመገናኛ ብዙኃንም እርስ በእርሳቸው የሚጣረሱ መረጃዎችን ይፋ ሲያደርጉ ይስተዋላል።

ይህ የሆነው የቱሪዝም ሳተላይት አካውንትን የመሰለ ሳይንሳዊ መለኪያ ተግባራዊ ባለመደረጉ ነው። ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አሁን ይህንን ችግር ይፈታልኛል ያለውን ማእቀፍ በአዲስ ዘመን መባቻ የመስከረም መጀመሪያ ይፋ አድርጎ ወደ ሥራ መግባቱን ነግሮናል። በቀጣይ ተግባር ላይ የሚውለውን ይህንን ማእቀፍ ተንተርሰው የሚወጡ አዳዲስ መረጃዎችንም የዝግጅት ክፍላችን በመከታተል የሚያቀርብ ይሆናል።

ሰላም!

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

## ዲፕሎማት እና የታሪክ ምሁሩ

ዋለልኝ አየለ

ስለኢትዮጵያ ቀደምት ታሪኮች ሲጠቀስ የእኚህን ምሁር ስም መጥቀስ የተለመደ ነው። በብዙ የታሪክ ድርሳናት ውስጥ የእርሳቸው መጻሕፍት ምንጭ ተደርገው ይጠቀሳሉ። «ከንግሥት ሳባ እስከ ዓድዋ» ከሚለው መጽሐፋቸው ጀምሮ የኢትዮጵያን የጥንት፣ የመካከለኛው ዘመን እና ዘመናዊ ታሪኮችን አስተዋውቀዋል። «ወዳጄ ልቤ» በሚለው መጽሐፋቸው በብዙዎች ዘንድ ይታወቃሉ።

በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ አምዳችን ከ86 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት መስከረም 9 ቀን 1931 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩትን ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴን እናስታውሳለን። ከዚያ በፊት ግን እንደተለመደው በዚህ ሳምንት የተከናወኑ ሌሎች ዓለም አቀፍ እና የሀገር ውስጥ የታሪክ ክስተቶችን እናስታውስ።

ከ129 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት መስከረም 7 ቀን 1888 ዓ.ም  የዓድዋ ጦርነት የክተት ዘመቻ አዋጅ ታወጀ። ንጉሰ ነገሥት ዳግማዊ አጼ ምኒልክ የውጫሌን ውል እንደማይቀበሉና ሁሉም ኢትዮጵያውያን ሀገራቸውን ከወራሪ ጠላት እንዲከላከሉ የሚያሳስብ ታሪካዊ አዋጅ ተናገሩ።  መስከረም 7 ቀን 1888 ዓ.ም የታወጀው አዋጅ የሚከተለው ነበር።

«እግዚአብሔር በቸርነቱ እስካሁን ጠላት አጥፍቶ ሀገር አስፍቶ አኖረኝ፤ እኔም እስካሁን በእግዚአብሔር ቸርነት ገዛሁ፤ እንግዲህ ብሞትም ሞት የሁሉ ነውና ስለኔ ሞት አላዝንም፤ ደግሞ እግዚአብሔር አሳፍሮኝ አያውቅም፤ ወደፊትም ያሳፍረኛል ብዬ አልጠራጠርም። አሁን ግን ሀገር የሚያጠፋ፣ ሃይማኖት የሚያስለውጥ ጠላት እግዚአብሔር የወሰነልንን ባህር አልፎ መጥቷል፤ እኔም ያገሬን ከብት ማለቅና የሰውን መድከም ዐይቼ እስካሁን ዝም ብለው ደግሞ እያለፈ እንደፍልፈል መሬት ይቆፍር ጀመር። አሁን ግን በእግዚአብሔር ረዳትነት ሀገሬን አሳልፌ አልሰጠውም፤ ያገሬ ሰው ካሁን ቀደም የበደልኩህ አይመስለኝም፤ አንተም እስካሁን አላስቀየምከኝም። ጉልበት ያለህ በጉልበትህ እርዳኝ! ጉልበት የሌለህ ለልጅህ፣ ለሚስትህና ለሃይማኖትህ ስትል በሀዘን እርዳኝ! ወስልተህ የቀረህ ግን ኋላ ትጣላኛለህ! አልተውህም! ማርያምን ለዚህ አማላጅ የለኝም! ዘመቻዬም በጥቅምት ነውና የሸዋ ሰው እስከ ጥቅምት እኩሌታ ድረስ ወረይሉ ከተህ ላግኝህ!»

ከ46 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት መስከረም 7 ቀን 1971 ዓ.ም  የግብጽ ፕሬዚዳንት አንዋር ሳዳት እና የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ሜናኸም ቤጊን በአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጂሚ ካርተር ሸምጋይነት፤ ከ12 ቀናት የምሥጢር ድርድር በኋላ፤ «የካምፕ ዴቪድ ስምምነት»ን ተፈራረሙ። «የካምፕ ዴቪድ ስምምነት» የመካከለኛው ምሥራቅ ፖለቲካን የለወጠ ክስተት ነበር። የአረቡ ዓለም መሪ ተደርጋ ትቆጠር የነበረችው ግብጽ ስምምነቱን መፈረሟ በከሃዲነት አስፈርጇት ለ10 ዓመታት ከአረብ ሊግ አባልነት ታገደች። ከዚህ በተጨማሪም ስምምነቱ፣ የስምምነቱ ፈራሚ የሆኑት ፕሬዚዳንት አንዋር ሳዳት እንዲገደሉ ምክንያት ሆነ።

አሁን በዝርዝር ወደምናየው የብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ ታሪክ እንመለስ።

ገና በሕፃንነታቸው ያሳዩት የትምህርት ፍላጎት፤ የነበራቸው የአዕምሮ ብሩህነት ሊቃውንት መምህሮቻቸውን አስደንቆ ከመምህሮቻቸው የተሰጡትን ስማቸውን እንዲሸልሟቸው ያስደረጉ የቀለም ቀንድ ናቸው። በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ከነበሩት የወቅቱ የኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ ምሁራን መካከል በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ እንደሆኑ በተደጋጋሚ ተመስክሮላቸዋል። ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ።

ኅሩይ የተወለደው በ1871 ዓ.ም ሸዋ፣ መርሐ ቤቴ አውራጃ፣ በታች ቤት ወረዳ፣ ረመሸት ቀበሌ፣ ደን አቦ ገዳም በተባለ ሥፍራ ነው። ወላጆቹ ያወጡለት ስም ገብረመስቀል ነበር። ገብረ መስቀል እንጦጦ ራጉኤል ደብር መጥቶ የመጻሕፍትን ትርጓሜ ከደብሩ ሊቃውንት በሚማርበት ወቅት ወልደጊዮርጊስ የተባሉት መምህሩ «ጎንደር በነበርኩ ጊዜ መምህሬ ስለሚወዱኝ ‹ኅሩይ› እያሉ ይጠሩኝ ነበር። ወደ አዲስ አበባ ከመጣሁ በኋላ ግን በዚህ ስም እየተጠራሁኝ አይደለም። አንተ የቀለም ቀንድ ስለሆንክና በምግባርህም የተወደድክ ስለሆንክ ‹ኅሩይ› የተባለውን ስሜን ትጠራበት ዘንድ ሸልሜሃለሁ» አሉት፤ እርሱም ስሙን በደስታ ተቀበለ።

አባቱ ትምህርት ባለመማራቸው ምክንያት ስድብ ደርሶባቸው ያውቅ ነበርና በእርሳቸው የደረሰው በልጃቸው ላይ እንዳይደርስ ሲሉ ኅሩይን ከልጅነቱ ጀምሮ ትምህርት ላይ እንዲያተኩር አደረጉ። ኅሩይም በተወለደበትና በሌሎች ቦታዎችም በመዘዋወር የንባብ፣ የዜማና የድጓ ትምህርቶችን



ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ

ከዘመኑ ሊቃውንት ተምሯል።

ኅሩይ በእንጦጦ ራጉኤል ደብር የመጽሐፍ ትርጓሜን በሚገባ ተምሮ አጠናቋል። በቀሰመው ትምህርትም በአስተርጓሚነት አገልግሏል። በባሕላዊው ትምህርት የተሟላ እርካታ ማግኘት ያልቻለው ኅሩይ፣ አዲስ አበባ ስዊድን ሚሽን ትምህርት ቤት ገብቶ እንግሊዝኛ ቋንቋ ተምሯል። ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ አረብኛ ቋንቋ ለመማር ጥረት ቢያደርግም «ኅሩይ ሰለመ» የሚል አሉባልታ ስለሰማ ለጊዜው ትምህርቱን ለማቆም ተገዷል። በኋላም ከፈረንሳያውያን ሐኪሞች ፈረንሳይኛ ቋንቋን መማር ችሏል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰነድ ላይ ሰፍሮ እንደሚገኘው፤ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ከ1910 እስከ 1914 ዓ.ም ድረስ የአዲስ አበባ ከንቲባ ሆነው አገልግለዋል። ከንቲባ ከመሆናቸው አስቀድሞ የከተማዋ ሥራ አስኪያጅ ሆነው ሰርተዋል። በከንቲባነት የአገልግሎት ዘመናቸውም ቀደም ሲል በተለያዩ የአስተዳደር ስያሜዎች ይጠራ የነበረውን የከተማውን አስተዳደር «ማዘጋጃ ቤት» ብለው በመሰየም እስካሁን ድረስ የዘለቀ ቋሚ ስያሜ ሰጥተውታል። ብላቴን ጌታ ኅሩይ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደራዊ መዋቅር መልክ እንዲይዝ እንዲሁም በከተማዋ የመሰረተ ልማት ተግባራት እንዲከናወኑ በርካታ ተግባራትን አከናውነዋል።

በዓለም መንግሥታት ማህበር የመጀመሪያው የኢትዮጵያ መልዕክተኛ ቡድን አባል ነበሩ፤ አልጋወራሽ ተፈሪ መኮንን የልዑክ ቡድናቸውን እየመሩ በአውሮፓ ጉብኝት ሲያደርጉ ብላቴን ጌታ ኅሩይም የቡድኑ አባል ሆነው የአውሮፓን ከተሞች ጎብኝተዋል። ይህም የአውሮፓውያንን ባሕል እንዲመለከቱና የወቅቱን የአውሮፓን ስልጣኔና አጠቃላይ ሁኔታም እንዲታዘቡ እድል ፈጥሮላቸዋል።

የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት ብላቴን ጌታ ኅሩይ የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገሥት መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ነበሩ። ለአጭር ጊዜ ቢሆንም ብላቴን ጌታ ኅሩይ በጃፓን የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገሥት መንግሥት አምባሳደር ሆነው ሰርተዋል። በጃፓን የነበራቸው ቆይታ ኢትዮጵያም በቴክኖሎጂ ታግዛ እንደጃፓን ጠንካራና ዘመናዊ እንድትሆን የሚያነሳሳ ምኞት ፈጥሮባቸው ነበር።

ብላቴን ጌታ ኅሩይ «ኢትዮጵያንና ጃፓንን ብዙ የሚያመሳስሏቸው ነገሮች አሉ፤ ስለሆነም ኢትዮጵያ ለዘመናዊነት የጃፓንን አርዓያ ብትከተል ጥሩ ውጤት ታገኝበታለች» ብለው ከሚያምኑትና «ጃፓናይዘርስ/ Japanisers» ተብለው ከሚታወቁት የ20ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ኢትዮጵያውያን ተፅዕኖ ፈጣሪ ምሁራን መካከል አንዱ ነበሩ። ብላቴን ጌታ ኅሩይ ኢትዮጵያና ጃፓን ለበርካታ ዓመታት የዘለቀ ዘውዳዊ የአስተዳደር ሥርዓት ባለቤት እንዲሁም የምዕራባውያንን ተፅዕኖ ተቋቁመው የኖሩ በመሆናቸው አንዳቸው ለሌላቸው አርዓያ የሚሆኑባቸው ብዙ ነገሮች እንዳሉ በጽኑ ያምኑ ነበር። ይህን እሳቤያቸውንም «ማኅደረ ብርሃን ሐገረ ጃፓን» በተሰኘው ስራቸው በዝርዝር አብራርተውታል።

ከማይጨው ጦርነት በኋላ ንጉሰ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ የዲፕሎማሲ ትግል ለማድረግ ወደ ውጭ በተሰደዱበት ወቅት ብላቴን ጌታ ኅሩይም ከኢትዮጵያ ወጡ። ቀዳማዊ አፄ ኃይለስላሴ ፋሺስት ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ ስለፈጸመችው የግፍ ወረራ ጄኔቫ ላይ ለዓለም መንግሥታት ማህበር ሲያስረዱ ኅሩይ ከጎናቸው ነበሩ።

ብላቴን ጌታ ኅሩይ ከመንግሥታዊ ኃላፊነቶቻቸው ባሻገር በደራሲነታቸውም ይታወቃሉ። በርካታ የታሪክ፣ የጉዞ ማስታወሻ፣ የሃይማኖት፣ የልብወለድ፣ የግጥምና የጠቅላላ ዕውቀትን ጨምሮ ከ16 በላይ መጽሐፍትን አበርክተዋል። ከሥራዎቻቸው መካከል «ወዳጄ ልቤ» የሚባለው መጽሐፍ በብዙዎች ዘንድ ታዋቂነትንና ተወዳጅነትን አትርፎላቸዋል።

ብላቴን ጌታ ኅሩይ እንግሊዝን፣ አሜሪካን፣ ቻይናን፣ ፈረንሳይን፣ ኢጣሊያን፣ ግብጽንና ሌሎች ሀገራትን ጎብኝተዋል። የሀገራቸውን ወደኋላ መቅረት ከአውሮፓውያኑ ዘመናዊነት አንፃር ባስተዋሉ ቁጥር ቁጭታቸውን ባገኙት አጋጣሚ ይገልጹ ነበር። በአንድ አጋጣሚ ኢጣሊያን ሲጎበኙ በኢንዱስትሪው አማካኝነት የሚከናወነውን ድንቅ ሥራ ተመልክተው በመደነቅ ተከታዩን ሃሳብ አስፍረው ነበር።

«ለሀገራችን ለኢትዮጵያ የልብስና የእርሻ መኪና የግድ ያስፈልጋል። ኑሯችን ሁሉ ሸማ ለብሰን ነው እንጂ እንደ አውሮፓዎች የበግ ጠጉርና ሐር ዘወትር አንለብስምና ሀገራችን ጥጥ ለማብቀል የተመቸ ነውና ስለዚህ የሸማ መኪና ያስፈልገናል። ምግባችንም እህል ነው እንጂ እንደ አውሮፓዎች ሥጋና ዓሣ አትክልት ሁልጊዜ አናገኝምና ሀገራችንም አሳምሮ እህል ያበቅላልና ስለዚህ የእርሻ መኪና ያስፈልገናል። ይህንንም አስቀድሞ መንግሥት ገዝቶ ፋብሪካውን ቢያቆም መኳንንቱና ያገር ባለፀጎች ሁሉ እንደ ኩባንያ ገንዘብ እያዋጡ አንድ አንድ መኪና እየገዙ ፋብሪካ ያቆሙ ነበር። ከዚህም በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም ያገኙበት ነበር »

በሌላ በኩል ብላቴን ጌታ ኅሩይ ዓለማዊ ችግርን ለመፍታት ዕጣፋንታ ላይ ተስፋ ማድረግ እንደማይገባና ፈጣሪም የሰጠንን ጸጋ የገጠሙንን ችግሮች ለመፍታት ማዋል ሲሳነን እንደሆነ በሚከተለው መልኩ ገልጸዋል።

«እግዚአብሔር ይጠብቀኛል ብሎ ቤት ሳይሠሩ፣ አጥር ሳያጥሩ፣ እህል ሳይዘሩ መንደር ለመንደር ሲዞሩ ቢሞቱ እግዚአብሔርን መፈታተን ነው። ንጉሥም እግዚአብሔር ይጠብቀኛል ብሎ ጋሻ ጦሩን፣ ሰይፉን፣ መድፉንና ጠመንጃውን ሳያዘጋጅ ቢቀመጥ ድንገት ጠላት መጥቶ እርሱን ገድሎ መንግሥቱን ቢወስድበት እግዚአብሔርን መፈታተን ነው። ጉልበታችሁን ተማምናችሁ እግዚአብሔርን አትርሱ»

ለንጉሰ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ የቅርብ አማካሪ በመሆን የሃይማኖትና የአስተዳደር ሕግጋትን እየተረጎሙና የአርትኦት ሥራዎቻቸውን እያጠናቀቁ እንዲወጡ ያደረጉት ታላቁ ዲፕሎማትና ደራሲ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ እንግሊዝ ውስጥ በስደት ላይ ሳሉ፣ መስከረም ዘጠኝ ቀን 1931 ዓ.ም አርፈው ሥርዓተ ቀብራቸው በዚያው እንዲፈፀም ተደረገ። የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር በኢትዮጵያውያን ተሸንፎ ከኢትዮጵያ ምድር ከተባረረ በኋላም በ1940 ዓ.ም አስክሬናቸው ካረፈበት ቦታ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ በመንበረ ፀባኦት ቅድሥት ሥላሴ ካቴድራል እንዲያርፍ በክብር ተድርጓል። በስደት ላይ የነበሩት ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ እንግሊዝ በነበረው የብላቴን ጌታ ኅሩይ ሥርዓተ ቀብር ላይ የሚከተለውን ንግግር አድርገው ነበር።

«አሁን የአዳምን ልጆች ወግ ሲቀበል የምታዩት ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ በሀገራችን ሥርዓት በመልካም አያያዝ ያደገ ከኢትዮጵያም ከፍ ካሉት ሊቃውንት የሚቆጠር ነው። ብልሃቱንና ትጋቱንም ለመልካም ሥራ የሚያገለግሉ መሣሪያዎች ስላደረጋቸው በመንግሥታችን ሥራ ለመመረጥና ወደ ታላቁ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት ለመድረስ በቃ። በየጊዜው የጻፋቸው ከፍተኛ ባህሪውን የሚገልጹ መጻሕፍት፤ ይልቁንም በቤተ-ክህነትና በታሪክ እውቀት በዓለም ሊቃውንት ዘንድ የታወቀና የተከበረ አደረጉት። ለምታውቁት ሰው ከታሪኩ ከዚህ የበለጠ ልነግራችሁ የሚያስፈልግ አልመሰለኝም። በአጭሩ ከጠባዩ ትልቅነት የሚሰማኝን ለመናገር ሳስብ ጊዜውን ሁሉ ቁም ነገር በመሥራት ማሳለፉ፤ ከራሱ ይልቅ የተቸገሩትን ለመርዳት መጣሩ፤ እውነትን፣ ፍርድንም ማክበሩና በሀገር ፍቅር መቃጠሉ ትዝ ይሉኛል።

አገልጋዬና ወዳጄ ኅሩይ! በተቻለህ ስለሀገርህ ሥራህን በሚገባ ፈጽመህ በምትሰናበትበት ጊዜ ታላቅ ነህ ሳልልህ ብቀር ሥራዎችህ ቀድመውኝ ይናገራሉ። በክፉ አድራጊዎች የሚገፋ የዓለምን ፀጥታ የሚያናውጥ ነፋስ ምንም ቢያንገላታህና በታላቅ ፈተና ላይ ቢጥልህም ሊያሸንፍ አልቻለም። ታላቅና ቸር በሆነው ጌታ በተመደበው ሕግ ግን መታዘዝ ግድ ሆነብህ። ይህም ለእያንዳንዳችን የሚደርሰን ዕድል ነው። አንተም እስከ መጨረሻ ከታገልክ በኋላ ዛሬ ደከመህ፣ አንቀላፋህም። በሥጋ ብትለየንም ስምህና ሥራህ በመካከላችን ይኖራሉ።

ኅሩይ፣ እግዚአብሔር ሲያስበን አጥንቶችህና መንፈስህ የሚሰፍሩበትን ቦታ እስኪያዩና ከአባቶችህ እስኪቀላቀሉ ድረስ በእንግድነት በመጣህበት በዚህ ሥፍራ በሰላም ዕረፍ።»

ብላቴን ጌታ ኅሩይ ከወይዘሮ ሐመረ እሸቴ ጋር ጋብቻ መስርተው ስድስት ልጆችን አፍርተዋል፤ ብዙ የልጅ ልጆችንም ለማየት በቅተዋል። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበር ከኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት ጋር በመተባበር ጳጉሜን ሁለት ቀን 2004 ዓ.ም በአዲስ አበባ ቴአትርና ባህል አዳራሽ የአራት ቀደምት ደራሲያንን ምስል የያዙ ቴምብሮች አስመርቆ ገበያ ላይ ሲያውል ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ምስላቸው በቴምብር ላይ ከታተሙላቸው ደራሲያን መካከል አንዱ ነበሩ። ጉለሌ የሚገኘው የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚም ያስገነባውን የስነ ጥበባት ማዕከል በስማቸው እንዲጠራ አድርጓል። የሕይወት ታሪካቸው «የብላቴን ጌታ ህሩይ ወልደ ሥላሴ ታሪክ  1871 - 1931 ዓ.ም» በሚል ርዕስ በኤመሪተስ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ ተዘጋጅቶ ታትሟል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

## ያልተወሳው የጥበብ ሰው

ሙሉጌታ ብርሃኑ

“በሉ እንጂ በሉ እንጂ…”ን ላቀነቀነችው አበበች ደራራ፤ ምን እንበል? ብለን ብንጠይቅ በወደድን ነበር። ነገር ግን ለማለቱ ቃላቶቹ ያጥሩናል። እንዲህ ላስባላት ድንቅ ሰው ግን በቃላቱ እጥረት መካከልም እያሳሳብንም ቢሆን ላልተወሳው እናውሳለት። ሠርቶ ሠርቶ ያልተወሳው አሳዬ ዘገየ…ጥላሁን ገሠሠ በህይወት ኖሮ እስቲ ጥቂት በልለት ቢሉት፤ ከአበበች ደራራ ጆሮ ጢጋ ብለው እንዲያው ስለ እርሱ ቢጠይቋት፣ ማርታ ሀይሉንም ቢሆን ቀርበው አሳዬን በመልካም እንማው ያሏት እንደሆን… ሁሉም እንዴት ባሉ ወለላ ቃላት እያሽሞነሞኑ እንደ ማር ከአንደበታቸው ጠብ! ጠብ! እያደረጉ ባጣፈጡለት ነበር።

ማርን የሚሰጠው አበባዋን የቀሰመ ንብ ነውና ከእርሱ ጥበብ ውብ የሆነውን ያገኙ ሁሉ ስለ እሱ አጣፍጠው መናገራቸው የማይቀር ነበር። በሀገራችን የሙዚቃ ኢንዱስትሪ ውስጥ አይጠበቡ ተጠበው ጥዑም የሙዚቃ እንኮይ ካረገፉልን የሙዚቃ ግጥምና ዜማ ደራሲያን አንደኛውና ከግንባር ከተሰለፉት መካከል አሳዬ ዘገየ አለበት። ከ47 ዓመታት በላይ በሙዚቃ ዓለም ውስጥ ሰንብቶ ዛሬም አልተለየም። በቁጥር ከሰፈሩት 3 መቶ ያህል የግጥምና ዜማ ሥራዎችን አድሏል።

ነገሩ መች ግጥምና ዜማ ብቻ ሆነና ብዙዎች ጆሯቸውን ቀጥ አድርገው እስኪያቆሙለት ድረስ በክራርና በኪቦርድ አጫዋወቱ ሸክፎ ይዟቸዋል። ወንበር ስቦ ከኪቦርዱ ላይ ያሉትን ባለ ነጫጭና ጥቋቁር ቁልፎችን መነካካት ሲጀምር ገና ጆሮ እንደቆመ ልብ ያስፈንድቃል። የክራሩ ጅማቶች ለመናዘር ግርፉን የሚጠብቁ እንኳን አይመስሉም። የክብሪት እሳት እንዳገኘው ሰንደል እየጨሱ ቡልል! ማለት ብቻ።

አሳዬ ዘገየን ያበቀለች የጎጃሟ የወርቅ አፈር ግሽ ዓባይ ናት። በተንጣለለው የጣና ሀይቅ፣ በሚያረሰርሰው የዓባይ ወንዝ ለምልሞ ያሸተውን የጥበብ አዝመራ እያሸና እየጠረጠረ የበላባት መነሻ ሀረጉ ናት። ከጎጃም ምድር አልፎ በመላው ሀገሪቱ የኪነጥ ጥበብ በተለይም ደግሞ የሙዚቃ ደጀን የሆኑትን ሲያመርት የነበረውን “የጎጃም ግሽ ዓባይ የባህል ኪነት” ቡድንን አቋቁመው ለወግ ማዕረግ ካደረሱት አባላት መካከል አሳዬ ግንባር ቀደሙ ነው። ኪነትን ቡድኑን ከመሠረቱት በኋላ በጎጃም ክፍለ ሀገር ከነበሩት ሰባት የኪነት ቡድኖች ጋር ተፎካካሪ በማድረግ በየዓመቱ ሲያካሂዱት በነበረው ውድድር ላይ ጎልቶ እንዲታይ አድርገውታል። የግሽ ዓባይ ፍሬ የሆነው አሳዬም ኋላ በ1970ዎቹ አጋማሽ ላይ ውድድሩን በዳኝነት ሲመራ ነበር።

በትውልድ ቀዬው ውስጥ ሆኖ ድንቅ ችሎታውን እያጎመራ በየመድረኮቹ ላይ ከልብ ከሚጨበጨብላቸው አንዱ ሆነ። ከዚያ እየቀጠለ ግን በመሀል ሾልኮ ውስጣዊ የሙዚቃ ጓዙን በመሸከፍ አዲስ አበባ ገባ። ብዙዎች ዛሬ ላይ ሆነው የትናንቱን አሳዬን ሲያስታውሱ በምናባዊ ምስል ድቅን ከሚልባቸው ስፍራዎች አንዱ ከሀገር ፍቅር ቲያትር ቤት ጀርባ የነበረው “ግራር” የምሽት ክበብ ነው። ጸሐይ ጠልቃ ጀንበር ስታዘቀዝቅ ወደዚህ ቤት የሚገሰገሰው ኮቴ ብዙ ነው። ሲሮጥ የመጣ ተጋፍቶ ቦታ ይዞ ከሚጠባበቃቸው ነገሮች አንዱ አሳዬ ከነሙዚቃ መሳሪያው መድረክ በድምጽ እያዜመ ሲጫወት መመልከት ነው። ጸጉሩን አጎፍሮ፣ በቄንጥ አለባበሱ ሽክ ብሎ ቦግ እልም እያለ ከሚያሸበርቀው የመድረክ መብራት ፊት ሲቆም ብቻውን ደስ የሚያሰኝ ነገር አለው። የሙዚቃ መሳሪያውን በአንገቱ እንዳነገተ ገረፍ! ገረፍ! እያደረገ ጭንቅላቱን ወዝወዝ፣ ወገቡን እንቅጥቅጥ! እግሮቹን ፍትግትግ! ሽክርር! ሲያደርጋቸው ከአለባበሱ ጋር የተመለከተው፤ ቁርጥ ማይክል ጃክሰንን ይሉታል።

ድምጹም ቢሆን ጣዕሙ የከረሜላ ነው። በድምጽ እያቀነቀነ የሙዚቃ መሳሪያዎቹን ራሱ ሲጫወታቸው መመልከት፤ አንድ ሰው ሳይሆን ለብቻው አንድ ሙሉ ባንድ ነው ያስብላል። ጥፍጥ



አሳዬ ዘገየ

ብሎ ከሚደመጠው ክራሩ ጀምሮ ከባህላዊ ቢሉ ከዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ጋር ያለው ቁርኝት የሚለይ ነው። እኔ ባለክራር አሊያም ኪቦርዲስት ነኝ ብሎ ራሱን ከየትኛው ጋር አይገድበውም። ምን ይሁን ምን ከተመለከተው የሙዚቃ መሳሪያ ሁሉ ጢጋ ብሎ በፍቅር ማውጋቱን አይተውም። መሀላቸው ቆሞ በመሀላ ያስተሳሰራቸው ማንና እንዴት እንደሆነ ራሱም በውል ባያውቀውም ከመሳሪያዎቹ ጋር ያለው የማይፈርስ ግንኙነት ግን አስደናቂ ነው። የሚፈልጋቸውን ያህል ፈልገው፣ የሚወዳቸውን ያህል የሚወዱት መሆኑ አይጠረጠርም። የያዛት ማሲንቆ ማጫወቻዋን ጢጋ አድርጎ ሊገዘግዛት ባለ ቅጽበት ፀሐይን የሚያስንቅ የፈገግታ ጥርሷን ወከክ አድርጋ ትስቅለታለች። አርሞኒካዋማ እንደ ጉብል ልጃገረድ ስትሽኮረመም ከእርሱ አልፎ አጠገብ ያለውን ልብ ሁሉ ታቀልጣለች። አኮርዲዮኑ ከሰውነቱ ደገፍ ሲል ገና በግርማ ሞገስ ከሚንቆረቆረው ድምጽ ሰፈፍ! እያለ ለጆሮ ምቾትን ለልብ እርካታን ያወርዳል። ሲደባብሳቸው እየቦረቁ ከሪትሙ ጋር አብረው ከአምባሰል እስከ ባቲ የሚነጥሩት ነጫጮቹና ጥቋቁር ሻርፖቹ የኪቦርድ ቁልፎች በስምንቱም አኪታሮች ሽብሻቦ ይጀምራሉ። የዋሽንቱ ዜማም እንኳን ሰው አዕዋፋትን ከሰማይ የሚጠራ ነው። ከሁሉም በላይ ግን፤ በነካካት ቁጥር አጸፋዊ የስሜት ንዝረት የምታከታትለዋ ክራሩ…ጅማቷ ከደም ስሩ ላይ የተመዘዘች እስክትመስል ራሱም በስሜት ይነሆልልባታል። ሲቀርቡትና ሲቀርባቸው ሁሌም እንደዚህ ነው።

ታላቁ ሰው ከታላላቆቹ ማጀት ውስጥ አሰናድቶ የሰጣቸው እጅግ በርካቶች ናቸው። ከእነዚህም መካከል ጥቂቱን ጠቃቅሰን ስናልፍ የምናገኘው አንድም የክብር ዶክተር አርቲስት ጥላሁን ገሠሠን ነው። ከጊዜያት በአንደኛው ጊዜ፤ አሳዬ አንድ ግጥምና ዜማ ሠራ። መቼም ደስ ይለዋል ሲል በልቡ እየተፍነከነከ ይዞት ወደ ጥላሁን ገሠሠ ገሰገሰ። ከጥላሁን ዘንድ እንደደረሰም የሠራለትን ሙዚቃ በኩራት አቀረበለት። ጥላሁን ሙዚቃውን አደመጠውና “አይ…” አለ። አልመስልህ ስላለው ይቅርብኝ ሲል ግጥምና ዜማውን መለሰው። ለአሳዬ ያልጠበቀው ምላሽ ነበር። ፊቱን መልሶም ወደ ተሾመ ወልዴ በማቅናት የሠራውን ሥራ አስደመጠው። ተሾመ ግን ሙዚቃው ደስ የሚል ስሜት ስለሰጠው ሊሠራው ቆርጦ ተነሳ። ሙዚቃውም እንዲህ የሚለው ነበር…

**—መጀመሪያ ማወቅ መተዋወቅ**
**ቀስ ብሎ በፍቅር መሳሳቅ**
**ሲይዝ አይታወቅ ልብ ሲሰርቅ**
**እንዲህ ያደርጋል ፍቅር ወይ ፍቅር“**

በዚህ ሙዚቃ የጥላሁን ገሠሠ ፍራቻ እንዳሰበው ሳይሆን ቀርቶ የተሾመ ቤት መታ። ከተሠራ በኋላ ምን ተወደደ ብቻ አይሉት፤ ገጠር ከተማውን ከጫፍ ጫፍ አዳርሷል ፈንደቅደቅ ተባለበት። ይህን ጊዜ ጥላሁን ምን እንደተሰማው ባይሰማም አሳዬ ለጥላሁን ገሠሠ የሰጠውን “ጉብል” የተሰኘውን ሌላኛውን ሙዚቃ ግን ከድምጸ ስርቅርቁ አንደበት ሰምተነዋል። ተሾመ ግን ከአጃቢ መካከል ከነበሩት ከበዛወርቅ አስፋውና ብፅአት ጋር ደመቅመቅ ብሎ ታየበት። በርከት ያሉ ጣዕመ ዜማዎች ባለቤት የሆነው ተሾመ ወልዴ በዚህኛው ግን ከመታወቁም በላይ የዝናን እርካብ የረገጠበት ነበር። ያልተወሳውን ሰው የሚያወሳው ድንቅ የሙዚቃ አልበም ከድምጻዊቷ ማርታ ሀይሉ ጋር ይተሳሰራል።

“ከረሜላዬ”ንና አዲስ አበባ ሆና የአስመራውን ሽጋ የምትናፍቅበት “ሀብ አስመራ”ን አካቶ በወጣው የማርታ ሀይሉ የመጀመሪያ አልበም ውስጥ አስሩንም ሙዚቃዎች ጥንቅቅ አድርጎ የቀመመላት አሳዬ ዘገየ ነው። ሙዚቃን በጆሮ ብቻ ሳይሆን በልብም ጭምር የሚያደምጡ የሙዚቃ አፍቃሪያን ሙሉ አልበሙን ከአንጀታቸው ይወዱታል። “ሸበል ዓለም”፣ “ብራ ነው ብራ ነው” በማለት “ና ጋሜ” ሲሉ “ርሀቤን ጥማቴን” በእርካታ ለወጡት የሚያሰኙ ናቸው። ሌላኛው የአበበች ደራራ “በሉ እንጂ” ደግሞ ለአሳዬ በሉለት እንጂ እያለ አስቁሞ የሚያስጨበጭብለት ሥራ ነው። ከዕለታት በአንዱ ቀን ላይ አሳዬና ወዳጆቹ ብርጭቆ ጨብጠው ሲዝናኑ ነበር… በጣቶቹ አንቆ ጎንጨት ሊያደርግባት ወደ አፉ ካስጠጋት ብርጭቆ ውስጥ “በሉ እንጂ በሉ እንጂ” እያለ ሽብልቅልቅ! ከሚለው ጥልቅ ባህር ውስጥ ብቅ ጥልቅ የምትል አንዲት አሳ የተመለከተ መሰለው። ድንገት ከምናቡ ላይ ቅጭል! ያለችውን የዜማ አሳ ሳትሰምጥበት በፊት ቶሎ ብሎ በመንጠቆው ደጋገማት። ያጠመዳትን ዘሜ እየተከተለም እዚያው ቁጭ ብሎ ግጥሟንም ይጽፋት ጀመረ። አብረውት ላሉት ሲያሰማቸው እጅግ ጥፍጥ ያለ ጅምር እንጎቻ ነበር። አጣፍጦ ያዘጋጃትን የአሳ ጥብስ በእንጎቻዋ ጠቅልሎ የሚያጎርሰውን ድምጻዊ ፍለጋ ወጣ። ከሃሳቡ የመጣችለት ጸሀይ እንዳለ ነበረች። በቀጥታ ወደ ብሔራዊ ቲያትር አቀና።

ሙዚቃውን ሊሰጣት በተዘጋጀበት ሰዓት ግን ተወዛዋዡ የነበረችው ፋንትሽ በቀለ ስትናጎራጉረው ድንገት ሰማት። የሰማው ድምጽ ለጸሀይ የመስጠቱን ሃሳብ አስለወጠው። “በቃ አንቺ ነሽ የምትዘፍኚው” አላት። ፋንትሽ ከዚህ ቀደም መወዛወዙን እንጂ ድምጻዊነቱን ሞክራውም ስለማታውቅ “እንዴት ብሎ ማን ይፈቅድልኛል…” ስትል ፍላጎቷ ውስጥ ጥርጣሬ ገባ። ሙዚቃውን የሠራሁት እኔ ነኝና ወስኛለሁ ሲል ቁርጥ አድርጎ ነገራት። ፋንትሽም ለመጀመሪያ ጊዜዋ መድረክ ላይ ወጥታ “በሉ እንጂን” አቀነቀነች። ግሩም አድርጋ በማቅረብ ሙዚቃውም እርሷም ከመወደዳቸውም የድምጻዊነትን ጎህ የቀደደላት ሥራ ነበር። በመድረኩ የኮራባት አሳዬም በሌላ ጊዜ ሌላ ሙዚቃ ሠራላት። በሉ እንጂንም ተቀብሎ ለአበበች ደራራ አልበም ካሰናዳቸው ሌሎች ሥራዎቹ ጋር ቀላቀለው። አበበች ደራራም በሉ እንጂን ሌላ ከፍታ ላይ አድርሳው ከስሟ ቀጥሎ መታወቂያዋ እስከመሆን ደረሰ። መታወቂያ በመሥራት አበበች ብቸኛው አይደለችም። ስዩም ዘውዴን ስናስበው ቀድሞ ብልጭ! የሚልልን “ጢጋ በይኝ ጢጋ”ን የተሸከመው ሳዱላዬ ነው። “ሰው አለኝ” የተሰኘው ለስለስ ያለ ነፋሻማ ሙዚቃም ከጣዕመ ዜማው ጋር ሀና ሸንቁጤን እንድንወዳት ያስገድደናል። ፋንትሽ በቀለ “አንተ ልጅ ወድጄህ ነው” ከምትለዋ ልብ አቅላጭ ሙዚቃ ጋር ያወጣችውን አልበም የሠሩት አሳዬና ንዋይ ደበበ ነበሩ። በዚህ አልበም ውስጥ ያዋጣው ከግማሽ በላይ የሆነ የጥበብ ድርሻ አለው። ሀመልማል አባተን ጨምሮ በወርቃማው ዘመን ነበሩ ከምንላቸው ጋር የአሳዬን ስም ማንሳት እንጀምረው ይሆናል እንጂ አንጨርሰውም።

አሳዬ በሀገር ውስጥ ዝነኝነቱ እየበረታበት፣ ከፍ ከፍ እያለ መብረር በጀመረበት ጊዜ ከሀገር የመውጣት ሃሳብ አቃጭሎበት መሹለኪያዋን ቀዳዳ ፍለጋ ወደ ጎረቤት ኬንያ ገባ። ጥቂት ከዚያ ከቆየ በኋላም የካናዳውን ነገር አመቻችቶ ለስደት እብስ አለ። ወደ ካናዳ የሚገባበትን መንገድና ጥበቡን ሲመክር ሲያስጠናው የነበረው ሰው ደግሞ አንጋፋው ሙዚቀኛ አለማየሁ እሸቴ ነበር። ዳሩ ለካናዳው ብቻም ሳይሆን በሙዚቃ ህይወቱም ብርሃን ከጨለማ ለይቶ በመልካም የሚጓዝበትን ስንቅ ያሰነቀው መሪውም ጭምር ነው። አሳዬ ካናዳ ደርሶ ከተቀበለው ሰውና ካረፈበት ቤት ውስጥ አንድ እውቅና መልህቅ የሆነ ዓለም አቀፍ አቀንቃኝ ወጥቶበታል። ያን ጊዜ የተቀበለው ሰው የዝነኛው አቤል ተስፋዬ( ዘ ዊኬንድ) አባት ሲሆን፤ ከአመት በላይ ከቤታቸው ኖሯል። አቤል ተስፋዬ ጊታሩን ይዞ የሙዚቃን ዱካና አሻራ ሲፈልግ ያን ጊዜ አሳዬ አጠገቡ ነበር። እጁን ይዞ በመምህርነት ባይገራውም ትንሹ አቤል አሳዬን እየተመለከተ የቀሳሰመው ዕውቀትና ጥበብ የለም ለማለት ግን አይቻልም።

ወደ ካናዳ ሲገባ ዘለግ ቢል ለዓመት እንጂ ከዚያ በላይ የመኖር እቅድ አልነበረውም። ነገር ግን እንደዋዛ 2 ዓመታት ሞሉት። አሁንም ነገ ዛሬ ሲል፣ ሲያስብ ሲያሰላስል ድንገት በትዳር ገመድ ተጠለፈ። እያለም ከካናዳ ወደ አሜሪካ ገባ። አሁንም ልቡ ሳይረግጥ ልጅ መጣ። የራሱንም ዘመናዊ የምሽት ቤት ከፈተ። ከዚያ በኋላ ግን ሥራ ያውጣህ ሲል የመምጣት ሃሳቡን ተወት አድርጎ ዲሲ ሙዚቃን ከዚያው አጥብቆ ያዘ። በአሜሪካን ዲሲ ከተማ ውስጥ “ደመራ” የተሰኘ ባንድ ውስጥ ከብዙ ታላላቅ ሙዚቀኞች ጋር አብረው መሥራት ጀመረ። ከአስፋ ደባልቄ፣ አበጋዝ ክብረወርቅ፣ ቴዲ ማክ እና ከሌሎችም ጋር በተለያዩ ጊዜያት አብሮ ሠርቷል። በዲሲ በነበረው ቆይታው ብቻ ከ150 በላይ ዝግጅቶች ላይ አሻራውን አኑሯል። በወቅቱ በዋናነት ያቀርቡ የነበረው ለነጮቹ በመሆኑ የኢትዮጵያ ሙዚቃ በአሜሪካ ውስጥ እንዲታወቅ ቀላል የማይባል ሚና ተጫውቷል። በዚህ ላይ ደግሞ አሳዬ በየዝግጅቶች የኢትዮጵያን የባህል ሙዚቃዎች በተጫወተ ቁጥር የሚታየው ሙዚቃውን ከሚመስሉ የባህል አልባሳት ጋር ነው። ሙዚቃውን ብቻ ሳይሆን ባህልን በማስተዋወቅ ምስጉን ነው።

አሳዬ በሙዚቃ ህይወቱ ሙዚቃን ከመሥራት ጎን ለጎን የሚነገርለት ሁለት አዳዲስ ነገሮች አሉት። የመጀመሪያው በቆዳ ተወጥሮ ሲሠራ የነበረው የክራር ክር ወደ ዘመናዊ አውታር በመቀየር ከጊታር ድምጸት ጋር በመቀየጥ ልዩ የዜማ ጦማር ለማምጣት በተደረገ ፈጠራ ውስጥ ስሙ ይነሳል። ሁለተኛው ደግሞ መድረክ ላይ ነው። በመድረክ የሙዚቃ ዝግጅቶች ላይ ቀደም ሲል የሚታወቀውና የተለመደው አንድ ድምጻዊ መድረክ ከወጣ በኋላ አንዲት ሙዚቃ አቀንቅኖ መውረድ ነበር። አሳዬ ይህን ልምድ በመለወጥ አንድ ድምጻዊ የተዘጋጃቸውን ልዩ ልዩ ሙዚቃዎችን አከታትሎና ቀጣጥሎ መጫወት እንዲችል አደረገ። በተመሳሳይ የሪትም ምት የሚገኙ የተለያዩ ሙዚቃዎችን ቀላቅሎ መጫወቱ የበለጠ የማዝናናት አቅም ስላለው ተወደደ በዚያው ልማድ ሆኖ ቀጠለ። ብዙ ጊዜ እንደምንለው ሁሉ የኛ የጥበብ ተቀባዮች ሠሪን ያለማውሳት ልምድም እንደጦፈ ነው። በመጥፎ አባዜው ላይ የብዙ የጥበብ ሰዎች ከሀገር ወጥቶ፣ ከሕዝብ ርቆ መኖር ደግሞ “በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ” ነው። ከሀገር እንደወጣ ረዥም ዓመታትን ከዚያው ለከተመው አሳዬም እጣ ፈንታው ይሄው ሆኗል።

ያልታወሰውን የሙዚቃ ፈርጥ ስናስታውስ ብዙ የህይወትና የኑሮ ውጣውረዶች ላይ ሲያዳልጠው ሲንሸራተት፣ ሲወድቅ ሲነሳ ዛሬም ድረስ አለ። ልቡ ተሰብሮ በጣሙን የተጎዳበትን ጊዜ ብንጠይቀው ኖሮ 2012ዓ.ም እንደሚጠቅስልን እሙን ነው። የዛሬ አራት ዓመታት ገደማ እጅግ የሚሳሳለት የ22 ዓመት ወንድ ልጁ በድንገት ሞቶ ተገኘ። ድንገቴ የሞት አውሎ ንፋስ ልጁን የነጠቀበት አስከፊ ጊዜው ነበር። ህይወት መዝገቧ ተገልጦ አያልቅምና ግን አሁን ደህና ነው…በሙዚቃ ጉዞው 50 ዓመታትን ደፍኖ ልዩዋን የኢዮቤልዩ ኒሻን ለማጥለቅ የቀረው ሁለት ዓመታት ብቻ ናቸው። እንደገና ሌላ ትውስታ…

# ዓለም አቀፍ

## በማሊ ዋና ከተማ ታጣቂዎች በፈጸሙት ጥቃት 70 ሰዎች ተገደሉ

በማሊ ዋና ከተማ ከአልቃይዳ ጋር ግንኙነት አላቸው የተባሉ ታጣቂ ቡድኖች በዚህ ሳምንት በፈጸሟቸው ጥቃቶች 70 ሰዎች መገደላቸው ተገለጸ፡፡ ላለፉት አስርተ ዓመታት በተደጋጋሚ በሚከሰቱ የሽብር ጥቃቶች ጉዳት እያስተናገደች የምትገኘው ምዕራብ አፍሪካዊቷ ሀገር በዚህ ሳምንትም መጠኑ ከፍ ያለ ጥቃት ደርሶባታል፡፡

በዋና ከተማዋ ባማኮ ተፈጽሟል የተባለው ጥቃት የፖሊስ ማሠልጠኛ ተቋም እና የሀገሪቱ አየር መንገድ ላይ ያነጣጠረ ነው፡፡ ታጣቂ ቡድኖቹ ይህን ጥቃት የፈጸሙት በማዕከላዊ የሀገሪቷ ክፍል ጭምር የትኛውንም አይነት የሽብር ተልዕኮ ማሳካት እንደሚችሉ ለማሳየት ነው ተብሏል፡፡

የሀገሪቱን መንግሥት በመፈንቅለ መንግሥት አስወግዶ እየመራ የሚገኘው ወታደራዊው አስተዳደር በማሊ የሚገኘው የጸጥታ እና ደህንነት ጉዳይ እየተሻሻለ እንደሚገኝ ተደጋጋሚ መግለጫዎችን እንደሚሰጥ ይታወቃል፡፡ ወታደራዊ አስተዳደሩ የፈረንሳይ እና የአሜሪካ ወታደሮችን ከሀገር እንዲወጡ ካደረገ በኋላ ፊቱን ወደ ሩስያ አዞሯል፡፡

ሽብርተኞችን ለመዋጋት በሚደረገው ጥረት የሩስያ ቅጥር ወታደር ቡድን ዋግነር ባሳለፍነው ሀምሌ በርካታ ቁጥር ያላቸው ወታደሮቹ በማሊ እንደተገደሉበት መዘገቡ ይታወሳል፡፡ ከሰሞኑ የተከሰተውን ጥቃት ተከትሎ አስተዳደሩ የሟቾችን ቁጥር ይፋ ባያደርግም ሮይተርስ ከዲፕሎማቲክ ምንጮች አገኘሁት ባለው መረጃ ወደ 70 የሚጠጉ ሰዎች መሞታቸውን ዘግቧል፡፡

በጥቃቱ ከሞቱት ሰዎች በተጨማሪ ጉዳት የደረሰባቸው ቁጥራቸው በውል ያልታወቁ ሰዎች በሆስፒታል የህክምና ክትትል እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ የማሊ ጋዜጦች በበኩላቸው በጥቃቱ የተገደሉ 50 የፖሊስ ሠልጣኞች ሥርዓተ ቀብር አርብ እለት መፈጸሙን ዘግበዋል፡፡

የማሊ ወታደራዊ አስተዳደር ከታጣቂዎች እና ሽብርተኞች ጋር በገባበት ውግያ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ሲገደሉ ሚሊዮኖች ከቀያቸው መፈናቀላቸውን አል ዐይን ዘግቧል፡፡





## ወደ ሰሜን ኮሪያ በመሸሽ እስር ተፈርዶበት የነበረው የአሜሪካ ወታደር ተለቀቀ

ባለፈው ዓመት ከደቡብ ኮሪያ ወደ ሰሜን ኮሪያ በሕገ ወጥ መንገድ አቋርጦ በመግባት የአንድ ዓመት እስር ተፈርዶበት የነበረው የአሜሪካ ወታደር ከእስር ተለቀቀ። ትሬቪስ ኪንግ የተባለው ወታደር ወደ ሰሜን ኮሪያ ከሸሸ በኋላ ወደ አሜሪካ እንዲመለስ ተደርጎ ነበር። ትሬቪስ በጦር ክህደት እና የጦር መኮንን ላይ ጥቃት በማድረስ ክስ የተመሠረተበት ባለፈው ዓመት ሐምሌ ወር ላይ ነው።

ሆኖም የቁም እስሩን ጊዜ በማጠናቀቁ እና በዚህ ጊዜ ባሳየው መልካም ሥነ ምግባር ምክንያት የ24 ዓመቱ ኪንግ ነጻ እንዲወጣ መደረጉን ጠበቆቹ ተናግረዋል። ኪንግ አርብ ዕለት በቴክሳስ ፎርት ብሊስ በተካሄደው ችሎት ከተመሠረቱበት 14 ወታደራዊ ክሶች መካከል በአምስቱ ጥፋተኛ መሆኑን ያመነ ሲሆን ሌሎቹ ውድቅ ተደርገዋል።

በችሎቱ ላይ ኪንግ ለጦሩ ዳኛ ሌተናንት ኮሎኔል ሪክ ማቴው፣ የአሜሪካን ጦር ጥሎ ለመውጣት የወሰነው "በሥራው ባለመርካቱ" እንደሆነ እና ወደ ሰሜን ኮሪያ ከመሸሹ አንድ ዓመት በፊት ጥሎ ለመውጣት ሲያስብ እንደነበር ተናግሯል። በችሎቱ ተገኝተው እንደዘገቡት ጋዜጠኞች ከሆነም "ከአሜሪካ ጦር መውጣት እና አለመመለስ እፈልግ ነበር" ብሏል ኪንግ።

ከዚህም በተጨማሪ ምንም እንኳን ችሎት ለመቅረብ እና ክሶቹን ለመረዳት ብቁ ቢሆንም የአዕምሮ ጤና ችግር እንዳለበት ለፍርድ ቤቱ አስረድቷል። የኪንግ ጠበቃ ፍራንክሊን ሮሰንብላት በመግለጫቸው እንዳሉት ደንበኛቸው ለተፈጠረው ክስተት ሙሉ ኃላፊነቱን መውሰዱን ገልጸው፣ ኪንግ የልጅነት አስተዳደጉ፣ ወንጀል በሚፈፀምበት አካባቢ ማደጉ እና የአዕምሮ ጤና ችግርን ጨምሮ በሕይወቱ ከባድ ፈተናዎች እንደገጠሙት አውስተዋል።

"እነዚህ ችግሮችም በጦሩ ውስጥ ያለውን ፈተና እንዳይቋቋም አድርገውታል" ብለዋል ጠበቃ ሮሰንብላት። ኪንግ የአሜሪካ ጦር ሠራዊትን የተቀላቀለው በአውሮፓውያኑ 2021 ሲሆን ደቡብ ኮሪያ ያለው ካምፕ ውስጥ ነበር። ወደ ሰሜን ኮሪያ የተሻገረውም ከባድ ጥበቃ በሚደረግለት እና በሰሜን እና ደቡብ ኮሪያ መካከል ባለ ነጻ ቀጣና በምትገኘው ፓንሙንጆም መንደር ጎብኚዎችን በመቀላቀል በሕገ ወጥ መንገድ ነው።

ኪንግ ቀደም ብሎ ሁለት ሰዎችን በመሳደብ እና የፖሊስ መኪናን በመምታት ወንጀል በደቡብ ኮሪያ እስር ቤት ወደ ሁለት ወር ለሚጠጋ ጊዜ ታስሮ ተለቅቋል ። በወቅቱ የአሜሪካ ባለሥልጣናት፣ በተደረገ “ጠንካራ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት” ከሁለት ወራት እስር በኋላ መለቀቁንና በደቡብ ኮሪያ ወደሚገኘው የአሜሪካ አየር ኃይል ሰፈር በአውሮፕላን መወሰዱን አስታውቀዋል። ከዚያም እአአ መስከረም 28 /2023 ወደ ቴክሳስ ተወስዷል ሲል የዘገባው ቢቢሲ ነው።


# ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ባለው ክፍት የስራ ቦታ በህግ ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪና ከዚያ በለይ ያለቸውን በዜሮ አመት የስራ ልምድ እና ከአምት አመት ባለይ የስራ ለምድ ያላቸውን ሙያተኞች አወዳድሮ መቅጠር ስለሚፈልግ ተወዳደሪዎች ይህማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ልደታ ክፍለከተማ ወረዳ 10 ሜክሲኮ መይጨው ክልኒክ ጀርባ በሚገኘው ፍትህ ቢሮ አቃበያነ ህግ ጉባኤ 5ኛ ፎቅ በአካል ወይንም ህጋዊ ወኪሎቻቸው አመካኝነት መመዝገብ ይችላሉ፡፡

መመዝገቢያ መስፈርቶች

1ኛ ኢትዮጵያዊ የሆነች/ የሆነ በኢትዮጵያ የሚኖር

2ኛ ለህገመንግስቱና ለህግ የበላይነት ተገዥ ሆነ

3ኛ የየትኛውም ፖለቲካ ድርጅት አባል ያልሆነ/ች እና ወንጀል ቅጣት የሌለበት፡፡

4ኛ በታታሪነቱ/ቷ/ በስነምግባሩ/ሯ/ መልካም ስምተረፈ/ች /ማስረጃ ማቅረብ ሚችል /የምትችል/

5ኛ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋም በህግ ትምህረት የመጀመሪ ዲግሪና ከዚያ በለይ የጠመረቀ /ች/

6ኛ የስራ ልምድ ዜሮ አመት በ2015 እና በ2016 የትምህርት ዘመን ተመራቂ ሆነው የመውጫ ፈተና ወስደው ያለፉ ለወንዶች የመመረቂያ ነጥባቸው 3.5 እና ከዚያ በላይ ለሴቶችና ለአከል ጉዳተኞች 3.25 እና ከዚያ በላይ

7ኛ ተፈላጊ የሰው ብዛት/ 15/ አስራ አምስት

8ኛ ከአምስት ዓመት በላይ የስራ ልመድ ላላቸው በአቃቤ ህግነት፣ በዳኝነት፣ በህግ ምርምር፣ በመምህርነት እና በተመራማሪነት ያገለገለ /ች/ እንዲወዳደሩ ይጋብዛል፡፡

9ኛ ተፈለጊ የሰው ብዛት ከአምስት ዓመት በላይ ላገለገሉ10/አስር/

10ኛ ደመወዝ በተቋሙ ስኬል መሰረት

11ኛ የስራ ቦታ ቢሮው በሚሰጠው ምደባ ቦታ፣


ተመዝጋቢዎች /ተወዳዳሪዎች/ ለምዝገባ ሲመጡ ሊያሟሏቸው የሚገቡ ሰነዶች ኢትዮጲያዊ መሆናቸውን ሚገልፅ መታወቂያ ፓስፖርት የትምህረት ማስረጃቸውን ዋና ከማይመለስ ፎቶ ኮፒ ጋር ከምትኖሩበት አካባቢ አግባብነት ካለው አካላት የተፃፈ የስነ ምግባር ማስረጃ ፣

የምዝገባ ቦታ ልደታ ክፍለከተማ ወረዳ 10 ሜክሲኮ በሚገኘው ፍትህ ቢሮ አቃበያና ህግ ጉባኤ 5ኛ ፎቅ በአካል ወይንም ህጋዊ ወኪሎቻቸው አመካኝነት መመዝገብ ይችላሉ፡፡

**ስተጨማሪ መረጃ ስልክ ቁጥር፡-** 0115159550/ 0115159548/

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ

# ስፖርት



## ቀጣዩ የዓለም አቀፉ ኦሊምፒክ ኮሚቴ መሪ ማን ሊሆን ይችላል?

**ብርሃን ፈይሳ**

ዓለም አቀፉ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ከወራት በኋላ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫውን ያካሂዳል፡፡ ዓለም አቀፉን ኮሚቴ ባለፉት ስምንት ዓመታት የመሩት የፕሬዚዳንት ቶማስ ባህ የሥልጣን ጊዜ መጠናቀቁን ተከትሎ ኮሚቴውን የሚመራ አዲስ ፕሬዚዳንት ለመምረጥ እጩዎች ከወዲሁ ራሳቸውን በማስተዋወቅ ላይ ይገኛሉ፡፡

እአአ ከ2013 አንስቶ በሁለት የሥልጣን ዘመን ኮሚቴውን የመሩት የ 70 ዓመቱ ባህ በኮሚቴው አዲስ ፕሬዚዳንት እንደሚያስፈልግና ከዚህ በላይ የሥልጣን ጊዜያቸውን ማራዘም አስፈላጊ አለመሆኑን ጠቁመዋል፡፡ በዚህም መሠረት በቀጣዩ የካቲት ወር 2017 ዓ/ም ምርጫው የኦሊምፒክ መነሻ በሆነችው ግሪክ የሚከናወን ይሆናል፡፡

ቀጣዩ የዓለም አቀፉ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ፕሬዚዳንት ለመሆንም 7 እጩዎች በምርጫው የመወዳደር ፍላጎታቸውን አሳይተዋል፡፡ ከእነዚህ እጩዎች መካከል ሁለቱ የቀድሞ የኦሊምፒክ ቻምፒዮናዎች ሲሆኑ፣ የመመረጥ ከፍተኛ እድል ይኖራቸዋል ተብሎ በልዩነት የስፖርት ቤተሰቡን ትኩረት ስበዋል፡፡ የተቀሩት እጩዎች ደግሞ የመካከለኛው ምስራቅ የዮርዳኖስ ልዑል ፈይሰል አል ሁሴን፣ ፈረንሳዊው የዓለም ብስክሌት ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ዴቪድ ላፓርቲየንት፣ ስፔናዊ ሁዋን አንቶኒዮ ሳማራንች፣ ስዊድናዊ ባለሀብት ዮሃን ኢሊያሽ እንዲሁም ጃፓናዊው የዓለም ጅምናስቲክ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ሞሪናሪ ዋታናቤን ናቸው፡፡

100 ዓመታትን በተሻገረው የዘመናዊው ኦሊምፒክ ታሪክ አንዲትም ሴት ፕሬዚዳንት ተመርጣ አታውቅም፡፡ በዚህ ምርጫ ብቸኛዋ ሴት ክርስቲ ኮቨንትሪ አፍሪካን በመወከል የቀረበች ሲሆን፤ ምናልባትም ጠንካራ ተፎካካሪ ይሆናሉ ተብለው ከሚጠበቁት እጩዎች መካከል አንዷ ነች፡፡ ከዚህ ቀደም ኮሚቴውን በፕሬዚዳንትነት ካገለገሉት መካከል 8 የሚሆኑት ከአህጉረ አውሮፓ የተገኙ ሲሆኑ፤ ከአሜሪካ አንድ ሰው በብቸኝነት መርጧል፡፡ ከወራት በኋላ በሚደረገው ምርጫ ሊያሸንፉ አሊያም ለተፎካካሪዎቻቸው ፈተና ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው ከሚጠበቁት እጩዎች መካከል ቀዳሚው አውሮፓዊው የዓለም አትሌቲክስ ፕሬዚዳንት ሰባስቲያን ኮ ናቸው፡፡



ብቸኛዋ ሴት እጩ ክርስቲ ኮቨንትሪ፤



የዓለም አትሌቲክስ ፕሬዚዳንት ሰባስቲያን ኮ፤

በምርጫው አሸናፊ ይሆናሉ በሚል የተገመቱት ሁለቱ እጩዎች ከሚኖራቸው የምረጡኝ ዘመቻ ፉክክር ባለፈ ሁለቱም ኦሊምፒክን በተወዳዳሪነት የሚያውቁትና የመድረኩን ታላቅነት ያጣጣሙ የቀድሞ አትሌቶች መሆናቸው ያመሳስላቸዋል፡፡ ትኩረት ሳቢዋና ነጭ የቆዳ ቀለም ያላት ዚምባቡዌያዊቷ ክሪስቲ እአአ በ1983 የተወለደች ሲሆን፤ በውሃ ዋና ሀገሯን በኦሊምፒክ መድረክ ማስጠራት የቻለች ብርቱ ስፖርተኛ ናት፡፡ እአአ በ2000 ኦሊምፒክ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ብትሆንም በመድረኩ ሀገሯን በመወከል እስከ ግማሽ ፍጻሜ በመጓዝ ቀዳሚዋ ዚምባቡዌያዊት ናት፡፡

በ2004 እና 2008 የአቴንስ እና ቤጂንግ ኦሊምፒኮች ላይም ሁለት ሁለት የወርቅና ብር ሜዳሊያዎችን አስመዝግባለች፡፡ በአህጉርና ዓለም አቀፍ ቻምፒዮናዎች በመሳተፍም በርካታ ሜዳሊያዎችን ማጥለቅ የቻለች ምርጥ ዋናተኛ ብቻም ሳትሆን በአፍሪካም ተወዳዳሪ ያልተገኘላት ብርቱ አትሌት ናት፡፡ እአአ ከ2017 አንስቶ ወደ ስፖርት አመራርነት የተሸጋገረችው የቀድሞዋ ዋናተኛ በዚምቧቡዌ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ምክትል ፕሬዚዳንት እንዲሁም በወጣቶች፣ ስፖርት፣ አርትና መዝናኛ ሚኒስትር ሆና እያገለገለች ትገኛለች፡፡ የ41 ዓመቷ ኮቨንትሪ ባለፈው ዓመት በዓለም አቀፉ የኦሊምፒክ ኮሚቴ ሥራ አስፈጻሚ አባልነት የተመረጠች ሲሆን፤ በዓለም አቀፉ የስፖርት አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ ውስጥም በአባልነት አገልግላለች፡፡

የዓለም አትሌቲክስ ፕሬዚዳንቱ ሰባስቲያን ኮ በበኩላቸው እአአ ከ2020 አንስቶ የዓለም አቀፉ ኦሊምፒክ ኮሚቴ አባል በመሆን በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡ በዓለም አትሌቲክስ ፕሬዚዳንትነት እአአ ከ2015 ጀምሮ ለሦስት የሥልጣን ዘመን ያገለገሉት እኚህ ሰው እአአ በ2027 የሥልጣን ዘመናቸው የሚጠናቀቅ ይሆናል፡፡ ነገር ግን በኦሊምፒክ ኮሚቴ ፕሬዚዳንትነት ለመመረጥ የእድሜ ገደቡ ከ70 ዓመት በታች በመሆኑ ጊዜያቸውን ላለማባከን የፈለጉ ይመስላል፡፡ የ68 ዓመቱ ኮ የአትሌቲክስ የሥልጣን ጊዜያቸውን ሲያጠናቅቁ ወደሌላኛው ተቋም በመዞር መሪነታቸውን የማጠናከር ፍላጎት አላቸው፡፡ በመሆኑም እንዳለፉት ፕሬዚዳንት ለ8 ዓመታትም ባይሆን ለ4 ዓመት የማገልገል ጽኑ ፍላጎት እንዳላቸው ዘገባዎች ያመላክታሉ፡፡

ከጊዜ ጋር ውድድር የገጠሙት ሰባስቲያን ኮ እአአ በ1956 የተወለዱ ሲሆን፤ ሀገራቸው እንግሊዝን ወክለው በ1980 ኦሊምፒክ በ1 ሺ500 ሜትር የወርቅ በ800 ሜትር ደግሞ የብር ሜዳሊያዎችን ሲያጠልቁ፤ እአአ በ1984 ኦሊምፒክም በተመሳሳይ ርቀቶች ተመሳሳይ ሜዳሊያዎችን ማስመዝገብ የቻሉ አትሌት ነበሩ፡፡ እአአ በ1990ዎቹ መጀመሪያ በተደጋጋሚ በሚገጥማቸው ጉዳት ምክንያት ከአትሌቲክስ ተወዳዳሪነት ራሳቸውን ሲያርቁ ፊታቸውን ወደ ፖለቲካው በማዞር ለዓመታት ቆይተዋል፡፡ ይሁንና ሀገራቸው እአአ የ2012 ኦሊምፒክ አዘጋጅ መሆኗን ተከትሎ በአመራርነት በድጋሚ ስፖርቱን በመቀላቀል አሁን ካሉበት ሊደርሱ ችለዋል፡፡

ብርሃን | ብርሃን ባንክ Berhan Bank

## የብርሃን ባንክ አክስዮን ማህበር
## የባለአክስዮኖች 15ኛ መደበኛ እና 6ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የጉባኤ ጥሪ

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የንግድ ሕግ አንቀጽ 366(1)፣367(1) እና 370 እንዲሁም በአክስዮን ማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ 9(3) እና መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 12(2) መሰረት የብርሃን ባንክ አክስዮን ማህበር የባለአክስዮኖች 15ኛ ዓመታዊ መደበኛ እና 6ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ጥቅምት 7 ቀን 2017 ዓ.ም ከጠዋቱ 2:00 ጀምሮ አዲስ አበባ ቦሌ በሚገኘው ሚሊኒየም አዳራሽ ይካሔዳል። ስለሆነም የተከበራችሁ ባለአክስዮኖች በዕለቱ በጉባኤው ላይ እንድትገኙልን የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያስተላልፋል።

1. የአክስዮን ማህበሩን የሚመለከቱ ዋና ዋና መረጃዎች
   - 1.1 የዋና መሥሪያ ቤት አድራሻ አዲስ አበባ፤ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 2185 ፤ ድህረገጽ www.berhanbanksc.com
   - 1.2 የምዝገባ ቁጥር = 06/1/28428/01
   - 1.3 የተፈረመ ዋና ገንዘብ/ካፒታል/ = 3,450,894,000
   - 1.4 የተከፈለ ዋና ገንዘብ/ካፒታል/ = 3,450,894,000
2. የ15ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች
   - 2.1 አጀንዳውን ማጽደቅ፤
   - 2.2 የተከናወኑ የአክስዮን ዝውውሮችን ማጽደቅና አዳዲስ ባለአክስዮኖችን መቀበል፤
   - 2.3 የዳይሬክተሮች ቦርድ እ.ኤ.አ. የ2023/24 ዓመታዊ ሪፖርት ማዳመጥ ፤
   - 2.4 የውጭ ኦዲተር እ.ኤ.አ. የ2023/24 ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርት ማዳመጥ ፤
   - 2.5 ከዚህ በላይ በቀረቡት ሪፖርቶች ላይ ተወያይቶ መወሰን፤
   - 2.6 የውጭ ኦዲተር መሰየምና ክፍያቸውን መወሰን
   - 2.7 በዘመኑ የተጣራ ትርፍ አደላደል እና አከፋፈል ላይ ተወያይቶ መወሰን፤
   - 2.8 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ወርኃዊ አበልና ዓመታዊ ክፍያ መወሰን፣
   - 2.9 የጉባዔውን ቃለጉባዔ ማጽደቅ
3. የ6ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች
   - 3.1 አጀንዳውን ማጽደቅ፤
   - 3.2 የባንኩን/ማህበሩን ካፒታል ማሳደግ፤
   - 3.3 የባንኩን/ማህበሩን የመመስረቻ ጽሁፍ ማሻሻል/ መተካት/
   - 3.4 የጉባዔውን ቃለጉባዔ ማጽደቅ ፤
4. ማሳሰቢያ

4.1 በጉባኤው ላይ ለመገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች በንግድ ሕግ አንቀጽ 377 መሰረት ጉባኤው ከሚካሄድበት ቀን አስቀድሞ ባሉት ቀናት ውስጥ በባንኩ ዋና መስሪያ ቤት የአክስዮን አስተዳደር ክፍል በመገኘት የውክልና ፎርም/ቅጽ በመሙላት ተወካይ በመወከል ወይም፤ በስብሰባው ለመገኘትና ድምጽ ለመስጠት የሚያስችል የውክልና ማስረጃ ያለው ተወካይ ዋናውን እና አንድ ፎቶ ኮፒ በጉባኤው ዕለት ይዞ እንዲቀርብ በማድረግ በወኪሎቻቸው አማካይነት መሳተፍ የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን። ሆኖም አንድ ባለአክስዮን መወከል የሚችለው አንድ ተወካይ ብቻ መሆኑን እናሳስባለን።

4.2 የአክስዮን ማህበሩ ባለአክስዮኖች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በጉባኤው ላይ ለመሳተፍ በሚመጡበት ጊዜ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፍቃድ ዋናውንና ኮፒ መያዝ አለባቸው። እንዲሁም ትውልደ ኢትዮጵያውን የውጭ አገር ዜግነት ያላቸው የማህበሩ ባለአክስዮኖች ትውልደ ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ቀኑ ያላለፈበት መታወቂያ( ቢጫ ካርድ) ይዘው መቅረብ እንዳለባቸው በአክብሮት እናሳውቃለን።

4.3 በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳ ከሚደረግባቸው ጉዳዮች መካከል የቀድሞውን መመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ በአንድ ላይ አካቶ በያዘውና ተሻሽሎ በተዘጋጀው የረቂቅ መመስረቻ ጽሁፍ ላይ መወያየት ይገኝበታል። ስለሆነም የተዘጋጀውን ረቂቅ የመመስረቻ ጽሁፍ ከባንኩ ድረገጽ ላይ በማውረድ መመልከት ወይም አክስዮን አስተዳደር ክፍል በመቅረብ መውሰድ የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን።

**የብርሃን ባንክ አ.ማ**
**የዳይሬክተሮች ቦርድ**